

Dar Al Ber Society
THE EMIRATES
مركز المعلومات الإسلامي
Islamic Information Center
This is Islam
Part of the
ISLAMIC
e-LIBRARY
Your Path To Peace..
@islamicicdxb
ይህ ነው
እስልምና
በዓለም ላይ በፍጥነት እየተስፋፉ በሚገኙ ሃይማኖቶች ዙሪያ የተደረገ ጥልቅ እይታ



# ይህ ነው እስልምና

በዓለም ላይ በፍጥነት እየተስፋፉ በሚገኙ
ሃይማኖቶች ዙሪያ የተደረገ ጥልቅ እይታ

ISLAM



LAUNCHING CURIOSITY

ነቢዩ ኢብራሂም እሱን ይገነቡ ዘንድ ወዳዛዘቻቸው፣ ሙስሊሞችም በየትኛውም ስፍራ ላይ ሆነው ስግደት ሲፈጽሙ ፊታቸውን ወደርሱ እንዲያዞሩ አላህ ወዳዘዛቸው ወደካዕባህ ፊታቸውን ሲያዞሩ የሚያሳይ ከሕዋ የተነሳ ምስል

THIS IS ISLAM

# ይህ ነው
# እስልምና

በዓለም ላይ በፍጥነት እየተስፋፉ በሚገኙ ሃይማኖ
ቶች ዙሪያ ጥልቅ እይታ

ፈህድ ሳሊም ባህማም



- **በዙሪያህ** ባሉ መገናኛ ብዙሃን በብዛት ክርክር በሚያስነሱ ሃይማኖቶች ዙሪያ ግልጽ የሆነ እይታ ማግኘት አያሳስብህምን?...
- **እንደው** ላፍታ ቆም ብለህ በዓለም የስታትስቲክስ መረጃ መሰረት ከሃይማኖቶች መካከል በስፋት እየተሰራጨና በፍጥነት ተቀባይነትን እያገኙ ካሉ ሃይማኖቶች መካከል ስለአንዱ በጥልቀት ማወቅ እንዳለብህ ግድ አይልህምን?...
- **ስለሌሎች** ማህበረሰቦች ባህል እንዲሁም ማህበረሰቦቹ ስለሕይወት፣ ሰለሃይማኖትና ሌሎች በዙሪያችን ስለሚገኙ ነገሮች ያላቸውን ፍልስፍና በማወቅህ ታላቅ ደስታና እርካታ አታገኝምን?
- **ስለእስልምና** ሃይማኖት ከተረጋገጡ ምንጮቹ መረጃዎችን ለማወቅና ካወቅክ በኋላ አእምሮህንና ችሎታህን ተጠቅመህ በእነሱ ላይ ለመወሰን ለነፍስህ እድል ትሰጣለህን?

እንዲህ የምትመለከት ወይም ከእሱ ውስጥ አስፈላጊ የሆነ አንድ ነገር ወይም ደስ የሚያሰኝ ነገር የምትመለከት ከሆነ ይህ መጽሐፍ ለማግኘት የምትፈልገውን ነገር ለማግኘት ያግዛሃል፡፡

# የመጽሐፍቱ ርዕሶች

ሁላችንንም እንቅልፍ የሚነሱ ጥያቄዎች 12

የእስልምና ዓለም አቀፋዊነት 19

አንድ ፈጣሪ . . . አንድ ተመላኪ 53

በእውነት መልዕክተኞች እነማን ናቸው? 68

እስልምና በዒሳ(ዐ.ሰ) (ኢየሱስ) ላይ ያለው አቋም 74

የእስልምና መልዕክተኛ ማን ናቸው? 84

Click on topic to go to the page.


ቁርኣን ከየት
ነው የመጣው?
144
Click to go to the page.

የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድ በፍትሐዊ አስተዋዮች እይታ 93

ከመልዕክተኛው ሙሐመድ የሕይወት ታሪክና ስነ-ምግባራት በከፊል 107

ከሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግሮች መካከል 124

ቁርአን ዘላለማዊ የእስልምና ተአምር 133

ቁርአን ከየት ነው የመጣው? 144

በእስልምና የአምልኮታዊ ተግባራት ተልእኮ ምንድን ነው? 160

ቤተሰብ በእስልምና 192


ቤተሰብ በእስልምና
192
Click to go to the page.

በእስልምና የሴቶች ስፍራ 203

እስላማዊው ሕግ በምግብና በመጠጥ ላይ 222

ሐጢአት እና ንሰሐ 237

የሃይማኖት እና የአእምሮ ተቃርኖ 244

እስልምና የሰላም ሃይማኖት ነው 255

በእስልምና እና በተወሰኑ ሙስሊሞች መካከል ያለው ነባራዊ ሁኔታ 267


የሃይማኖት እና
የአእምሮ ተቃርኖ
244
Click to go to the page.



# ሁላችንንም እንቅልፍ የሚነሱ ጥያቄዎች



ስንቶቻችን ነን በሕይወት ዘመናችን አንድ ቀን ላፍታ ቆም ብለን ነገሩ ምንድን ነው? እኔ ማን ነኝ? ከየትስ ነው የመጣሁት? ወዴት ነው የምሄደው? ፍጻሜዬስ ምንድን ነው? የዚህ ሁሉ ግኝትስ ዓላማው ምንድን ነው? የዚህች ዓለም ፍጻሜ በርግጥ ሞት፣ አፈር መሆንና መጥፋት ከሆነ በዚህ ዓለም ላይ የሚደረገው ሁሉ ድካም ፋይዳው ምንድን ነው ብለን የምናውቀው?

ሙስሊሞችም ሆኑ የሰማያዊ ሃይማኖት ተከታዮች ፍትሐዊ በሆነ ፈጣሪ መኖርና መልካም የፈጸመ ሰው መልካም ምንዳውን፣ ሃጢአት የፈጸመውም ተገቢ የሆነ ቅጣቱን ያገኛል የሚለው እምነት በልቦናቸው ውስጥ ከሌለ የሰው ልጅ ሕይወት ትርጉም የለሽ ጨዋታ፣ ምትክ የለሽ ቅጣትና ሕመም፣ ፋይዳ ቢስ ቧልት እንደሆነ ያምናሉ፡፡

ፍትሐዊ፣ ያሻውን የሚፈጽም የሆነ ፈጣሪ በመኖሩ ላይና ይህ ፈጣሪ ለዚህች ዓለም ሕይወት ፍጻሜ እንዳደረገ፤ ከፍጻሜ በኋላ እያንዳንዱ የሰው ልጅ በምድር ላይ ይፈጽመው በነበረው ተግባር ምክንያት የእጁን እንደሚያገኝ እስካላመንክ ድረስ የዚህችን ዓለም ሕይወት ተቃርኖ፣ የኑሮ አለመመቸት፣ ስህተት፣ ትክክለኛነትና ችግር ፈጽሞ ልትረዳ አትችልም፡፡

ጥልቅ እምነት በሁሉም የሕይወታችን እሴቶችና ግንዛቤዎቻችን ውስጥ ሲሰርጽ ብቻ ነው ሁሌም የምንናዘዛቸው አሊያም የሕይወት መሰረቶች ናቸው ብለን የምንጠራቸው እንደ ፍትሕ፣ ፍቅር፣ መተዛዘን፣ እውነተኝነት፣ ትእግስትና ርህራሄ ከእውነተኛው ሕይወት ጋር የመቆራኘታቸው ትርጉም የሚገባን፡፡ የትግበራው ጣእም የሚታወቀን፡፡ እንዲሁም የትእግስትን ጣእም ልናጣጥም የምንችለው፡፡

> የሕይወት ተቃርኖዎችን፣ የኑሮን ከባድነት፣ የስሕተትን፣ ትክክል የመሆንንና የመቸገርን ምስጢራዊ ጥበብ ፍትሐዊ ጥበባዊ በሆነው ጌታ እስካላመንን ድረስ ልትረዳ አትችልም፡፡

የሙስሊሞች ቅዱስ መጽሐፍ የሆነው ቁርኣን ይህንኑ ያመላክታል፡፡ አላህ የሚያስተውልና የሚያስተነትን አእምሮ ሰላላቸው ሰዎች በቁርኣን ውስጥ እንዲህ በማለት ነግሮናል፡፡

“በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያሰተነትኑ፡- ‹‹ጌታችን ሆይ! ይኸን በከንቱ አልፈጠርከውም ጥራት ይገባህ›...” (3፡191)

## የእስልምና ሃይማኖት

በምድር ላይ ያሉት አብዛኛዎቹ ሃይማኖቶች በግለሰብ ወይም በሕዝብ ወይም በተመሰረቱበት ሐገር ስም የተሰየሙ ናቸው፡፡ ክርስትና ስያሜውን ያገኘው ከመሲሕ (የአላህ ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን) ሲሆን አይሁድ ይሁዳ ከተሰኘ ጎሳ፣ ቡድሂዝም ሃይማኖቱን መስራች ከሆነው ቡድሃ የተባለ ግለሰብ፣ ሒንዱዊዝም ደግሞ ከሕንድና..... ወ.ዘ.ተ እንዲሁ ስያሜዎቻቸውን አግኝተዋል፡፡

እስልምና ግን በአንድ ግለሰብ ወይም ጎሳ ወይም ብሔር ወይም ሕዝብ የሚሰየም ሃይማኖት አይደለም፡፡ ለዚህም ነው እስልምና የሚሰየምበት ሕዝብ የሌለውና በራሱ አንደበት የፈጠረው፣ በሱ ስም የሚጠራበት የሆነ ግለሰብ የለውም፡፡ በዚህ የተነሳም ሃይማኖቱ እስልምና የሚል ስያሜ ተሰይሟል፡፡ ለየት ያለ ጎሳ...........

## ‹‹እስልምና›› የሚለው ቃል ትርጓሜ

እስልምና ወደሚለው የዐረብኛ ቃል ግኘት ስንመለስ ቃሉ እጅ መስጠት፣ መተናነስ፣ መታዘዝ፣ ቅንነት፣ ደህንነትና መረጋገት የሚሉ በርካታ ትርጓሜዎችን በውስጡ አካቷል፡፡

እስልምና ማለት፡- ምሉእ የሆነን መታዘዝ፣ ሁሉን አጠቃሎ ለያዘ ጌታ እጅ መስጠትና ከእሱ ውጭ ላሉ ነገሮች ከሚፈጸም አምልኮታዊ ተግባራት ራስን ነጻ ማውጣት ማለት ነው፡፡

ስለእስልምና በቁርአን ውስጥ በበርካታ የቁርአን አንቀጾች ውስጥ ተረጋግጦ የተቀመጠው ትርጓሜ ይህ ነው፡፡

በልቦናውና በመላ አካላቱ ወደአላህ ራሱን ያዞረ፣ በመተናነስ እጅ የሰጠ፣ ለትእዛዛትና ለክልከላዎች ታዛዥ የሆነ ሰው በእርግጥ ፈጽሞ የማይበጠስ የሆነውን የነጻነት ገመድ እንደያዘና ሁሉንም መልካም እንዳገኘ ብሎም እንደተቀዳጀ ቁርአን ይነግረናል፡፡

‹‹እርሱ መልካም ሠሪ ሆኖ ፊቱን ወደ አላህ የሚሰጥም ሰው ጠንካራን ገመድ በእርግጥ ጨበጠ፡፡ የነገሩም ሁሉ ፍጻሜ ወደ አላህ ነው፡፡›› (31 ፡ 22)

ስለዚህ እስልምና ማለት አምልኮትን በሙሉ ለአላህ መስጠትና ራስን ከአላህ ውጭ ከሚፈጸሙ አምልኮዎችና

ከርሱ ሌላ ላሉ ነገሮች ከሚፈጸም የታዛዥነት ስነ-ምግባር ነጻ ማውጣት ማለት ነው፡፡ ሙስሊም ማለት ደግሞ ለአምልኮቱ ቅን የሆነ፣ በውስጣዊ ሰላም የሚኖርና በዙርያው ሰላምን የሚያሰራጭ ማለት ነው፡፡

ነገር ግን ይህ መልዕክተኞች በሙሉ ይዘውት የመጡት ነገር ነውን?

## እስልምና የሁሉም መልዕክተኞች ሃይማኖት ነው፡፡

በተለያዩ ጊዜያት በምድር ላይ ይኖሩ ለነበሩ ሕዝቦች የአላህን ሃይማኖት የሚያስተምሯቸው በርካታ መልዕክተኞች ተልከውላቸው እንደነበር፣አላህም በቁርኣን ላይ መልዕክተኛው የሆኑትን ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ)

«እኛ አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን በእውነቱ (መምሪያ) ላክንህ፡፡ ማንኛይቱም ሕዝብ በውስጧ አስፈራሪ ያላለፈባት የለችም፡፡» (35፡24)

በማለት ሲያናግር ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልዕክተኞች በአጠቃላይ እውነተኛ ሃይማኖትን ይዘው እንደመጡ፣ሁሉም ይዘዋቸው በመጧቸው የእምነት መልዕክት፣መሰረተ-ሕግጋትና ስነ-ምግባራት ፈጽሞ እንደማይለያዩ ቁርኣን አረጋግጧል፡፡

የነብያት መደምደሚያ የሆኑት ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከአንድ ሺህ አራት መቶ ዓመታት በፊት የተላኩበት እስልምና ቀደምት መልዕክተኞች በአጠቃላይ ከተላኩበት ሃይማኖት ጋር ተያይዞ የመጣ ሃይማኖት ነው፡፡ ሙስሊሞች እንደ ኢብራሂም፣ኢስሐቅ፣ ያዕቁብ፣ ሙሳ፣ ዒሳ የመሳሰሉ ቀደምት መልዕክተኞች ያመኑበትን እንዲያምኑ ቁርኣን ያዛል፡፡ (2፡136)

ለምሳሌ ያህልም «በርግጥ አላህ እውነተኛ የሆነ ሃይማኖትን መርጦላቻኋል፡፡ እስከትሞቱ ድረስም በእስልምና ላይ ጽኑ፡፡» በማለት የነቢያት አባት የሆኑት ኢብራሂምና የዕቁብ ለልጆቻቸው የሰጡትን ምክር አስቀምጦልናል፡፡ (2፡132)

ይህ ሃይማኖት ከነቢያት ባጠቃላይ የተያዘ ሃይማኖት ነው፡፡ የእምነት መሰረቱ አንድ ነው፡፡ ትክክለኛ መሰረቱ ፈጽሞ አይቀየርም፡፡ የመጨረሻው መልእክተኛ ሙሐመድ (በእሳቸው ላይ ሰላም ይሁን) በመልእክተኛነት ተልከው ለሰው ልጆች ባጠቃላይ የመጨረሻዎቹን ድንጋጌዎች እስከሚቋጩ ድረስ በእርግጥ ሊቀየሩ የሚችሉት ከተለያዩ ዘመናት ሁኔታዎች ጋር ለማጣጣም ሲባል ሕግጋቱና የሕግጋቱ ዝርዝር ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ከዚህ በመነሳትም በዓለም ላይ ብቸኛው ሃይማኖት እስልምና እንደሆነ፣ በምድራችን ላይ የምንመለከተው በሰማያዊ ሃይማኖቶች እምነት መካከል ያለ ልዩነት ሊከሰት የቻለው በእምነቶቹ ላይ ከተፈጸመው የመበረዝ ተግባር በስተቀር ሌላ እንዳልሆነ፤ይህም መልዕክተኞች ከመጡበት ቀጥተኛ መንገድ እንዲርቁና እንዲያፈነግጡ ያደረጋቸው መሆኑን ቁርኣን ግልጽ በሆነ ሁኔታ ያረጋግጣል (3፡19)

> ኢስላም የተሰኘው ቃል በዐረቢኛ ቋንቋ ውስጥ እጅ በመስጠት፣ በመተናነስ፣ በመታዘዝ፣ በቅንነት፣ በደህንነትና በመረጋጋት መካከል የሚንሸራሸሩ በርካታ ትርጓሜዎችን ይዟል፡፡

# የእስልምና ዓለም አቀፋዊነት



# ቁርኣን

ቁርኣን በዐረቦች ምድርና ቋንቋ የወረደና የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድ በእነርሱ ውስጥ ሆነው ለዓለም የተላኩ ቢሆንም በቁርኣን ውሰጥ ‹ዐረብ› የሚል ቃል ፈጽሞ አለመኖሩ በጣም የሚገርም ነው፡፡ በአሁኑ ዘመን ከአጠቃላዩ የሙስሊሞች ቁጥር የዐረቦች ቁጥር በእጅጉ አነስተኛ ነው፡፡እንዲያውም ከዓለማችን ሙስሊሞች አጠቃላይ ቁጥር ከ20% በታች የሚሆኑት እነርሱ እንደሆኑ መረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡ በዓለም ላይ ካሉ ሀገራት በርካታ የሙስሊም ቁጥር ያላት በደቡብ ምስራቅ እስያ የምትገኛዋ ሀገር ኢንዶኔዥያ ነች፡፡ ዝቅተኛ የሙሰሊሞች ቁጥር ያላት ሀገር ደግሞ ሕንድ ስትሆን ሕንድ ውስጥ የሚገኙት ሙስሊሞች ቁጥር ከዐረብ ሀገራት የሙስሊሞች ቁጥር በእጅጉ ይበልጣል፡፡



# እስልምና

እስልምና ዘር፣ ቀለም፣ ጎሳ፣ ብሔር፣አህጉርና ሀገር ሳይለይ ለሁሉም ሕዝቦች እዝነትና ወደ ቀጥተኛው መንገድ መመሪያ ሆኖ መጥቷል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፣ ‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም፡፡›› (21፡107)

ቀደምት ሥርዓቶች ለሰው ልጆች በዘር፣በቀለም፣ ጎሳ፣ብሔር መለያየት ፍጹም ሰጥተውት ያልነበረውን እውቅና እስልምና ሰጥቷል፡፡

ይህን እስላማዊ አስተምህሮ ለማረጋገጥ ቁርኣን ዐረቦችና ሙስሊሞች ሳይል ሁሉንም የሰው ልጆች በአንድነት የሚያናገርበትን ሁኔታ እንደሚከተለው እናስተውል፡፡ አላህ ቁርኣን ውስጥ እንዲህ ብሏል፣ ‹‹እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፤ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፤ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፤አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው፡፡›› (49፡13)



እዚህ ላይ ቁርኣን የሚያረጋግጥልን ምንም ቢሆን የሰው ልጆች በአጠቃላይ በዘር ሐረግና በቀለም የተለያዩ ቢሆኑም የሰውነት ዘራቸው ግኝትና መነሻ አደምና ሐዋ (አዳምና ሔዋን) (ዐ.ሰ) እንደሆኑ፣በመካከላቸው ያለው የዘርም ሆነ የቀለም ልዩነት በምንም መልኩ በእነርሱ መካከል ማበላለጫ እንዳልሆነ፣በተቃራኒው እንዲህ ልዩነት ኖሯቸው የተፈጠሩት ይተዋወቁ፣ተዋውቀውም እንዲተጋገዙና እንዲረዳዱ ዘንድ ነው፡፡ በሰው ልጆች መካከል ልዩነት የሚፈጥረው ነገር የፈጠራቸውንና የሚያኖራቸውን ጌታቸውን አላህን በመፍራት በሚኖራቸው የደረጃ ልዩነት ብቻ ነው፡፡

> እስልምና ሌሎች ስርአቶችና የዓለም ሕዝቦች ፈጽሞ በማያውቁት መንገድ ስለሰው ልጆች ብዝሃነት ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

የሰው ልጆች በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በቋንቋ፣በባህል፣ በአኗኗር መለያየታቸው በዚህ ፍጥረተ-ዓለም ትልቅ የአላህ ጸጋ፣የአፈጣጠሩ ተአምር መሆኑን ከሰማያትና ምድር አፈጣጠር ጋር አነጻጽሮና ያላቸውን ጠቀሜታ እንዲሁ አንድ ላይ በማቅረብ የዚህን ውስጠ ምስጢር የእውቀት ባለቤቶችና የሚያስተነትኑ ሰዎች ብቻ የሚያውቁ መሆኑን የመግለጹ ጥበብ ቁርኣን አትኩሮታችንን ከሚስብበት ነገሮች መካከል አንዱ ነው (30፡22)

የሰውን ልጅ እኩልነት የሚያረጋግጥው የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደነገገው እ.ኤ.አ. በ1948 ሲሆን ተግባራዊ የሆነው ደግሞ ከዚያ በኋላ በነበሩት ጥቂት ዓመታት በኋላ ነው፡፡ ነገር ግን የእስልምና መልዕክተኛ የሆኑት ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከዛሬ 1400 ዓመታት በፊት በስፋት ደንግገውት ነበር፡፡ «እናንተ ሰዎች ሆይ! አዋጅ! ጌታችሁ አንድ ነው፡፡ አዋጅ! አባታችሁም ነው፡፡ አዋጅ! ዐረብ በሆነውና ባልሆነው፣ ዐረብ ባልሆነውና ዐረብ በሆነው፣ቀይ በሆነውና ጥቁር በሆነው፣ጥቁር በሆነውና ቀይ በሆነው መካከል አላህን በመፍራት ካልሆነ በስተቀር ምንም ብልጫ የለም፡፡» (አሕመድ 23489) በሚለው ንግግራቸው ለሰው ልጅ አዲሱን የብርሃንና የእኩልነት መብት አብስረዋል፡፡



እንደ አውሮፓዊያን
አቆጣጠር በ630
ዓመተ-ልደት



ሙሐመድ የኢስላም መልእክተኛ

“የሰው ልጆች ሆይ! አዋጅ! በርግጥ አባታችሁ አንድ ነው፡፡ አዋጅ! ዐረብ የሆነ ሰው ዐረብ ባልሆነ ሰው ላይ እንዲሁም ዐረብ ያልሆነ ሰው ዐረብ በሆነ ሰው ላይ፤ ቀዩ በጥቁሩ፣ ጥቁሩ በቀዩ ላይ አላህን በመፍራት ካልሆነ በስተቀር ምንም ብልጫ የለውም፡፡”



እንደ አውሮፓዊያን
አቆጣጠር በ1948
ዓመተ-ልደት

ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት

ነጻነትን፣ መብቶችንና ክብርን የሚያናፍሱትን ሰዎች እኩልነት የሚያረጋግጥ የሆነ ነው፡፡

## አካባቢን መንከባከብከ ከእምነት አንዱ ክፍል ነው፡፡

የሰው ልጅ ያለ ማንም ተቆጣጣሪነትና የበላይ ኃላፊነት ፍጥረተ-ዓለሙን ያለ ገደብ እንዳሻው የሚያስተዳድር ብቸኛው ፍጡር ነው በማለት አንዳንድ ፍልስፍናዎች ይገምታሉ፡፡ ነገር ግን ፍልስፍናዎቹ እንደሚሉት ቢሆን ኖሮ ፍጥረተ-ዓለሙ በተበላሸና በፍጥረተ-ዓለሙ ውስጥ የሚኖሩ፣ ከሰው ልጅ ውጭ ያሉ የፍጡራን ዓይነቶች፡ - በአጠቃላይ የሰው ልጅን ፍላጎት እስካላሟሉ ድረስ ለዓይነት እንኳ ሳይቀሩ ሙሉ ለሙሉ በጠፉ፣ፍጥረተ-ዓለሙም በተበላሸ ነበር፡፡ታዲያ የሰው ልጅ ከፍጥረተ-ዓለሙ ጋር ሊኖረው የሚገባውን ግንኙነት እስልምና እንዴት ይመለከተዋል? የሚል ጥያቄ አንስተን እስልምና ለፍጥረተ-ዓለሙ የሰጠውን ትኩረት በአጭሩ መመልከትና መረዳት እንችላለን፡፡

የእስልምና አብይ እይታ የሚመሰረተው፡- የሰው ልጅ ለፍጥረተ-ዓለሙ ካለው እሳቤና ቀጥተኛ ግንኙነት ላይ ሲሆን ይህ ሁኔታ ከሰው ልጅ፣ ከእንስሳት፣ ከምድርና ከተፈጥሯዊ ምንጮች ጋር የሚኖርን ትስስር ሥርአት ያለው ይሆን ዘንድ በሚደረጉ ግልጽ ድንጋጌዎች ይቋጫል፡፡

ስለእስልምና በፍጥረተ-ዓለሙና በሰው ልጅ መካከል ያለውን አመለካከት የሚያጠና ሰው የሚያገኘው አብይ ነገር ሚዛናዊነት ነው፡፡ አላህ የሰው ልጅን ከሌሎች ፍጡራን መካከል ለይቶ ፈጥሮታል፡፡ ክብርንም አጎናጽፎታል (17፡70) ይጠቀምበትና ፍላጎቱን ያሟላበት ዘንድም በዙሪያው ያሉትን ነገሮች ሁሉ ገር እንዲሆኑ አድርጎለታል፡፡ (14፡32-33) የሰው ልጅ በበሊዮኖች ከሚቆጠሩ ሌሎች ፍጡራን መለያ የሌለው ፍጡር አይደለም፡፡ በተቃራኒው ከሌሎች ፍጡራን የሚለይባቸው በርካታ ባህሪያት ያለው፣የላቀና የተከበረ እንዲሁም ተፈጥሮ እርሱን ታገለግል ዘንድ የተመቻቸለት የሆነ ፍጡር ነው (2፡29)

የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጡራን በተለየ በአላህ ዘንድ ክብርን የተጎናጸፈ ፍጡር ቢሆንም በፍጥረተ-ዓለሙ ላይ ወሰንና ድንበር የሌለው ስልጣን ባለቤት አይደለም፡፡ ከሌሎች ፍጡራን መካከል የተለየ በመሆኑ ብቻ የሚፈልገውንና ያሻውን ያለገደብ መፈጸም አይችልም፡፡ ይህ መለያው ፍጥረተ-ዓለሙን እንዲያበላሽና እንዲያወድም መብቶችን አልሰጠውም፡፡ ምክንያቱም የፍጥረተ-ዓለሙ ባለቤት፤ፍጥረተ-ዓለሙን፣ በውስጡ የሚገኙትን ፍጡራንንና ራሱን የሰው ልጅን የፈጠረው ነው፡፡ ፈጣሪውን ተክቶ ፍጥረተ-ዓለሙን ከብክነትና ጉዳት በመታደግ በሥርዓቱ ያስተዳድርና ያለማ ዘንድ አላህ መብቱን ሰጥቶታል (11፡61) (2፡11)

በሰው ልጅና በፍጥረተ-ዓለሙ፣በሰው ልጅና በዙሪያው በሚገኙ ሌሎች ፍጡራን መካከል ሊኖር የሚገባውን ሚዛናዊነትን የጠበቀ ግንኙነትን አስመልክቶ እስላማዊው ሕግ (ሸሪዓ) በመቶዎች የሚቆጠሩ ደንብና ሥርዓቶችን አስቀምጧል፡፡ ለምሳሌ ያህል፡-

1. እንስሳትን መንከባከብ

የእንስሳትን መብቶች በመጠበቅ የሚያነሳሱ፣ ለእንስሳቱ መልካም የዋለላቸው ሰው በወዲያኛው ዘላለማዊ ዓለም የላቀ ሽልማት እንዳለው የሚያበስሩ፣ እንስሳትን ከመጉዳት የሚከለክሉና በእነሱ ላይ ጉዳት የሚያስከትልን ሰው በወዲያኛው ዓለም በብርቱ ቅጣት የሚያስጠነቅቁ በርካታ ነገሮች ከሙሐመድ (በእሳቸው ላይ ሰላም ይሁን) ተዘግበዋል፡፡

በዓለማችን ላይ የተለያዩ ጉዳዮችን አስመልክተው በተለያዩ ጊዜያት በሀገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደነገጉ ድንጋጌዎችና እነዚህን ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የተቋቋሙ ድርጅቶች ቁጥር እጅግ በርካታ ነው፡፡ የእንስሳት መብቶችን አስመልክተው ከተቋቋሙት መካከል የግንባር ቀደምትነቱን ስፍራ የሚይዘው እ.ኤ.አ. በ1824 እንግሊዝ ውስጥ የተቋቋመው ‹‹የንጉሳዊያን የእንስሳት መብቶች ማህበር›› የተሰኘው ተቋም ነው፡፡ በቅርብ ጊዜ በእንስሳት ላይ የሚደርሱትን ጥቃቶች የሚያወግዝና ድርጊቱንም በወንጀል ተርታ የሚያስቀምጠው ሕግ የተደነገገው እንግሊዝ ውስጥ እ.ኤ.አ 1949 ላይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እስልምና ከ14 ክፍለ-ዘመናት በፊት በእንስሳት ላይ የሚደርሱትን ጥቃቶች የሚያወግዙና ድርጊቱንም ከወንጀል ተርታ የሚመድቡ አንቀጾችን አስፍሯል፡፡ ምሳሌውንም በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አንደበት አስቀምጧል፡፡ ለምሳሌ ማንኛውንም እንስሳ እንዲራብ ማድረግ፣ ያለ አግባብና በመጥፎ

ሁኔታ መቅጣት፣ በምንም ዓይነት ምክንያት ይሁን በምንም ነገር ፊታቸውን መምታት ወ.ዘ.ተ የመሳሳሉና በእስልምና ሥነ-ሕግ መጽሐፍት ውስጥ የሰፈሩትን ሁሉ መፈጸም ክልክል እንደሆነ በግልጽ አስቀምጧል፡፡

ማንኛውም አንባቢ እስልምና ለእንስሳት ያስቀመጠውን ልዩ እንክብካቤ በቀላሉ ሊያውቅ የሚችለው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣አንዲት በዝሙት ሥራ የተሰማራች ሴት (ዝሙት በእስልምና ከባባድ ወንጀሎች ከሚባሉት መካከል አንዱ ነው) በውሃ ጥም ምክንያት ሊሞት የተቃረበ ውሻን ሁኔታ ተመልክታ በማዘኗ ጫማዋን በማውለቅ ከኩሬ ውስጥ ውሃ ከሞላችው በኋላ ውሻውን በማጠጣቷ ምክንያት አላህ ወንጀሏን እንደማረላት ለሰዎች እንደተናገሩ ሲያነብ ነው፡፡ (ቡኻሪ 3280)



እንስሳት እንዲራቡ ማድረግን፣ ማሰቃየትን፣ ካቅማቸው በላይ ማሸከምን ወይም ጉዳት በሚደርስባቸው ሁኔታ በእነሱ መጫወትን እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ632 ዓመተ-ልደት ክልክል አድርጓል፡፡



እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1824 ዓመተ-ልደት የመጀመሪያው የእንስሳት መብቶች ጉባኤ



እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1949 ዓመተ-ልደት በእንስሳት ላይ የሚፈጸም ወንጀልን የሚቀጣ ሕግ ለመጀመሪያ ጊዜ እንግሊዝ ውስጥ ጸደቀ፡፡





2. ዕጽዋትን መንከባከብ፡

ራስን ለመጥቀምም ይሁን ሌሎች ሰዎችን ወይም ሌሎች በፍጥረተ-ዓለሙ ውስጥ የሚኖሩ ፍጡራንን ለመጥቀም ሰዎች ዕጽዋትንና የእርሻ ስፍራዎችን እንዲንከባከቡ እስልምና አሳስቧል፡፡

ይህን በተመለከተ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አንድ ሰው እህል ከዘራ ወይም ፍጡራንን ለሚጠቅም በሚደረግ የዕጽዋት አስተዳደግና እንክብካቤ ሥራ ውስጥ ከተሳተፈና ከዚህ አዝርእት ላይ አእዋፋት ወይም ሰዎች ወይም እንስሳት ከተመገቡ ሰውዬው ባያስበውም ይህ ተግባሩ እንደ ሰደቃህ (ምጽዋት) እንደሚቆጠርለት ነግረውናል፡፡ (ቡኻሪ 2320)

እንዲያውም እኚህ ቸር የሆኑ ነቢይ አንድ ሙስሊም በጣም ከፍተኛ በሆነ ችግር ውስጥ ቢሆንም አካባቢን በመንከባከብ፣ በመሬቱ ምንም ዓይነት ጥቅምና ትርፍ ባያገኝም እንኳ በእርሻና በእጽዋት ምድርን በማልማት፣ በማሳመር ሂደት ማድረግ የሚችለውን ጥረት ፈጽሞ እንዳይደብቅና እንዳይሰስት እንዲህ በማለት መክረዋል፤ ‹‹የትንሳኤዋ እለት ስትደርስ (ይህች ከባድ ክስተቶች ያለባት እለት ነች) አንዳችሁ በእጁ ላይ አንዲት የተክል ዝንጣፊ ካለች ምጽዋት ትሆንለት ዘንድ ከቻለ እሷን በመተካት ላይ ይቻኮል፡፡›› (አሕመድ 12981) በማለት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በጭንቅና በአስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ቢሆንም እስልምና ምድርን ማልማትንና መገንባትን ከአምልኮታዊ ተልዕኮዎች መካከል ከማድረጉም በላይ የችግሩ ወይም የጭንቁ ሁኔታ እጅጉን የከፋ ቢሆንም ሰዎች ትኩረታቸውን ወደ ሌላ እንዳያደርጉ ያስተምራል፡፡



3. የተፈጥሮ ሐብትን መንከባከብ

እስልምና አካባቢ እንክብካቤ ሊደረግለት እንደሚገባና የተፈጥሮ ምንጮቹ መጥፋት፣ መመንመን፣ መበከል ወይም መበላሸት እንደሌለባቸው አረጋግጧል፡፡ (ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ) በሚል መርሕ ላይ የሚመረኮዝ የተሟላ እቅዶችን ለሰው ልጆች አዘጋጅቷል፡፡ ከነዚህ እቅዶች መካከል፡- ግለ-ንጽሕና መጠበቅና እንክብካቤ ሊደረግለት እንደሚገባ፣ ተፈጥሯዊ ምንጮች መጠበቅ እንዳለበቸውና አጠቃቀማቸውም ሚዛናዊ መሆን እንዳለበት፣ እነዚህን ተፈጥሯዊ ምንጮችን ማበላሸት ወይም መበከል በወንጀል እንደሚያስፈርጅ አረጋግጧል፡፡ ለአብነት ያህል፡-

- እስልምና የተፈጥሮ ሐብትን በመጠቀም ረገድ አባካኝነትን ከልክሏል፡፡ ሌላው ቀርቶ አምልኮታዊ ተግባር ለመፈጸም ዉዱእ (ከስግደት በፊት የተወሰኑ የሰውነት አካላት ማጠብ) ለማድረግም ቢሆን እንኳ ውሃን ማባከንን ፍጹም ክልክል አድርጓል፡፡

- እስልምና የጉልበት ባለቤቶችና ባለሥልጣናት የተፈጥሮ ሐብትን ደብቀው እንዳያከማቹና በዚህም ሌላውን ጉዳት ላይ እንዳይጥሉ በጥብቅ ከልክሏል፡፡ ውሃን (እንደተፈጥሯዊ ሐብት ምሳሌነቱ) እሳትን (እንደሃይል ሐብትነቱ) እንዲሁም የግጦሽ መሬትን (እንደ ምግብ ሐብትነቱ) በብቸኝነት የበላይ ሆኖ መቆጣጠርን፣መደበቅንና ከሌሎች መከልከልን በጥብቅ ከልክሏል፡፡ (አቡዳዉድ 3477)
- በዙሪያችን የሚገኘውን አካባቢን ማበላሸትን እስልምና ከልክሏል፡፡ ለምሳሌ በረጋ ውሃ ላይ መሽናትን ከልክሏል፡፡ ምክንያቱም ሽንቱ ውሃውን ይበክለዋልና፡፡ ሰዎች ለጥላነት፣ ለማረፊያነትና በጉዞ ላይ ለመተላለፊያነት ይፈልጓቸዋል፣ ይተላለፉባቸዋል በሚል እሳቤ በጥላነት በሚገለገሉባቸው ስፍራዎችና መተላለፊያ መንገዶች ላይ መጸዳደትን ከልክሏል፡፡

እነዚህ ቀለል ያሉ ምሳሌዎች መኖሪያ አካባቢን ከቆሻሻ ነገሮች ማጽዳትና ጎጂ የሆኑ ነገሮችን ከመንገድ ላይ ማስወገድ ጽድቅ ተግባር ሳይሆን የእምነት ማረጋገጫ እንደሆነ አድርጎ ከሚወስድ (ሙስሊም 35) ክቡር የሆነ መልእክተኛና ሃይማኖት በኩል መገኘታቸው የሚገርም ነገር አይደለም፡፡

> የኢስላም መልእክተኛ እንደሚናገሩት አካባቢን መንከባከብና ንጹሕናውን በመጠበቅ ላይ መሳተፍ የእምነት አካል ነው፡፡



## የእውቀት ሃይማኖት

በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ መጀመሪያ የወረደው ‹አንብብ› የሚለው ቃል እንደ አጋጣሚ የወረደ አይደለም፡፡ ታላቁ ቁርኣን ውስጥ የሰፈሩትንና በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አንደበት የተነገሩትን ለሰው ልጅ የሚጠቅሙ የእውቀት ዘርፎችን ለማጠናከር የወረደ ነው፡፡ እንደውም አንድ ሙስሊም እውቀትን ለመፈለግ የሚያደርገው ጉዞ ወደ ጀነት የሚያደርሰው መንገድ ነው፡፡ ይህንኑ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ በማለት ገልጸውታል፡፡ «እውቀትን ለመፈለግ ጉዞ ለጀመረ ሰው አላህ ወደ ጀነት የሚወስደውን መንገድ አግርቶለታል፡፡» (ሙስሊም 2699)

የእውቀትን ታላቅነት በሚደንቅ ሁኔታ አዛኙ መልዕክተኛ እንዲህ በማለት ገልጸውታል፡፡ «አንድ ምሁር ራሱን በአምልኮ ተግባር ላይ ካስተሳሰረ ሰው አንጻር ያለው ብልጫ ልክ በአዛኙ መልዕክተኛ ሙሐመድና በተራ ሰው መካከል እንዳለው ብልጫ ነው፡፡» (አት-ቲርሚዚይ 2685)

እስልምና በእውቀትና በሃይማኖት መካከል አለ የሚባልን ጦርነትና ተቃርኖ ሌሎች ሃይማኖቶች እንደሚያንጸባርቁት ፈጽሞ አያውቅም፡፡ በጨለማው ክፍለ-ዘመን ምሁራን እውቀታቸውንና አእምሯቸውን ተጠቅመው በሚያቀርቡት ትንታኔ ይፈረድባቸው የነበረ ሲሆን በተቃራኒው እስልምና እነዚህን ምሁራን አይፋረዳቸውም ነበር፡፡ እንደውም በተቃራኒው የእስልምና ሃይማኖት የእውቀት ነጸብራቅ፣ረዳትና ደጋፊ፣በመማር ማስተማር ወደርሱ ተጣሪ ነበር፡፡ በእስልምና ታሪክ መስጊዶች ለሰው ልጆች ጠቃሚዎች እስከሆኑ ድረስ ዘርፈ ብዙ እውቀቶች የሚቀሰምባቸው የእውቀት ማማዎች ነበሩ፡፡

በዚህ የተነሳ በዓለማችን ላይ በተፈጥሮ ሳይንስ ስማቸው ከገነነላቸው መካከል በርካቶቹ የሕይወታቸውን ጅማሬ ቁርአንን በመማር፣በቃል በማጥናት፣ሃይማኖታዊ እውቀቶችን በመከታተል አንደርድረው፤በመቀጠል የየራሳቸውን ዝንባሌ በመከተል በሙያቸው ብቁ ለመሆን የቻሉ ሙስሊሞች እንደ ነበሩ ስናውቅ ግር ሊለን አይገባም፡፡

በእርግጥ አላህ ለሰዎች መልካም ነገርን የሚያስተምርን ምሁር ክብር የላቀ አድርጓል፡፡ በላቀ ደረጃም አሸብርቆታል፡፡ ነቢዩ (የአላህ ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን) ለሰዎች መልካም ነገርን ለሚያስተምር ምድር ላይ የሚገኙ ፍጡራን ባጠቃላይ ይጸልዩለታል፡፡ ብለዋል (አት-ቲርሚዚይ 2685)

LAUNCHING
CURiOSiTY
CLICK HERE



> አብዛኛዎቹ ሙስሊም የስነ-ተፈጥሮ ምሑራንና ሙስሊም ሐኪሞች በሌሎች እውቀቶች ላይ ሰፊ ያለ እውቀት ይኖራቸው ዘንድ ጥሪ ያደረገላቸውን ቁርአንን በመማር ነው ሕይወታቸውን የጀመሩት።

## እውቅ ከሆኑ ሙስሊም ምሁራን መካከል



1. አል-ኸዋሪዝሚ (እ.ኤ.አ. 790-850 ባግዳድ)፡- የሒሳብ፣የምህንድስና እና የሥነ-ፈለክ ሊቅ እንዲሁም አልጀብራ የተሰኘውን የሒሳብ እውቀት ለመጀመሪያ ጊዜ ለዓለም ያስተዋወቀ ታላቅ ምሁርና ሊቅ ናቸው፡፡በርካታ መጽሐፎቻቸው ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል፡፡ መጽሐፍቱ በተተረጎሙበት ቋንቋዎች ውስጥ አልጀብር (Algebra) እና ዜሮ (Zero) የተሰኙት የዐረብኛ ቋንቋ ቃላት እንዲገቡ ምክንያት ሆነዋል፡፡



2. ኢብን አል-ሀይሠም (እ.ኤ.አ. 965-1040 ካይሮ)፡- ከአል-አዝሀር መስጊድ ጋር በተገናኘ የፊዚክስና የምህንድስና ሊቅ ነበሩ፡፡ በሥነ-በሲር (በብርሃንና ጨረር ምርምሮች) በርካታ አስተዋጽኦዎችን አበርክተዋል፡፡ የካሜራ ጥበብ ሕግጋት ባለቤትም እንደሆኑ ይነገራል፡፡ ከዐረብኛው ቋንቋ ‹ቁምራህ› የተሰኘ ቃል በስተቀር በርካታ ጠበብቶችና ምሁራን እንደሚሉት ካሜራ የተሰኘው ቃል በበርካታ የዓለማችን ቋንቋዎች ዘንድ እንደሚታወቅ ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን ‹ቁምራህ› የተሰኘው ቃል ምስጠራዊ ስያሜ ኢብንአል-ሀይሠም ለብርሃን የሰሯት የብርሃን ክፍል ስያሜ ነበር፡፡



3. አል-በይሩኒ / (973-1048 ኸዋሪዝም) ስመ-ጥር የስነ-ፈለክ ምሁር ሲሆን ምድር በራሷ ምሕዋር (ዛቢያ) ላይ እንደምትሽከረከርና የምድርን ስበት ለመጀመሪያ ጊዜ ያረጋገጠ ምሁር ነው፡፡





4. አዝ-ዘህራዊ (እ.ኤ.አ 936-1013 አንደሉሲያ /እስፔን/)፡ - ሙስሊም ሐኪምና የቀዶ ጥገና ስፔሻሊስት ነበሩ፡፡ የቀዶ ጥገና ሕክምና በእሳቸው በኩል እጅግ እንዲያድግ ከማድረጋቸው ጎን ለጎን በመቶዎች የሚቆጠሩ የቀዶ ጥገና ሕክምና ቁሳቁሶችን ቢሯቸው ውስጥ ለመፍጠር የቻሉ እንዲሁም እሳቸው ከነበሩበት ክፍለ-ዘመን በኋላ ለተተኩት ክፍለ-ዘመናት የሚጠቅሙ የቀዶ ጥገና ሕክምና መጽሐፍትን ያዘጋጁ፣እነዚህ መጽሐፎቻቸው በተለያዩ ቋንቋዎች የተተረጎሙላቸው ታላቅ ሊቅ ነበሩ፡፡



5- ኢብን ሲና (980-1037 ቡኻራ) በሳይንሳዊ ስሙ (አቬሴና) በመባል ይታወቃል፡፡ በዘመኑ የነበሩትን ሁሉ በመላቅ በርካታ የሕክምና ምርምራዊ ግኝቶችን ያገኘና ለበሽታዎች መድሐኒቶችን ያስቀመጠ የሕክምና ባለሙያና ፈላስፋ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር በሕክምና ጥናቱና ምርምሩ የስነ-ተሞክሮን ጥበብ ያላቀና ያጎላ በዚህም ጥልቅ የሆኑ ምርምሮችን ያካሄደ ይህ ምርምሩና ጥናቱ ለዘመናዊ የሕክምና ሳይንስ መሰረትን የጣለ ነው፡፡ ይህ ደግሞ (አልካኖን) በተሰኘውና ለሰባት ክፍለ-ዘመናት በቆየው የሕክምና ሳይንስ እድገት በቀደምትነት እንደመረጃ በሚያገለግለው መጽሐፉ ውስጥ በግልጽ ሰፍሯል፡፡ ይህ መጽሐፍ በአውሮፓ ዩኒቨርስቲዎች እስከ አስራ ሰባተኛው ክፍለ-ዘመን ድረስ በማስተማሪያነት አግልግሏል፡፡

በሕክምናው ዘርፍ ስመ-ጥር ከሆነ በኋላ ሰብአዊነቱ አስገድዶትና ይህን የላቀ የእውቀትና የጥበብ ጸጋን ያጎናጸፈውን አላህ ለማመስገን ሰዎችን በነጻ ያክም ነበር፡፡



6- ኢብን አን-ነፊስ (1213-1288 ደማስቆ) የኢስላማዊ ስነ-ሕግ ምሁር ነበር፡፡ በዚሁ ዘመን ስመ-ጥር ከነበሩ የሕክምና ጠበብትና በታሪክ የስነ-አካላት (ፊዚዮሎጂ) ጠጠብት መካከልም አንዱ ነበር፡፡ ኢብን አን-ነፊስ በዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ የደም ዝውውር ዑደትን ያገኘና ዑደቱንም ያብራራ የመጀመሪያው ሰው ነው፡፡ እስከ አሁን ድረስም በማጣቀሻነት የሚያገለግሉ በርካታ የቲዎሪ ሃሳቦችን አዘጋጅቷል፡፡



## እስልምና ሁሉንም የሰው ልጅን የሕይወት ዘርፎች ያጠቃልላል



ሰዎች ያለፉባቸው በርካታ ሃይማኖቶች እንደሚሉት ሳይሆን እስልምና ሃይማኖታዊ ስርኣት ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ስነ-ምግባራዊ መመሪያም ጭምር መሆኑን ሲያውቁ እጅጉን ይገረማሉ፡፡

በእውነቱ ከሆነ እስልምና፡- ሙሰሊሞች በመስጊዶች ውስጥ በስግደት፣ በጸሎት የሚፈጽሙት መንፈሳዊ ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ ተከታዮቹ ብቻ የሚያምኑበት ተራ የሆነ እምነት፣አስተሳሰብና ፍልስፍናም አይደለም፡፡ የምጣኔ ሀብት ወይም የተሟላ አካባቢ ብቻም አይደለም፡፡ አንድን ሕብረተሰብ ለመፍጠር የተቀመጠ ስርአት ወይም ሃሳባዊ እቅድ ብቻም አይደለም፡፡ እንዲሁም ስነ-ምግባርን ለማረቅ የተዘጋጁ የስነ-ምግባር ሕግጋት ስብስብ ብቻም አይደለም፡፡



ነገር ግን የሕይወት ዘርፎችን በአጠቃላይ የያዘ የተሟላ መመሪያ ነው፡፡ እንዲያውም ሁሉን አጽናፍ ያካተተና ሌላውንም ያጠቃለለ መመሪያ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን እስልምና የሰዎች ሕይወት በተቻለ መጠን ቀላል እንዲሆን ከማድረጉ በተጨማሪ የሰው ልጅን ነጻነት አይገድብም፡፡ ይህ ሁሉ የሰው ልጆች አእምሮ በሥልጣኔ እድገትና በፈጠራ ስራ ላይ ትኩረት ጥረት እንዲያደርግ ነው፡፡ ይህ ደግሞ አላህ ለሰዎች ከለገሳቸው ታላላቅ ፀጋዎች መካከል አንዱ ሲሆን ቁርኣን እንደሚያረጋግጠው አላህ በአገልጋዮቹ ላይ የሚመጻደቅባቸው ነገር ነው (5፡3)

አንድ ሙስሊም ያልሆነ ሰው -ሰልማን አል-ፋሪሲይ- የተባለልን በመልእክተኛው ባልደረባ ላይ ሙስሊሞች በማላገጥ፤ «ወዳጃችሁ (የአላህን መልእክተኛን ማለቱ ነው) የመጸዳዳትን ስነ-ስርአት እንኳ ሳይቀር ሁሉንም ነገር ያስተምራችኋልን? አለው፡፡ ይህ ታላቅ የነቢዩ ባልደረባም፤ «አዎን በእርግጥ አስተምሮናል፡፡» አለውና ይህን አስመልክቶ እስልምና ያስቀመጣቸውን ሕግጋትና ስነ-ስርአቶች ጠቀሰለት፡፡ (ሙስሊም 262)

> ኢስላም አጠቃላዩ የሕይወት ዘውጎችን የሚያጠቃልል መመሪያ ነው፡፡

## ምድራዊው ዓለምና መጻኢው ዓለም

ቀደምት ግብጻዊያን የአንድ የሞተ ሰውን በድን አካልን ከከፈኑ በኋላ ውድና ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ንብረቶቹን ከእሱ ጋር ይቀብሯቸው ነበር፡፡ ይህን የሚያደርጉት ሰውየው ከሞት በኋላ ባለው ዓለም ሕይወቱ ሊፈልጋቸው ይችላልና የሚል ጥርጣሬ ስለነበራቸው ነው፡፡

እንደዚሁ የቲቤት ሕዝቦች የሞተባቸውን ሰው በድን አካል በመቆራረጥ የአእዋፍ ምግብ ይሆን ዘንድ ከፍ ያለ ስፍራ ላይ ያስቀምጡ ነበር፡፡ ሒንዱዎች እስከ አሁን ድረስ የሞተባቸውን ሰው በድን አካል ያቃጥላሉ፡፡ ምክንያቱም ከመንፈሶቻቸው መገላገያ ብቸኛ መንገድ ይህ ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡

ይህ ሁሉ እንግዲህ ለዘመናት የተለያየው የሰው ልጅ ግነዛና ሽኝት ስርአቶች ምሳሌዎች ናቸው፡፡ በዘመናት የተፈራረቁ እምነቶችና ሃይማኖቶች ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት ያላቸው አመለካከት ይህን ይመስላል፡፡ነገር ግን ጥልቅ የሆኑ ማብራሪያዎችንና መልሶችን የሚሹ ጥያቄዎች አሉ፡፡ከእርሱም

ውስጥ እውን ከምድራዊ ሕይወት ሌላ ሕይወት አለን? ጠባዩስ ምንድን ነው? እዚያ የምንፈልገው ነገር ምንድን ነው?

በሌላኛው ዓለም አማኞች ሆንን ወይም የሥራችንን ዋጋ በስሜታችን፣ በአይናችን፣ በምንመለከተውና በምንዳስሰው ነገር ላይ የተገደበ ነው ብለን እንመን ወይም ለዚህ ፍጻሜያዊ ጉዞ ራሳችንን ያዘጋጀን ሆነን ወይም በዙሪያችን ያሉ በርካታ ቧልቶችና ጨዋታዎች ይህን እውነታ የዘነጉት ወይም የረሱት ቢሆኑም ሞት የላቀው እውነታና ሁላችንንም የሚጠብቅ በመሆኑ ላይ ሁሉም የሚስማሙበት ነጥብ ነው፡፡

በዚህ ላይ ሁላችንም ካለ ልዩነት የምንስማማ ከሆነ ዘውትር ዝንጉና ቸላ የሚሉ ሰዎች እንዲሁም ማንኛውም ሰው ላፍታ ብቻውን ስለዚህች ምድራዊ ሕይወት ሲያስብ አእምሮ ላይ በተደጋጋሚ የሚመላለስ ጥያቄ አለ፡፡ እሱም እውን ሞት የመጨረሻ ፍጻሜ ነውን? ከዚያ በኋላ ምንም ነገር የለምን? እውን በምድር ላይ የመኖራችን እውነታ ያፍታ ጨዋታ ነውን? የሚል ነው፡፡

በአእምሯችን በተደጋጋሚ የሚመላለሰውና ቁርአንም በተለያየ አገላለጽ የሚደጋግመው ጥያቄ ይህ ነው፡፡ በዚያው ወቅት ስለፀፀትና በርካታ ሰዎች በትንሳኤ እለት በዋይታ ውስጥ እንደሚሆኑ ይነግረናል፡፡ ምክንያቱም የሰው ልጆች አንድም ጊዜ ላፍታ ቆም ብለው ስለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ከራሳቸው ጋር ተነጋግረው አያውቁም፤ ለጉዞውም አልተዘጋጁም፡፡ በዚህ ጊዜ ከፊላቸው ምናለ ለሕይወቴ መልካም ነገር በስቀደምኩ ኖሮ (አል-ፈጅር፡ 24)፣ ሲሉ ከፊሎቹም፡ «ምናለ አፈር በሆንኩ ኖሮ» (አን-ነበእ ፡ 40) ይላሉ፡፡



እንደሚታወቀው ሁሉም ሰማያዊ ሃይማኖቶች በወዲያኛው ዓለም ሕይወት፣ በውስጡም ባለው ሽልማትና ቅጣት ያምናሉ፡፡ ምክንያቱም ይህ ሁሉም መልእክተኞች ይዘውት የመጡት መልእክት ነው፡፡ የሰው ልጅ አእምሮ ይሰሩት በነበረው ስራ በወዲያኛው ዓለም ከመተሳሰብና የሰው ልጅ በሰራው መልካምም ሆነ መጥፎ የሥራውን ዋጋ ከማግኘት ውጭ ሕይወት፣ ሃይማኖትና ስነ-ምግባር ምንም ዓይነት ፋይዳ እንደሌለው ያምናል፡፡

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ብዙ ሰዎች ሃይማኖትና አምልኮታዊ ተግባራት ገንዘብ ከማግኘት፣ከመደሰት፣ከመበልጸግ ጋር ፍጹም መገናኘት የለበትም፣ሥራ ከተባለ ለምድራዊ ወይም ለወዲያኛው ዓለም ብቻ ተብሎ መሰራት አለበት እንጂ ልክ ቀንና ማታ በአንድ ቀን ውስጥ በአንድ ላይ እንዳሉ ሁሉ የሁለቱም ሥራዎች በአንድነት መፈጸም የለባቸውም፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ወይ ከዚህ ወይ ከዚያ መወሰን ይኖርበታል ብለው ያስባሉ፡፡

> ሁሉም ሰማያዊ ሃይማኖቶች በወዲያኛው ዓለም፣ እዚያ ባለው ምንዳ (ሽልማት) እና ቅጣት ያምናሉ፡፡

የእንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ግርምት ፍጻሜ የለውም፡፡ እንደውም ራስን በማስደሰት፣ በአምልኮታዊ ተግባራትና በገንዘብ መካከል ያለው ክፍፍልና ልዩነት በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ እንደሌለ ሲነገራቸው ለማመን ይከብዳቸዋል፡፡ የተከበሩት መልዕክተኛ ሙሐመድ ማንኛውም ሰው በማንኛውም የሥራ መስክ ይሥራ መልካም ለመስራት ብሎ እስከተነሳሳና ሥራውንም እስከተገበረው ድረስ በወዲያኛው ዓለም ምንዳ እንደሚያገኝበት ነግረውናል፡፡ለዚህም ምሳሌ ሲያስቀምጡ አንድ ሰው መንገድ ላይ ወድቃ ያገኛትን እሾህ ሰዎችን እንዳትጎዳ ብሎ ከመንገዱ ላይ ቢያስወግዳት ወይም አንድ ሰው ለሚስቱ በሚያጎርሳት ጉርሻ እንኳ ምንዳ ይጻፍለታል፡፡ (ቡኻሪ 56)

የተከበሩት መልዕክተኛ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የመልካም ሥራ መንገዶች በርካታ እንደሆኑና ተቆጥረው እንደማይዘለቁ ሲናገሩ በወቅቱ ከእሳቸው ጋር የነበሩ ባልደረቦቻቸው በጣም የተገረሙበትና ግርምታቸውን እንደጠየቁ ተዘግቧል፡፡ ይኸውም የተከበሩት መልዕክተኛ፣ ‹‹ከእናንተ መካከል አንዱ ከሚስቱ ጋር ስሜቱን በማርካቱ ምንዳ ያጸፍለታል› ብለው ሲሉ ባልደረቦቻቸው፣ ‹ስሜትን ማርካትና ምንዳ መጻፍን ምን አገናኛቸው?› ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ የተከበሩት መልዕክተኛም፣ ‹ሰው የውስጥ ስሜቱን ፍጹም ክልክል በሆነ ነገር ላይ ቢያረካ በእሱ ላይ ሐጢአት አይያዝበትምን?› አሉ፡፡ ባልደረቦቻቸውም፣ ‹አዎ› አሏቸው፡፡እሳቸውም፣ ‹ስለዚህ ሰውየው ትክክለኛውን መንገድ በመምረጡ ምንዳ ይጻፍለታል፡፡› (ሙስሊም 1006)

ስለሆነም ከእስልምናን ጋር የሚተዋወቅ ከመጀመሪያው ጀምሮ ቁርኣን እንዳስቀመጠው በምድራዊውና በወዲያኛው ዓለም ሕይወት መካከል የሚዛናዊነትን መኖር ያስተውላል፡፡ ሰዎች አምልኮታዊ ተግባራትን በመፈጸም የላቀ ሽልማትን እንዲቀዳጁ ለማድረግ ሲያነሳሳ በምድራዊው ዓለም የአላህን ችሮታ ለማግኘት ጥረት መደረግ እንዳለበት ያረጋግጣል (አል-ጁሙዐህ ፡ 9-10)፡፡ የሰው ልጅም አላህ በማሰብ ይህን በመፈጸሙ ለፈጣሪያዊ ምንዳና ሽልማት የተገባ ነው፡፡ አንድ ሙስሊም በሥራው፣ ሲሳዩን በመፈለግ፣ ልጆቹን በመንከባከብና በማሳደግ፣ ጤንነቱንና አካባቢውን በመጠበቅ እንዲሁም ማሕበረሰቡን በማበልጸግ ጥረት እንያደረገ ልክ አላህን በስግደቱ፣ በምጽዋቱና በጾሙ እንደሚያመልከው በእነዚህ ተግባራትም አላህን እንዲያመልክ ታዟል፡፡

አንድ ሙሰሊም የምድራዊ ዓለም ሕይወቱና የወዲያኛው ዓለም ሕይወቱ፣አምልኮቱና ደስታው ሳይነጣጠሉ አንድ ላይ መሆናቸው ውስጣዊ የሕሊናና የመንፈስ መረጋጋት ሊያገኙባቸው ከሚችልባቸው ምስጢራዊ ዘዴዎች መካከል አንደኛው ዘዴ ይህ ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች አንዳቸው ሌላኛውን ደግፈው አብረው የሚያድጉ፣ፍጹም የማይነጣጠሉና ምሉእ የሆኑ ነገሮች ናቸው፡፡

ከዚህ በመነሳት የእስልምናን ፍልስፍና ባጠቃለለ ሁኔታ የማንኛውም ሙስሊም መርሕ ቃል፡- «ስግደቴ ብቻ ሳይሆን ሕይወቴ ባጠቃላይ በሁሉም ሁኔታዎቹ ለአላህ አምልኮ ነው፡፡ ምንዳዬንም አላህ ዘንድ እተሳሰባለሁ፡፡ እርሱም ከሞትኩ በኋላ በፈጸምኩት ተግባር ይፈርድብኛል፣ዋጋዬንም ይሰጠኛል፡፡ ስለዚህ የአላህ ትእዛዝና ሃይማኖቱ የሆነውን እስልምናን የተቆራኘሁ እሆናለሁ፡፡»

(አል-አንዓም ፡ 162) የሚል እንዲሆንና ይፋዊ እንዲያደርገው አዟል፡፡





## የግንኙነትና የመተባባር ሃይማኖት

ሙስሊም ተጓዥ የሆነው አሕመድ ኢብን ፉድላን ስለ ሩስያ፣ ዴንማርክና ስለ እስካንዲኒቪያ ሐገሮች በጉዞ ማስታወሻ ውስጥ በስፋት ዘግቧል፡፡ ይህ ተጓዥ የሰዎቹን አኗኗርና የማሕበረሰቡን ጠባይ ለዓለም በማስተዋወቅ የመጀመሪያው ሰው ነው፡፡

አሕመድ ኢብን ፉድላን ጉዟቸውን እ.ኤ.አ በ921 በሚገርም ሁኔታ ጀመሩ፡፡ ይህ ጉዞ በመካከለኛው ክፍለ-ዘመን ከተከናወኑት በርካታ የሥልጣኔ ግንኙነት ዋና ዋና ጉዞዎች መካከል አንዱ ነበር፡፡ ጉዞው የተጀመረው በወቅቱ የሳይንስና የሥልጣኔ ከተማ ከነበረችው ባግዳድ ሲሆን በጉዞው በርካታ ቁጥር ባላቸው ሕዝቦች መካከል አልፈዋል፡፡ በጉዟቸው የተመለከቱትንና የታዘቡትን ሁሉ በጥንቃቄ በማስታወሻቸው ላይ አስፍረዋል፡፡ ይህ ማስታወሻቸው ሩሲያ ውስጥ በመገኘቱ እ.ኤ.አ በ1923 በመጽሐፍ መልክ ታትሟል፡፡

አሜሪካዊው ምሁር ሚካኤል ክሪክቶን የኢብን ፉድላንን አጻጻፍ አስፈላጊነት አስመልክቶ እንደተናገረው ባግዳድ ውስጥ የነበሩት ሙሰሊሞች ሃይማኖታቸውን አጥብቀው ከመያዛቸው የተነሳ ከእነርሱ በገጽታና በእምነት ከሚለዩ ሕዝቦች ጋር በቀላሉ የሚዋሃዱና የሚቀራረቡ ነበሩ፡፡ሙስሊሞች በወቅቱ በክልል ደረጃ አነስተኛ ሕዝቦች ነበሩ፡፡ ይህ ደግሞ ለባይተዋር ሕዝቦች የበይ ተመልካች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ Michael Crichton (Eaters of the Dead).



እስልምና ሰዎች እርስ በርሳቸው ሥልጣኔን በማጎልበትና በማልመት ረገድ እንዲተባበሩ፣ምንም እንኳ በመካከላቸው የባሕል፣የብሔርና የሃይማኖት ልዩነት ቢኖርም የርስበርስ ግንኙነት እንዲያደርጉና እሱንም በላቀ ስነ-ምግባር እንዲያጠናክሩ ዘውትር ለሰዎች ጥሪ ያቀርባል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ከሰው መገለልና ብቸኝነት ከትክክለኛው እስላማዊ ፈለግ ውስጥ እንደሌለ በጥብቅ ያስጠነቅቃል፡፡ለዚህም ነው የአላህ መልዕክተኛ የሆኑት ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እለታዊ ግንኙነት ያደርጉ የነበሩት፡፡ ያደርሱባቸው የነበረውን ችግሮችና ጥፋቶች ችለው ያሳልፉ የነበሩትና ከሰዎች ከመገለል ይልቅ ይህንን የመረጡት፡፡ (ኢብን ማጀህ፡ 4032)፡፡

# አንድ ፈጣሪ . . .
# አንድ ተመላኪ

# እስልምና

እስልምና ሃሳባዊ እምነት ብቻውን ወደእምነት ለመግባት በቂ እንዳልሆነ ያረጋግጣል፡፡ ፈጣሪ የሆነው ጌታ አንድ ከሆነ አምላክና አምልኮ የሚፈጸምለትም አንድ መሆኑ ግድ ይላል፡፡



በዐረብኛ ቋንቋ ‹አላህ› የሚለው ቃል ሶስት ትርጉሞችን በአንድነት አጠቃሎ ይዟል፡፡ይኸውም፡፡

- አላህ ማለት ሰዎች በስግደታቸው፣በፆማቸው፣ በልቦናቸውና በአምልኮታዊ ተግባሮቻቸው ፊታቸውን ወደርሱ የሚያዞሩለትና በቅንነት የሚታዘዙት የሆነ ተመላኪ ነው፣
- ያ በይዘቱና በመገለጫ ባህሪያቱ ፍጹም እጅግ በጣም የላቀ፣የሰው ልጅ አእምሮ መገለጫውን ይህ ነው ብሎ ሊዘልቀው የማይችልና በዙሪያቸው ካሉ ነገሮች ጋር ፈጽሞ ሊያመሳስሉት የማይችሉት፣
- የሰው ልጆች ልቦናዎች የሚንጠላጠሉበት፣ የሚናፍቁት፣ እርሱን በማስታወሳቸው እጅጉን የሚረኩበት፣እርሱን በማምለካቸው ወደርሱ በመቅረባቸው ወደር የሌለው ደስታን የሚጎናጸፉበት የሆነ ማለት ነው፡፡

ቁርአን ማንኛውም ሰው ስለ (አላህ) ያለው እይታ እንዲስተካከል፣ክብሩንና ልዕልናውን ዝቅ ከሚያደርጉና ከሚያጎድፉ ነገሮችና አነጋገሮች ማጥራት እንደሚገባ ያስገነዝባል፡፡

ቁርአን እንደሚያብራራው አላህ የዚህ ፍጥረተ-ዓለም ፈጣሪና ስርአቱንም አስተናባሪ ነው፡፡ ምንም ያህል ይዘቱ ቢያንስ ማንኛውም ነገር በፍላጎቱ፣ በችሮታውና በእውቀቱ የፈጠረው እርሱ ነው፡፡ ከእርሱ እውቅና ውጭ በምድር ላይ ያለች የማንኛዋም ዓይነት ፍጡር እንስት ፈጽሞ አትጸንስም፣ አትወልድምም፣አንዲት ጠብታ ዝናብ አትዘንብም፣ በይፋም ይሁን በድብቅ ምንም ዓይነት ቀንና በሌሊት መፈራረቅ በየትኛውም የፍጥረተ-ዓለሙ ክልል አይከሰትም ምክንያቱም አላህ በእውቀቱ፣ በችሮታውና በእዝነቱ ሁሉንም አካቦታልና ነው (ፉሲለት ፡ 47)፣ (አል-አንዓም ፡59)

ጥራት የተገባው አላህ ከመገለጫዎች ሁሉ እጅጉን ያማሩ፣የተዋቡና ምሉእ የሆኑ መገለጫዎች አሉት፡፡ አላህ ፍጹም የማይሸነፍ ብርቱ፣ርሕራሔው ሁሉን ነገሮች ያካበበ እጅግ አዛኝ፣በማንኛውም ሁኔታ ክብሩ የማይጎድል እጅጉን የላቀ ፈጣሪ ነው፡፡

> በእስልምና ብርቱና ግልጽ የሆነው አምልኮ ተግባርን ለአላህ በብቸኝነት መፈጸም ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቁርአን እንደሚያረጋግጠው የሁሉም መልእክተኞች ጥሪ ነው፡፡

አንዳንድ ሰዎች አላህ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አረፈ ብለው ሲናገሩ ቁርኣን ደግሞ ይህን መሰሉን አሉባልታ ግልጽ በሆነ ቋንቋ እንዲህ በማለት አስተባብሏል፡፡ ‹‹ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ በስድስት ቀናት ውስጥ በእርግጥ ፈጠርን፤ድካምም ምንም አልነካንም፡፡›› (50፡38) ይህ መሰሉ አሉባልታና መሰል አነጋገሮች አላህን ከፍጡራን ጋር ፍጹም እንዲመሳሰል በአእምሮ የተፈበረኩ እንጂ ሌላ አይደሉም፡፡ ነገር ግን አላህ ከእንዲህ ዓይነቱ መመሳሰል የጠራና ከፍጡራኑ መካከል በባህሪና በመሳሰሉት አንድም እርሱን የሚመስል የለም፡፡ የሚገርመው እርሱ ፈጣሪ ሆኖ እያለ ከፍጡራኑ ጋር ይመሳሰላል መባሉ ነው፡፡ እውነቱ፣ ‹‹የሚመስለው ምንም ነገር የለም፤እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው፡፡›› (42፡11)

ጥራት የተገባው ፈጣሪ ቅንጣት ታህል የማይበድል ፍትሐዊ ዳኛ ነው፡፡

በሕይወታችንና በዙሪያችን የምንመለከታቸው ገሃዳዊ ነገሮች ሁሉ የእርሱን ጥበብና ችሮታ የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ አንድ ሕጻን ልጅ በሕጻንነቱ ከወላጆቹ እንቅስቃሴዎች መካከል የሚያውቀው የተወሰኑትን ብቻ እንደሆነ ሁሉ የሰው ልጅ አእምሮም ስለአላህ ጥበባት የሚያውቀው ጥቂት ነው፡፡ ይህ ማለት ከአእምሮው እይታ በላይ የሆኑ በርካታ የአላህ ፈጣሪያዊ ጥበቦች አሉ ማለት ነው፡፡

እስልምና ገሃዳዊ ምልክቶችን በመመልከት ብቻ እምነት ውስጥ ለመግባት በቂ እንዳልሆነ ያስተምራል፡፡ፈጣሪ አንድ ብቻ ከሆነ አንድ አምላክና አንድ ተመላኪ ብቻ ሊኖር ግድ ነው፡፡ይህ ማለት የፈጣሪ አንድነት ከታወቀ ከእርሱ ውጭ ላሉ ነገሮች አምልኮትን መፈጸምና መጸለይ አይገባም ማለት ነው፡፡ አምልኮ ካለምንም አማላጅነትና ጣልቃ ገብነት በቅንነት መፈጸም የሚገባው ጥራት ለተገባው አንድ አላህ

ብቻ ነው፡፡ምክንያቱም ፈጣሪ ከሁሉም ነገሮች በእጅጉ የላቀና የተከበረ ነው፡፡

አንድ ንጉሥ ወይም የሀገር መሪ የመራቸውንና የሚያስተዳድራቸውን ሰዎች ሁኔታና ችግር በረዳቶቹ በኩል ብቻ ካልሆነ በቀር ለማወቅ አይችልም፡፡ አላህ ግን ግልጹንና ድብቁን ነገር ጠንቅቆ የሚያውቅ፣የሁሉም ነገሮች ባለቤትና ሁሉንም ነገር ቻይ፣ሁሉም ነገሮች በርሱ ቁጥጥርና እንቅስቃሴ ውስጥ የሆኑ በመሆኑ አንድነገር ለመፈጸም ሲፈልግ ‹ሁን› ብቻ ይለዋል ይሆናልም፡፡ አላህ ይህ ሆኖ ሳለ ከአላህ ሌላ ወዳለ ነገር ማዘንበሉና መሄዱ ለምን አስፈለገ?

ማንኛውም ሙስሊም ጉዳዮቹን ሁሉ ፊት ለፊቱ ጥሎ ወደጌታው ዘንድ እስካልተጠጋ ድረስ ልባዊ መረጋጋትንና ልበ-ሰፊነትን መቀዳጀትና ምሉእ መሆን እንደማይችል ቁርአን ያረጋግጣል፡፡ ምክንያቱም ቻዩ፣ አጅግ የላቀው፣ ባሪያዎቹን ወደጁ፣ ቸሩና ወደነርሱ በጣም የቀረበው፣ በባሪያዎቹ ጸሎት ተደሳቹ እርሱ በመሆኑ ነው፡፡ ያከራቸዋል፣ ወደርሱ እንዳቀራረባቸው መጠን ምንዳን ይሰጣቸዋል (አል-በቀራህ ፡ 28)፣ (አን-ነምል ፡ 62-63)

ከዚህ በመነሳት በእስልምና በግልጽ የተብራራውና የተቀመጠው አብይ ጉዳይ የሁሉም መልዕክተኞች ጥሪ ነው፡፡ ቁርኣን አምልኮታዊ ተግባራት በቅንነት መፈጸም ያለባቸው ከአላህ ሌላ ላሉ ነገሮች ሳይሆን ለአላህ ብቻ እንደሆነ ያረጋግጣል (16፡36)፡፡ ማንኛውም መልዕክተኛ ወይም ንጉሥ ወይም መልካም ሰው ምንም መልካምነቱ ግልጽና የተጋነነ ቢሆንም እርሱ አላህን ከባሪያዎቹ ጋር ማገናኛ ድልድይ ነው ብሎ በማሰብ በጸሎት እርሱን መማጸንና መማለድ ፈጽሞ አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ከላይ የተጠቀሱት በሙሉ በአላህ የተፈጠሩ ፍጡራን ናቸው፡፡ አላህ ደግሞ ለባሪያዎቹ እጅግ ቅርብና ንግግራቸውን የሚሰማ፣አምልኮቶችን በቅንነት ለእርሱ እስከፈጸሙ ድረስ ለጸሎታቸው ምላሽ የሚሰጥ ጌታ ነው፡፡

በቅንነት ወደአላህ ራሱን ያዞረ ሰው እንዴት ነው የላቀ ደስታና ፍሰሐ የማያገኘው ይህ ሰው ልቦናው አይበታተንም እንዲሁም አያወላውልም፡፡ ብቸኛው የሁሉም ባለቤት፣ ብቸኛው ፈጣሪ፣ ብቸኛው ተመላኪ በእርግጥ እርሱ ነው፡፡ ፊትን ማዞርና መጠጋት እጅግ ወደላቀውና ለእሱ ተገቢ ካልሆኑ ነገሮች ወደጠራው አላህ እንጂ ከእሱ ውጭ ወዳሉ ነገሮች አይደለም፡፡

ይህ መልዕክት በቁርኣን ውስጥ ካሉት ታላላቅ ምዕራፎች መካከል የአል-ኢኽላስ ምዕራፍ በሚል ስያሜ የምትታወቀው አጭር ምዕራፍ አጠቃላይ ትርጉም ነው፡፡





LAUNCHING
CURiOSiTY
CLICK HERE

ሁሉም ነገር የሚከሰተው በአላህ እውቀትና ውሳኔ እንደሆ ቁርአን ያረጋግጣል፡፡ የዝናብ ጠብታዎችም ሆኑ የዛፍ ቅጠሎች መርገፍ የአላህ እውቅና እና ውሳኔ ናቸው፡፡

## የአል-ኢኽላስ ምዕራፍ

አላህ ማን ነው? የሚል ጥያቄ ለሚያነሱ ሁሉ አጥጋቢ ምላሽ ይሆን ዘንድ የአላህ መልዕክተኛው ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን ምዕራፍ በተብራራ ሁኔታ ግልጽ ያደርጉ ዘንድ አዟቸዋል፡፡

- አላህ በአምልኮት ላይ አጋር የሌለው ብቸኛ ጌታ ነው፡፡
- አላህ ሁሉም ፍጥረታት ጉዳያቸው ይፈጸምላቸው ዘንድ ወደርሱ የሚጠጉበትና በርሱ ላይ የሚመኩበት ነው፡፡
- አላህ ልጅ አለው፣ተወልዷል ከሚለው አነጋገር በእጅጉ የጠራ ጌታ ነው፡፡ አላህ ቀድሞውንም የነበረ ከርሱ በፊትም ማንም የሌለ የሆነ ጌታ ነው፡፡
- አላህ በባህሪዎቹም ሆነ በመገለጫዎቹ የሚመሳሰለው አምሳያ የለውም፡፡ እርሱ ፈጣሪ ሲሆን ከርሱ ሌላ ያሉት ሁሉ ተፈጣሪዎች ናቸው፡፡



## በተፈጥሮና በሸሪዐ ሕግ መካከል

ይህን የምንኖርበትን ፍጥረተ-ዓለም አላህ በሰውነታችን ውስጥ ከምትገኝ ከእሷ ይበልጥ በጣም ያነሰ የሆነ ነገር ከማይገኝ ከአንዲት ትንሽ ነገር በጥንቃቄና በሚደንቅ ስርኣት ለፍጡራን በሚመች ሁኔታ ፈጥሯል፡፡የተፈጥሮ ሳይንስ ሊቃውንት በፍጥረተ-ዓለሙ አፈጣጠር ላይ አንዳች መዛነፍ ወይም ክፍተት ቢኖር ኖሮ ውጤቱ ይህ ነው የማይባል ከፍተኛ እልቂትና ብልሽት ያስከትል እንደነበር አረጋግጠዋል፡፡

ማንኛውም ሙስሊም ይህን ረቂቅ የሆነ የፍጥረተ-ዓለም ስርኣት ያስገኘውና የፈጠረው እንዲሁም ያስተናበረ ፈጣሪ ለፍጡራኑ የሚበጁ ሕግጋትን በአርግጥ ያውቃል፣ የደነገገው ሃይማኖትም ለሰው ልጅ ሕይወት እጅግ ጠቃሚ የሆነና ከሌላ ወገን የጭካኔ ተግባር ነጻ የሚያወጣ የሆነ እንደሆ ያምናል፡፡ የፍጥረተ-ዓለሙና ሰው ልጅን መፈጠር ዓላማ አላህ በቁርአን ላይ ሲያብራራ የሚጠቅሟቸውን ነገሮች በጥልቅ ዐዋቂ እንደሆነ ተናግሯል፤ (የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀት ረቂቁ፣ ውስጥ ዐዋቂው ሲኾን ((ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን?)) (አል-ሙልክ ፡ 14)



LAUNCHING
CURiOSiTY
CLICK HERE



## በእስልምና ቅስና የለም

በርካታ ሃይማኖቶች ለተወሰኑ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች የተለየ መገለጫዎችንና ቦታዎችን እንደሰጡና የሌሎች ሰዎችን እምነትና አምልኮ ከእነርሱ ፈቃድና ፍላጎት ጋር በእጅጉ እንዳስተሳሰሩ እናገኛለን፡፡ -በእነዚህ ሃይማኖቶች አስተያየት- እነዚህ ሰዎች በሰዎችና በአምላክ መካከል መገናኛ ድልድይ እንደሆኑ፣እነርሱም ምህረትን እንደሚሰጡ፣ምናልባትም የሩቁን ስውር ነገር እንደሚያውቁና እነርሱን የሚቃረንና የማይታዘዝ ግልጽ የሆነ ክስረት ውስጥ እንደሚወድቅ ይታመናል፡፡

ነገር ግን እስልምና ውስጥ የሃይማኖት ሰው የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ልዩ ተግባራትን የሚያከናውን ሰው ፍጹም የለም፡፡አላህ የሰው ልጅን አክብሮ ፈጥሮታል፡፡ከፍጡራን መካከልም ደረጃውን አልቆታል፡፡በእርሱና በፈጣሪው አላህ መካከል ከሰዎች ጋር የተያያዘ መንፈሳዊ ግንኙነት እንዳይኖር እስልምና የሰው ልጅን ከምንም ነገር ነጻ አውጥቶታል፡፡ በሚሰሩት የጽድቅ ተግባር በፈጣሪ ዘንድ ከሌሎች ሰዎች በተለየ ከፍ ያለ ስፍራ ተሰጥቷቸዋል ከሚባሉ ሰዎች ጋር ማንኛውም ሰው የሚፈጽመው ንሰሃ፣አምልኮታዊ ተግባራት ተቀባይነትና የሚያገኘው ደስታ ምንጭ ፈጽሞ እንዳይያዝ ይህን መሰሉን የግንኙነት መስመር ውድቅ አድርጓል፡፡

እንዲሁም እስልምና የሰው ልጅን ሃይማኖታዊ እውቀት በተወሰኑ ሰዎች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው ከሚል ማነቆ ነጻ አውጥቶታል፡፡ ቁርኣን ሃይማኖታዊ እውቀትና ቁርኣንን በአግባቡ መረዳት የተወሰኑ ሰዎች መብት አድርጎ አላስቀመጠም፡፡ እንዲያውም ቁርኣን ሃይማኖታዊ እውቀትን መፈለግና ቁርኣንን በአግባቡ መረዳት የሁሉም ሰው መብት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ሰው ግዴታ እንደሆነ ነው ያስቀመጠው፡፡ ሰዎች በአጠቃላይ ቁርአንን እንዲማሩ፣እንዲያጠኑ፣እንዲያውቁ፣ትርጉሙንና መልዕክቱን በወጉ እንዲረዱና በተግባር እንዲተረጉሙ ያዛል፡፡ (ሷድ ፡ 29)

> እስልምና የሰውን ልጅ አክበሮታል፡፡ ደረጃውንም አልቋል፡፡ በእሱና በአላህ መካከል ድልድይ ከሚሆን ማንኛውም መንሳዊ ስልጣን ነጻ አውጥቶታል፡፡ የሰው ልጅ ደስታ ወይም ንሰሐ ወይም አምልኮ ምንም የችሮታና የመልካምነት ደረጃ ላይ ከደረሱ ከተወሰኑ ሰዎች ጋር ማስተሳሰርን ውድቅ አድርጓል፡፡

አምልኮና አምነት በሰው ልጅና በፈጣሪ መካከል የሚኖር ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በዚህ ውስጥ ችሮታ ሊኖረው ወይም አዋሳኝ ድልድይ ሊሆን አይችልም፡፡ ተገቢ ካልሆኑ ነገሮች የጠራው አላህ ወደባሪያዎቹ በእጅጉ የቀረበ ነው፡፡ የማንኛውንም ባሪያ ጸሎት ይሰማል፣ አምልኮታዊ ተግባራቶቹን፣ ስግደቱን ይመለከታል በእርሱም ሽልማትን ይሰጠዋል፡፡ ማንኛውም የሰው ልጅ የሰው ልጅን ሃጢአት የማሰረይና ንስሐን የመቀበል መብት የለውም፡፡ አንድ ሰው በሠራው ሃጢአት ከተፀፀተ፣ ወደአላህም በቅንነት በፀፀት ከተመለሰ አላህ ንስሐውን ይቀበለዋል፣ ሃጢአቱን ይሰርይለታል፡፡ አላህ ለሚለምኑት፣ ለሚቀርቡትና ፊታቸውን ወደርሱ ለሚያዞሩት ይበልጥ ቅርብ ነው፡፡ አላህ በቁርአን ላይ እንዲህ ብሏል፤ ((ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው)፡- እኔ ቅርብ ነኝ፡፡ የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ፡፡ ስለዚህ ለኔ ይታዘዙ፤ በኔም ይመኑ፤ እነሱ ሊመሩ ይከጀላልና፡፡)) (አል-በቀራህ ፡ 186)





> ሰዎች ወደእሱ ፊታቸውን አዙረው እስከጠየቁ ድረስ አላህ ለሁሉም በጣም ቅርብ እንደሆነ ቁርአን ያረጋግጣል፡፡

## ወደ እስልምና ለመግባት የተለዩ ሃይማኖታዊ ሥርኣቶች አሉን?

አምኖበትና ተቀብሎት ወደ እስልምና ለመግባት ለፈለገ ሰው እስልምና ውስጥ ውስብስብ የሆኑ ሃይማኖታዊ ስርኣቶች የሉም፡፡ እንዲሁም ወደ እስልምና ለመግባት ልዩ ናቸው የተባሉ ሰዎች በሚሰባሰቡበት ቦታ ላይ መገኘት እንዲሁም ወደ ተለየ ስፍራ መሄድ ግድ አይልም፡፡ እስልምናን መቀበል የሚፈልግ ከርሱ የሚጠበቅበት ነገር የሁለቱን ምስክርነት (ሸሃደተይን) ቃላ ትርጓሜ፣ዓላማና ግብ ብቻ በደንብ አውቆ የምስክርነት ቃላቱን መናገር ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት የምስክርነት ቃላት የሚከተሉት ናቸው፡፡

አሽሀዱ አንላኢላሀ ኢልለላህ (በእርግጥ ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እርሱንም በብቸኝነት አመልካለሁ)፡፡

ወአሽሀዱ አንነ ሙሐመደንረሱሉላህ (መሐመድ ደግሞ ለሰው ልጆች በአጠቃላይ ከአላህ የተላኩ መልዕክተኛ ናቸው ብዬ እመሰክራለሁ፡፡ ለትእዛዞቻቸው ቅን ታዛዥ እሆናለሁ፡፡ ከከለከሏቸው ነገሮች እርቃለሁ፡፡ በእሳቸው ፈለግ፣ሕግና ሥርኣት መስረት አላህን አመልካለሁ)



# በእውነት መልዕክተኞች እነማን ናቸው?



# አላህ

አላህ ሰዎችን ያመለኩት ዘንድ ፈጥሯቸዋል፡፡ የርሱን ድንጋጌዎችንም ያስተምሯቸው፣ በሃይማኖቱ ላይም ያስታውሷቸው፣ በሰዎች መካከል እርቅን ያሰፍኑ፣ ለሕዝባቸው መልካም ተምሳሌት እንዲሆኑ፣ ጋጠ ወጥነትን እንዲቃወሙ፣ ሰዎችንም ወደቅን መንገድ ይጣሩ ዘንድና በእርሱ ማመን ላይ ሰዎች መከራከሪያ እንዳይኖራቸው መልእክተኞችን ልኮላቸዋል፡፡ ታዲያ የመልእክተኞች እውነታ ምንድን ነው?



## የመልዕክተኞች ሰብአዊነት

ቁርአን በበርካታ አንቀጾች ላይ መልእክተኞች ባጠቃላይ ሰብአዊና አላህ ለየት አድርጎ ለመኮታዊ ርእይና ለመልእክተኛነት የመረጣቸው ፍጡሮች እንደሆኑ ያረጋግጣል፡፡ በእኛና በነቢያት መካከል ተመሳሳይነት ቢኖርም በያዙት አቋም ላይ ቀጥ በማለታቸውና በልቦናቸው ጽዳት ከእኛ በደረጃ በእጅጉ የላቁ ናቸው፡፡ በዚህም ሳቢያ መልእክቱን ለሰዎች ያደርሱ ዘንድ አላህ መርጧቸዋል፡፡ ((በላቸው! «እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት ወደኔ የሚወረድልኝ ቢጤያችሁ ሰው ብቻ ነኝ፡፡»)) (አል-ከህፍ ፡ 110)

መልዕክተኞች በሙሉ ሰዎች ናቸው፡፡የሰው ልጆች እንደሚወለዱ እነርሱም ይወለዳሉ፣እንደሚሞቱት ሁሉ እነርሱም ይሞታሉ፣ፍላጎት እንዳላቸው ሁሉ እነርሱም ፍላጎት አላቸው፡፡ በሰውነት አፈጣጠራቸውም ሆነ በመሰረታዊ ፍላጎቶቻቸው ከሰው ልጆች ጋር ፈጽሞ አይለያዩም፡፡

ከመልኮታዊነት አንዳቸም ነገር በውስጣቸው የለም፡፡ ምክንያቱም መለኮታዊነት ለአላህ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን እነሱ መለኮታዊ ርእይ የሚወርድላቸው ሰው ናቸው፡፡ ይህ ማለት የአላህ ትእዛዝ በመልአክ በኩል ወይም በሌላ መንገድ ይደርሳቸዋል ማለት ነው፡፡

የመጀመሪያዎቹ ሕዝቦች በርዕይ ላይ ተገርመው የነበረ ሲሆን አላህ ይህ አግራሞታቸው ምንም አሳማኝ ነገር የሌለው አግራሞት እንደሆነ በመንገር ነቅፏቸዋል፡፡ ምክንያቱም መለኮታዊ ርዕይ የአላህን ወደቀጥተኛ መንገድ ፍጡራኖቹን የመምራት መመሪያና ሃይማኖቱን የማስተማሪያ ብቸኛ ድልድይ በመሆኑ ነው፡፡ (10፡2)

## ሚዛናዊነት በመልዕክተኞች ዘንድ

አላህ ከፍጡራኑ መካከል መልእክቱን ይሸከም ዘንድ መልካሞቹን መርጧቸዋል፡፡ በቀጥተኛውና ትክክለኛው የላቀ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች ናቸው፡፡ ቁርአን መልእክተኞች ቅኑን መንገድ የተመሩ፣ መልካም የሆኑ፣ ጥሩዎች፣ ምርጦችና ከዓለማት በላጮች መሆናቸውን ገልጿል፡፡ (አል-አንዓም ፡ 84 -87)

> መልእክተኞች ባጠቃላይ የሰው ልጅ እንደሆኑና አላህ መለኮታዊ ርእይና መልእክት ከሰዎች ለየት ያደረጋቸው እንደሆኑ ቁርአን አረጋግጧል፡፡

መልዕክተኞች ይሳሳታሉ፡፡ የሚሳሳቱት ግን እንደማንኛውም ሰው ሆነ ብለው ሳይሆን በሚያደርጉት ሃሳባዊ ጥረት ነው፡፡ ስለዚህ ከመልዕክተኞች መካከል አንዳቸው ባደረገው ሃሳባዊ ጥረት ቢሳሳት አልያም ስህተት ውስጥ ቢወድቅ አላህይህን ስህተቱን እየተመለከተ ዝም ብሎ

አያልፈውም፡፡ይልቁንም ከዚህ መሰሉ ስህተት ይታረም ዘንድ ይነግረዋል፡፡ ያስተምረዋልም፡፡

ቁርአን ነቢያትን እንዲህ በረቀቀ ሁኔታ እንደሚገልጽ እንመለከታለን፡፡ አገላለጹ ወሰን ያለፈና የተጋነነ አይደለም፡፡ መልእክተኞች ከታላላቅ ሃጢአቶች የተጠበቁ ናቸው፡፡ እንደዚሁም አማልከት ወይም የአማልክት ልጆች አይደሉም፡፡ የመለኮታዊነትና የፈጣሪነት አንዳችም መገለጫ የላቸውም፡፡

ከዚህ አንጻር ነገሩን ይበልጥ የተብራራና ግልጽ የሚያደርገው አላህ ቁርኣን ውስጥ የጠቀሰውና በትንሳኤ ቀን የነብዩ ዒሳን (ዐ.ሰ) (ኢየሱስን) ንጽህናና ሰዎች ከሚናገሩባቸው ያልተገባ ንግግር የጸዱ መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት የሚከተለው ከነብዩ ዒሳ (ዐ.ሰ) ጋር ያደረገው ውይይት ነው፡፡ «አላህም፡- ‹የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ፡- እኔና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን?› በሚለው ጊዜ (አስታውስ)፤ ‹ጥራት ይገባህ፤እኔ ተገቢዬ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም፤ብዬው እንደኾነም በእርግጥ ዐውቀኸዋል፤ነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ፤ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም፤አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም አዋቂ አንተ ብቻ ነህና› ይላል፡፡ ‹በርሱ ያዘዝከኝን ቃል ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም፤በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርኩ፤ተሞላኸኝም ጊዜ (ባነሳኸኝ ጊዜ) አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ፤አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነህ፡፡» (5፡116-117)፡፡

ቁርአንን የሚያነብ ሁሉ በርካታ የቁርአን ምዕራፎች እንደ ኢብራሂም፣ ዩሱፍ የነቢያት ስሞች ከመሰየሙ ባሻገር በዒሳ (ዐ.ሰ) እናት ጥብቋ መርየም ስም ሳይቀር መሰየሙንም ይረዳል፡፡

## እስልምና በመልእክተኞች ላይ ያለው አቋም

አንዳንድ ሰዎች የአላህ መልእክተኛ የሆኑት የሙሐመድ (በእሳቸው ላይ ሰላም ይሁን) ልበ-ወለዳዊ ጽሑፍና ዜና መዋእል አድርገው ይጠረጥራሉ፡፡ ነገር ግን ቁርአን የዒሳን (በእሳቸው ላይ ሰላም እዝነት ይሁን) ታላቅነትና ከከንቱ አባባሎች የጠሩ መሆናቸውን አስመልክቶ 25 ጊዜ ጠቅሷቸዋል፡፡ ሙሳን (በእሳቸው ላይ ሰላምና እዝነት ይሁን) ስም ደግሞ 136 ሲጠቅስ ቁርአን የወረደላቸውን ሙሐመድን (በእሳቸው ላይ ሰላምና እዝነት ይሁን) ከ 5 ጊዜ በላይ አለመጥቀሱን ሲመለከቱ በጣም ይገረማሉ፡፡

በርካታ ሃይማኖቶች ነቢዮቻቸው እውቅና ባልሰጡበት፣ አንዳቸውን የሌላቸውን ነቢያት በጠላትነት በፈረጀበት ወቅት ቁርአንን የሚያነብ ሰው በበርካታ አንቀጾች ውስጥ አንድ ሙስሊም በሁሉም ነቢያት እስካላመነ ድረስ ሙስሊም እንደማይሆን እንደሚያረጋግጥ ያገኛል፡፡ አንድ ሙስሊም አንዳቸውን ቢክድ ወይም በአንዳቸው መልእክት ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ ቢያሳድር ወይም በከንቱ ቢጠረጥር በእርግጥ ከእስልምና ወጥቷል፡፡ መልእክተኛውና በእርሱ ያመኑ በእርግጥ ከአላህ ዘንድ በመጣው መልእክት አምነዋል፡፡ በዚህም መሰረት በአላህ፣ በመላእክት፣ በመልእክተኞች ያመኑ ሲሆን በመካከላቸውም በማመን አንዳቸውንም አይለዩም፡፡ (አል-በቀራህ ፡ 285)



# እስልምና በዒሳ (ዐ.ሰ) (ኢየሱስ) ላይ ያለው አቋም



ዒሳ (ዐ.ሰ) በታሪክ ታላላቅ ሰዎችና መልካም ነገሮችን ለሰዎች ካበረከቱ ሰዎች መካከል አንዱ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ እሳቸውን አስመልክቶ ሰዎች በአመለካከት ተለያይተዋል፡፡ አምላክ ያደረጓቸው ወይም የአምላክ ልጅ ያደረጓቸውም አሉ፡፡ አንዳንዶች በከንቱ ንግግሮች አጣጥለዋቸዋል፡፡ ታዲያ ከዚህ በመነሳት በዒሳ (ዐ.ሰ) ላይ የኢስላም አቋም ምንድን ነው?




## 1 ዒሳ (ዐ.ሰ) ከታላላቅ መልዕክተኞች መካከል አንዱ ናቸው፡

ዒሳ (ዐ.ሰ) ከታላላቅና ከፍተኛ ስፍራ ካላቸው መልእክተኞች መካከል አንዱ እንደሆኑ እናታቸው መርየም እውነተኛ፣ ፍጹም አምላኪ፣ ጌታዋን ተገዢ፣ ጥብቅና ድንግልናዋን ጠባቂ እንደሆነች ቁርአን ያረጋግጣል፡፡ በእርግጥ ዒሳን (ዐ.ሰ) ካለአባት በአላህ ችሮታ ጸንሳለች፡፡ አላህ አደምን ካለአባትና እናት በፈጠረበት ተአምርም ለዘላለም ተአምር ይሆኑ ዘንድ ዒሳን (ዐ.ሰ) ፈጥሯቸዋል፡፡ ልክ አላህ በቁርአን ላይ፤ዒሳ ዘላለማዊ ተአምር ነው፡፡ ልክ አደምን ካለአባትና እናት እንደፈጠረ ሁሉ ዒሳን ካለአባት በችሮታው «ሁን» ሲለው በሚሆነው ቃሉ ፈጥሮታል፡፡ « አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አዳም ብጤ ነው፡፡ ከዐፈር ፈጠረው፡፡ ከዚያም ለርሱ (ሰው) «ኹን» አለው፤ ኾነም፡፡» (አል-ዒምራን ፡ 59)

## 2 ማንኛውም ሙስሊም በተአምራቶቻቸው ያምናል፡

ማንኛውም ሙስሊም አላህ በዒሳ (ዐ.ሰ) እጆች ባሳያቸው እንደ የለምጥ በሽተኞችን ማዳን፣ለዓይነ-ስውራን ብርሃን መስጠት፣ሙታንን ከሞት መቀስቀስ (ዳግም ሕይወት እንዲኖራቸው ማድረግ)፣ሰዎች በቤቶቻቸው ውስጥ ምን እንደሚያስቀምጡና ምን እንደሚበሉ ማወቅ ወዘተ... የመሳሰሉ ተአምራት ያምናል፡፡ እነዚህ ተአምራት በአላህ ፈቃድ የሚከሰቱ ከመሆናቸውም ባሻገር ዒሳ (ዐ.ሰ) የአላህ መልዕክተኛና ነብይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ግልጽ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

## 3 ቅዱስ የሆነና ኢንጂል (ወንጌል) የተሰኘ መለኮታዊ መመሪያ አላህ አውርዶላቸዋል፡

አላህ በእሳቸው ላይ ከመጽሐፍቱ መካከል አንዱ የሆነው መጽሐፍ (ኢንጂል) ለሰዎች ቅን መመሪያነት፣ ብርሃንነትና እዝነትነት እንዳወረደላቸውና በታሪክ ሂደት በኢንጂል ላይ የተለያዩ ለውጦች መበረዞች እንደተፈጸሙ ቁርአን ያረጋግጣል፡፡

LAUNCHING
CURiOSiTY
CLICK HERE

## 4 ዒሳ (ዐ.ሰ) ሰው እንጂ አምላክ አይደሉም፡

እስልምና ዒሳ (ዐ.ሰ) ከሰው ልጆች የተገኙ ሰው እንደሆኑ ከሰዎችም ተመርጠው ወደ እስራኤላዊያን አላህ እንደላካቸው፣ በእጆቻቸውም የተለያዩ ተአምራትን እንዳሳዩ፣ የመለኮታዊነትም ሆነ የጌትነት መገለጫዎች እንደሌላቸው ያረጋግጣል፡፡ ልክ ቁርአን እንዳለው፡- ዒሳ መልካም ባሪያ የሆነ፣ ጸጋችንም ያላበስነው፣ ለሕዝቦቹ ማስረጃና በመልካም ነገር ላይ አመላካች ይሆን ዘንድ ተአምራትን የሰጠነው ቢሆን እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ «እርሱ በርሱ ላይ የለገስንለት ለእስራኤለም ልጆች ተዓምር ያደረግነው የኾነ ባሪያ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡» (አዝ-ዙኽሩፍ ፡ 59)

## 5 አልተሰቀሉም ነገር ግን ወደ ሰማይ አርገዋል፡

በእስልምና አመለካከትና አስተምህሮ ዒሳ (ዐ.ሰ) አልተገደሉም፣ አልተሰቀሉም፡፡በተቃራኒው ጠላቶቻቸው ሊገድሏቸው ሲመጡ አላህ እሳቸውን ወደ ሰማይ ካሳረጋቸው በኋላ ከጠላቶቻቸው መካከል አንዱን ከእሳቸው ምስል ጋር እንዲመሳሰል አደረገ፡፡ ጠላቶቻቸውም ይህ ሰው ዒሳ (ዐ.ሰ) ነው ብለው በማሰብ የተመሳሰለውን ግለሰብ ገደሉት፣ሰቀሉት የሚል አስተምህሮ አለው፡፡ቁርኣን ይህን አረጋግጧል (4፡ 157-158) ፡፡

# የነብያት የዘር ሐረግ

የአላህ ነቢያት ብዙ ናቸው፡፡ እነዚህ ከእነርሱ ይበልጥ ታዋቂዎቹ ናቸው (የአላህ ሰላምታና እዝነት በእነሱ ላይ ይሁን)፡፡

## አደም

አደም (አዳም) የሰው ልጆች አባት ሲሆን አላህ ከአፈር ፈጥሮታል፣መላእክትም ለርሱ ክብር እንዲሰግዱለት አድርጓል፣ከገነትም ወደ ምድር አውርዶታል፡፡

## ኑሕ

ኑሕ (ኖኅ) ሕዝባቸውን ወደ ቀጥተኛው መንገድ ጠርተዋል፡፡ ነገር ግን ሕዝቦቻቸው እርሳቸውን አስተባብለዋል፡፡ ይህን በማድረጋቸው ከነርሱ መካከል ኑህና በርሳቸው ያመኑ ሰዎች ነጻ ሲወጡ ሌሎቹ ግን በጎርፍ መጥለቅለቅ ተቀጥተዋል፡፡

## ኢብራሂም

ኢብራሂም (አብርሃም) የነብያት አባት፣አላህን በብቸኝነት ወደ መገዛት ከጠሩት የላቁ መልዕክተኞች መካከል አንዱ ከመሆናቸው ባሻገር የሙስሊሞች የስግደት አቅጣጫ የሆነውን ካዕባ የተሰኘ ቤት የገነቡ ነብይ ናቸው፡፡

## ኢስማዒል

ኢስማዒል (እስማኤል) የነብዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ) (አብርሃም) ልጅ ሲሆኑ ካዕባን በመገንባቱ ሂደት አባታቸው ኢብራሂምን ረድተዋል፡፡

## ኢስሐቅ

ኢስሐቅ (ይሳቅ)፡- የኢብራሂም (ዐ.ሰ) ልጅ ናቸው፡፡ መላእክት አባታቸውን ልጅ በመውለድ ካበሰሯቸው በኋላ ተወለዱ፡፡

## ያዕቁብ

የነብዩ ኢስሐቅ (ይስሐቅ) (ዐ.ሰ) ልጅ ሲሆኑ እስራኤል በመባልም ይታወቃሉ፡፡ በዚህ ሳቢያም የእስራኤል ልጆች በሙሉ ወደርሳቸው ይመደባሉ፡፡

## ዩሱፍ

ዩሱፍ (ዮሴፍ)፡- የየዕቁብ (ዐ.ሰ) ልጅ ናቸው፡፡ ለበርካታ ችግሮች ተዳርገዋል፡፡ በስተመጨረሻ በግብጽ አስተዳደር ሆነዋል፡፡

## ሙሳ

ሙሳ (ሙሴ) አላህ ወደ እስራኤል ልጆች ከላካቸው የላቁ መልዕክተኞች መካከል አንዱ ሲሆኑ መለኮታዊ መመሪያ ይሆናቸው ዘንድ አላህ ተውራት (ኦሪት) የተሰኘ መለኮታዊ መጽሐፍ አውርዶላቸዋል፡፡ በተአምራትም አጎናጽፏቸዋል፡፡ በጊዜያቸው የነበረው የግብፅ ንጉሥ ፈርኦን አስተባብሏቸዋል፡፡እሳቸውና ተከታዮቻቸው ነጻ ሲወጡ ፈርኦን ነብዩ ሙሳን (ዐ.ሰ) በማስተባበሉ አላህ ባሕር ውስጥ አስጥሞታል፡፡

## ዳዉድ

ዳዉድ (ዳዊት) በሕዝቦቻቸው ውስጥ አላህ ስልጣንን የሰጣቸው ነብይ ናቸው፡፡

## ሱለይማን

ሱለይማን (ሰለሞን)፡- የዳዉድ (ዐ.ሰ) ልጅ ናቸው፡፡ አላህ በርካታ ስልጣን የሰጣቸውና በርካታ ፍጡራን ለእርሳቸው ያደሩላቸሰው ነቢይ ናቸው፡፡

## ዘከሪያህ

ዘከሪያህ (ዘካሪያስ) ከእስራኤል ልጆች ውስጥ የአላህ ነብይ ከሆኑ ነብያት መካከል አንዱ ሲሆኑ የዒሳን (ኢየሱስ ክርስቶስን) እናት መርያምን (ማርያምን) (ዐ.ሰ) በማሳደግ፣በመንከባከብና በማስተማር ላይ ሞግዚት የነበሩ ናቸው፡፡ እርጅና ላይ ሆነው ሳለና ባለቤታቸውም መኻን በነበሩበት ወቅት የሕያ (ዮሐንስ) የተባለ ልጅ አላህ ሰጥቷቸዋል፡፡

## ዒሳ

ዒሳ (ኢየሱስ) በአላህ ዘንድ በእጅጉ ከላቁት መልዕክተኞች መካከል አንዱ ሲሆኑ አላህ ካለ አባት ከእናት ብቻ ፈጥሯቸው ወደ እስራኤል ልጆች በመልዕክተኛነት ልኳቸዋል፡፡ መለኮታዊ መመሪያ ይሆናቸው ዘንድ ኢንጂል (ወንጌል) የተነሰኘ መለኮታዊ መጽሐፍ አውርዶላቸዋል፡፡በተለያዩ ተአምራትም አጎናጽፏቸዋል፡፡

## ሙሐመድ

ሙሐመድ፡- የነቢያት መቋጫ፤ ከእሳቸው በፊት የነበሩትን መልእክተኞች እውነታነት አስመስክሮ አላህ ለሰው ልጆች ባጠቃላይ ልኳቸዋል፡፡ ከንቱ ነገር ከፊቱም ከኋላውም የማይመጣበትን ቁርአንንም አውርዶላቸዋል፡፡



# የእስልምና መልዕክተኛ ማን ናቸው?

# ሙሐመድ

ሙሐመድ የኢስላም ነቢይ ስም ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ዙርያ በስፋት ተሰራጭተው ከሚገኙ ስሞች መካከል አንዱ ሲሆን ትርጉሙም በስነ-ምግባራቱና በተግባራቱ ሰዎች የሚያመሰግኑት የሚያወደሱት ሰው ማለት ነው፡፡

ሙሐመድ ማነው?

## የእስልምና መልዕክተኛ ስም፡-

ስማቸው ሙሐመድ ኢብን አብዳላህ ኢብን አብዱልሙጠሊብ ኢብንሃሺም አል-ቁረሺይ ሲሆን እ.ኤ.አ ከ570 -632 ዓ.ል ድረስ በሕይወት የኖሩ ናቸው፡፡

ሙስሊሞች ባጠቃላይ እሳቸው፡-

## ወደ ሰው ልጆች በአጠቃላይ የተላኩ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው፡

አላህ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ለሰው ልጆች በአጠቃላይ ልኳል፡፡ እሳቸውንም መታዘዝ በሰው ልጆች ላይ ግዴታ አድርጓል፡፡ይህን አስመልክቶ አላህ እንዲህ ብሏል፣ ‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው፡- እላንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደ ሁላችሁም የአላህ መልዕክተኛ ነኝ፤›› (7፡ 158)፡፡

## ቁርአንን አውርዶላቸዋል፡

አላህ በሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ከመለኮታዊ መጽሐፍቱ የላቀውን፣የእነርሱ መጨረሻና ማጠቃለያ የሆነውን እንዲሁም ከፊቱም ሆነ ከኋላው ምንም ዓይነት እንከን የማያገኘውን ቁርአን የተሰኘ መለኮታዊ መጽሐፍ አውርዷል፡፡

## የነቢያት እና የመልዕክተኞች መደምደሚያ፡

ቁርአን እንዳለው አላህ ሙሐመድን (ዐ.ሰ) የነቢያት መቋጫ አድርጎ ልኳቸዋል፡፡ ከእሳቸው በኋላ ነቢይ አይመጣም፡፡ ‹‹ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፡፡›› (አል-አሕዛብ ፡ 40)



የእስልምናን መልዕክተኛ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ለማወቅ የሚረዳ አጠር ያለ ዳሰሳ፡-

1. ውልደታቸው፡

እ.ኤ.አ 570 በምዕራብ አረቢያ በምትገኘው መካ ከተማ ውስጥ አባታቸውን በሞት ያጡ የሙት ልጅ ሆነው ተወለዱ፡፡ በልጅነት እድሜያቸው እናታቸውን በሞት አጡ፡፡ በአያታቸው በአብዱል ሙጠልሊብ እንክብካቤ ስር እስከ ተወሰነ እድሜያቸው ድረስ አደጉ፡፡እሳቸውንም በሞት አጡ፡፡ ከዚያ በመልዕክተኛነት እስከተላኩበት እድሜያቸው ድረስበአጎታቸው እንክብካቤ ስር አደጉ፡፡

2. ሕይወታቸውና አስተዳደጋቸው፡

በነቢይነት ከመላካቸው በፊት እ.ኤ.አ ከ570 እስከ 609 ዓ.ል ድረስ ቁረይሽ በተባለው ጎሳቸው ውስጥ የመልካም ስነ-ምግባርና የቀናኢነት ተምሳሌት ሆነው ኖረዋል፡፡ በተለይም እውነተኛውና ታማኙ በሚል የማዕረግ ስም ይጠሩ ነበር፡፡ በልጅነታቸው በእረኛነት ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ በንግድ ስራ ላይ ተሰማርተዋል፡፡

በነቢይነት ከመላካቸው በፊት የነቢዩ ኢብራሂምን (አብራሃምን) መንገድ በመከተል ፈጣሪያቸውን ያመልኩ የነበሩ ከመሆናቸው ባሻገር የጣኦታትን አምልኮና ጣኦተኛነትን አጥብቀው ይቃወሙ ነበር፡፡ ከዚሁም ጋር ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መጻፍና ማንበብ የማይችሉ መሃይም ነበሩ፡፡

## 3. ተልዕኳቸው፡

የአላህ መልእክተኛ (ዐ.ሰ) እድሜያቸው አርባ ዓመት ሲሞላ (መካ ውስጥ ከሚገኙ ተራራዎች መካከል አንዱ በሆነው) በኑር ተራራ ላይ በሚገኘው ሒራእ ዋሻ ውስጥ ያስተነትኑ፣ አላህንም ያመልኩ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ መለኮታዊ ርእይ መጣላቸው፡፡ ቁርአንም ይወርድላቸው ጀመር፡፡ ከቁርአን አንቀጾች መካከል በመጀመሪያ የወረደላቸው የአላህ ቃል የሆነውና በፈጠረህ በጌታህ ስም በመታገዝ አንበብ የሚል ነበር፡፡ «አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም፡፡» (አል-ዐለቅ፡1) ይህ የወረደው ይህ ተልእኮ ከጅማሬው የእውቀት፣ የንባብ፣ የብርሃንና ሰዎችን ወደቅኑ መንገድ የመመራት ዘመን እንደሆነ እንደያውጁ ነው፡፡ ከዚያ ቁርአን ለሃያ ሶስት ዓመታት በተከታታይ በእሳቸው ላይ ወረደ፡፡



## 4. የጥሪያቸው ጅማሮ፡

የአላህ መልዕክተኛ ለሶስት ዓመታት በምስጢር ጥሪያቸውን ሲያስተላልፉ ከቆዩ በኋላ ቀሪዎቹን አስር ዓመታት መካ ውስጥ በይፋ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡ ፡ሌሎች መልዕክተኞች በአጠቃላይ ድሆችና አቅመ-ደካሞች ይከተሏቸው እንደነበረው ሁሉ እሳቸውንም የተከተሏቸው ድሆችና አቅመ-ደካማ ሰዎች ነበሩ፡፡ለሰዎች ጥሪ በማድረጋቸው የተነሳ የአላህ መልዕክተኛና በእሳቸው ያመኑ ምእመናን ከፍተኛ ችግር፣መከራ ጭቆናና በደል ከጎሳቸው ከቁረይሽ አባላት በኩል ደርሶባቸዋል፡፡ የሐጅ ስነ-ስርአትን ለመፈጸም ወደ መካ ይመጡ ለነበሩ የተለያዩ ጎሳዎች እስልምናን ይሰብኩ ስለነበር በወቅቱ ከመዲና ለሐጅ የመጡ ሰዎች ጥሪያቸውን ሰምተው በመቀበላቸው ቀስበቀስ ወደነሱ (ወደመዲና) የሙስሊሞች ስደት ተካሄደ፡፡

## 5. ስደታቸው፡

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እድሜያቸው ሃምሳ ሶስት ሲሆን ጥሪያቸውን የተቃወሙት የቁረይሽ ጎሳ ባላባቶች እሳቸውን ለመግደል ስላሴሩባቸው የተወለዱባትን፣ያደጉባትንና የእስልምናን ጥሪ የጀመሩባትን ያቺን የሚወዷትን መካን ትተው በወቅቱ የሥሪብ ተብላ ትጠራ ወደ ነበረችው መዲና አል-ሙነወራህ እ.ኤ.አ በ622 ዓ.ል ተሰደዱ፡፡ እዚያም ለአስር ዓመታት ሰዎችን ወደ እስልምና እየጠሩ ኖሩ፡፡ መዲና ውስጥ በስደት ላይ እያሉ ስግደት፣ምጽዋት፣የስነ- ምግባር እሴቶችና ሌሎች እስላማዊ ድንጋጌዎች ተደነገጉ፡፡



## 6. እስልምናን ማሰራጨታቸው፡

የአላህመልዕክተኛየእስልምናስልጣኔንእ.ኤ.አከ622-632 ዓ.ል መዲና ውስጥ በስደት ላይ እያሉ መሰረቱ፡፡ የሙስሊም ማህበረሰብ መገለጫ የሆኑ እሴቶችን በሙስሊሞች መካከል አሰረጹ፡፡የዘረኝነትን በሽታ አጠፉ፡፡ እውቀትን አስፋፉ፡፡ የፍትሕ፣የወንድማማችነትን፣የመረዳዳትንና የመተጋገዝን ስርአት አሰፈኑ፡፡ አንዳንድ ጎሳዎች እስልምናን ለማጥፋት ሞከሩ፡፡ በዚህም የተነሳ በሙስሊሞችና እስልምናን ለማጥፋት ቋምጠው በተነሱ ሕዝቦች መካከል በርካታ ጦርነቶች ተካሄዱ፡፡ አላህም እስልምና እና መልዕክተኛው ድልን እንዲቀዳጁ አደረገ፡፡ እለት ከእለትም በራሳቸው መልካም ፈቃድ ወደ እስልምና የሚገቡ ሰዎች እየጨመረ ሄደ፡፡ መካ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የተለያዩ ጎሳ አባላት እንዲሁም በአረቢያ ግዛት ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የተለያዩ ጎሳዎች ማንም ሳያስገድዳቸው የእስልምናን ትልቅነትና እውነተኛነት በማመን ወደ ሃይማኖቱ ገቡ፡፡

## 7. ሕልፈታቸው፡

የአላህ መልዕክተኛ የተላኩበትን የእስልምና መልዕክት በተገቢው ለሰዎች ካደረሱ፣አላህም ሃይማኖቱን በመሙላት ጸጋውን በሰዎች ላይ ካሰፈነ በኋላ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ መዲና በተሰደዱ በአስራ አንደኛ ዓመታቸው በሃይለኛ ንዳድ ታመሙ፡፡ሕመሙም ስለጠናባቸው የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሰኞ እለት በወርሃ ረቢዑ-ል-አወል 11ኛው ዓመተ ሂጅራ (እ.ኤ.አ በ8/6/632 ዓ.ል) ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ በሞት ሲለዩም እድሜያቸው በስልሳዎቹ አካባቢ የነበረ ሲሆን በባለቤታቸው በዓኢሻህ ቤት ውስጥ ከመስጂዳቸው አጠገብ ተቀበሩ፡፡





# የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድ በፍትሐዊ አስተዋዮች እይታ

ባህሉ

(ባህሉ የትኛውም ይሁን) የነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) የሕይወት ታሪክ ያጠና ማንኛውም ፍትሐዊ አስተዋይ ሰው በእሳቸው ታሪክ ከመደነቅና ከመመሰጥ ውጭ ሌላ የሚለው ነገር የለም፡፡ በምዕራብና ምስራቅ የሚገኙ ስመ-ጥር ምሁራን፣ፈላስፎችና የስነ-ጸሑፍ ሰዎች ለዚህ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመጣጥፎቻቸውና በመጻሐፎቻቸው ውስጥ በጉልህ አስቀምጠዋል፡፡ ከእነዚህ ስመ-ጥር የዓለማችን ታላላቅ ሰዎች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡፡



እ.ኤ.አ በ1924 ዓ.ል 'Young India' ለተሰኘ የሕንድ ጋዜጣ ማህተመጋንዲ እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ «በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን ልብ ካለምንም ንትርክና ሃይል ለመግዛት ስለቻለ ሰው መገለጫ ማወቅ ፈለግኩኝ፡፡ በእርግጥም ሰይፍ ለእስልምና ይህን ስፍራ እንዳላጎናጸፈና እንዲጎናጸፍም ምክንያት እንደማይሆን ከልቤ እርግጠኛ ለመሆን በቃሁ፡፡ በአንጻሩ ይህን ሊያጎናጽፈው የቻለው የመልዕክተኛው እውነተኛነት፣ቃልኪዳን ጠባቂነት፣ለባልንጀሮቹና ለተከታዮቹ ይቅር ባይነትና ቀናኢነት እንዲሁም በጌታውና በመልዕክቱ ላይ የነበረው የመተማመን ጀግንነት እንደሆነ ተረዳሁ፡፡ ሰይፍ ሳይሆን እነዚህ መገለጫዎች ለእስልምና መንገዶቹን ሁሉ ጠርገዋል፡፡ ችግሮችን እንዲያልፍ አድርገዋል፡፡ የመልዕክተኛውን ሕይወት ታሪክ ሁለተኛ ክፍል አንብቤ ስጨርስ ስለዚህ ታላቅ ሰው የሕይወት ታሪክ ይበልጥ እንዳውቅ ተጨማሪ ምንጭ ባለማግኘቴ እጅጉ ተጸጸትኩኝ፡፡»

በጽሑፎቹ ስብስብ ቅጽ ፡ 25 ገጽ ፡ 127 ላይ ሰፍሯል፡፡

“ካለጦርነት የሚሊዮኖችን ልቦና ሊቆጣጠር የቻለውን ሰው መገለጫዎች ማወቅ ፈለግኩኝ፡፡ እስልምና ቦታውን እንዲቀዳጅ አንዱ መንገድ ፈጽሞ ሰይፍ እንዳልሆነ ሙሉ ለሙሉ ላለረጋግጥና ላምን ችያለሁ፡፡” ማሐተመ ጋንዲ



ማይክል ሐርት «100ዎቹ በታሪክ ውስጥ በጣም ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎች» (The 100: A Ranking of the Most Influential Persons in History) የተሰኘውን መጽሐፉን ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) በማስቀደም ጀምሯል፡፡ ይህን የመረጠበትን ምክንያት ሲያስረዳ ሚካኤል ሐርት እንዲህ ብሏል፣ «በታሪክ ውስጥ ከነበሩት ታላላቅ ሰዎች መካከል ሙሐመድ የመጀመሪያ እንዲሆን መምረጤ አብዛኛውን አንባቢ ሊያስገርም ይችላል፡፡ ነገር ግን እሱ በታሪክ ውስጥ ካሉት በአጠቃላይ በሁለት ደረጃዎች ከፍተኛ ስኬትን ተቀዳጅቷል፡፡ እነርሱም፡- ሃይማኖታዊና ምድራዊ ናቸው፡፡»

The 100: A Ranking of the Most Influentail Persons in History በተሰኘው መጽሐፉ ገጽ ፡ 3



ዝነኛው ፈረንሳዊ ገጣሚ አልፎንስ ዱላ ማርቲን ‹‹የቱርክ ታሪክ›› በተሰኘው መጽሐፉ፣ ‹‹የዓላማ ጽናት፣ የመገናኛ ዘዴዎች ደካማነትና የውጤቶቹ ትልቅነት እነዚህ ሶስቱ የጀግና ሰው መገለጫዎች ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት ሙሐመድን በታሪክ ካለፉት ታላላቅ ጀግኖች ጋር የሚያነጻጽረው ማነው?›› Histoire de la Turquie ቅጽ ፡ 1 ገጽ ፡ 111



ሕንዳዊው ፈላስፋ ራማ ክሪሽና እንዲህ ብሏል፤ ‹‹ነገሮች ሁሉ ተለዋውጠዋል፡፡ ነገር ግን በድልም ሆነ በሽንፈት፣ በስልጣንም ሆነ በብርቱ ሁኔታዎች፣ በፍሰሐና በችግር ጊዜ ሙሐመድ ፈጽሞ አልተቀየረም፡፡ በዚያው ስብእናው በዚያው መገለጫው ላይ ያለ ሰው ነው፡፡ ልክ በሁሉም ነቢያት ላይ እንደማይቀየረው የአላህ ፍላጎት አልተቀየረም፡፡



ስመ-ጥሩ ጀርመናዊ ገጣሚ ጎቴ (ጆሃን ዎልፍጋንግ ቮን ጎቴ) (እ.ኤ.አ በ1832 የሞተ) ‹የሙሐመድ ትራጄዲ› በተሰኘው ግጥማዊ ተውኔት የሙሐመድን የሕይወት ታሪክ በማሞገስና በማስዋብ ካቀረበ በኋላ ሰባ ሰባተኛው እድሜው ላይ ቢደርስም ስለእስልምና ያለው አድናቆት ፈጽሞ እንደማይመነምን እንዲያውም ይበልጥ እንደሚልቅ በደንብም ወደውስጡ ሰርጾ እንደሚገባ በመናገር ስለእስልምና ያለውን አድናቆት ሲናገር ተስተውሏል፡፡

ይህን እንዲሁ ካርቲና ሞሚዝን ስለጎቴ በጻፈችበት መጽሐፏ ጠቅሳለች፡፡ Goethe und die arabische Welt ገጽ ፡ 177.

ፕሮፌሰር ስቱዋርት እንዲህ ብለዋል፡- « በሰው ልጆች ታሪክ ባጠቃላይ ከሙሐመድ ስብእና ጋር የሚቀራረብ ስብእና አይገኝም፡፡ በትንሹ ያገኘው ቁሳዊ ነገር፣ ያመጣው ወደር የማይገኝለት የላቀ ጅግንነት፣ ታሪክን ከዚህ አንጻር ካጠናን ይህን ብርሃን የሚያበራ ስም ፈጽሞ አናገኝም፡፡ ከሁሉ ነገር በላይ ዐረብ ከሆነው ነቢይ ስም ይበልጥ ግልጽ የሆነ ነገር የለም፡፡ Islam and Its Fouder ገጽ ፡ 227- 228፡፡



ሳይሞን አክሌይ የኢስላማዊ ግዛቶች ታሪክ በተሰኘው መጽሐፉ ላይ እንዲህ ብሏል፤ «ግርምት የሚገባው እስላማዊ ጥሪ መስፋፋት ሳይሆን ለዘመናት ቀጣይነቱና ጽናቱ ነው፡፡ እስከአሁንም ሙሐመድ በመካና በመዲና ያሳረፈው አሻራ አስገራሚና ደስ የሚል አሻራ ነው፡፡ እስከአሁንም የራሱን መስህብነትና ብርታት በሕንዳውያን፣ በአፍሪካውያንና በቱርኮች ዘንድ የቅርብ ዘመን ትውስታ ነው፡፡» History of Saracen Empire ገጽ ፡ 45፡፡

> “ሙሐመድ መካና መዲና ውስጥ የተከለው መሰረት ከቁርአን ጋር አዲስ ከሆኑት ሕንዳዊያን፣ አፍሪካዊያንና ቱርኮች ነፍስ ውስጥ የራሱ ውበትና ጥንካሬ አለው፡፡” ሳይሞን አክሌይ



ዋል ዱራንት ‹የስልጣኔ ታሪክ› (The Story of Civilization) በተሰኘው የአውደ-ጥበብ መጽሐፉ ቅጽ፣ 13 ገጽ፣ 45-47 ላይ እንዲህ በማለት አስፍሯል፣

‹‹አንድ ታላቅ ሰው በሰዎች ውስጥ ባሳደረው ተጽእኖ ሳቢያ በትልቅነት ላይ ውሳኔ የምስጥ ከሆነ ሙሐመድ በታሪክ ታላላቅ ነበሩ ከሚባሉት መካከል ትልቁ ሰው ነበር ማለት እንችላለን፡፡ የአረመኔነት ጨለማ ያጠለለበትን፣ በድርቅና በሐሩር የነተበ ሕዝብን መንፈሳዊና ስነ-ምግባራዊ ደረጃውን ከፍ ለማድረግ ለራሱ ቃል ገብቷል፡፡ በታሪክ ውስጥ ማንም የሰው ልጅን ለማስተካከል የሚጥር ሰው ሊያሳካው የማይችለውን ታላቅ ግብ በተሳካ ሁኔታ ሊያሳካና ከግብ ሊያደርስ ችሏል፡፡ በትክክል ቀድሞ ያሰበውንና ያለመውን ሙሉ ለሙሉ ያሳካ ሰው የማግኘት እድሉ በጣም አናሳ ነው፡፡ሙሐመድ ጥሪውን ማስተላለፍ በጀመረበት ወቅት አረቢያ ጥቂት ጣኦት የሚያመልኩ ሰዎች የሚኖሩባት፣ ቋንቋቸው በጥቂቱ የሚለያዩ ማህበረሰቦች የሚገኙባት ምድረ-በዳ የሆነች ግዛት ነበረች፡፡ ሙሐመድ ሲሞት ግን የተሳሰሩና አንድ የሆኑ ሕዝቦች ያሉባት ግዛት ነበረች፡፡ አጉል ባህሎችንና ዘረኝነትን አሽቀንጥሯል፡፡ በአይሁዳዊያን፣ በክርስቲያንና በአባቶቹ የቀድሞ እምነት መካከል ቀለል፣ ግልጽ፣ ብርቱና ቀጥተኛ የሆነንና የብሔርተኝነትን ኩራት የሚያላብስ ሃይማኖት መስርቷል፡፡ በአንድ ትውልድ በመቶዎች

የሚቆጠሩ ጦርነቶችን በድል ለማጠናቀቅ እንዲሁም በአንድ ክፍለ-ዘመን ውስጥ ታላቅ ሀገር ለመመስረት ችሏል፡፡ እስከአሁኑ ድረስ በዓለማችን ላይ አስጊ የሚሆን ሃይል እንዲቆይ አድርጓል፡፡»

The Story of Civilaization: The age of Faith ክፍል አራት ገጽ ፡ 174›

> “አንድ ታላቅ ሰው በሰዎች ውስጥ ባለው ተጽእኖ በታላቅነት ላይ የምንፈርድ ከሆነ፤ ሙሐመድ በታሪክ ታላላቅ ከሆኑ ይበልጥ ታላቅ የሆነ ሰው ነው፡፡» ዌል ዱራንት




እስልምናን ሳይቀበል በፊት ለሙሐመድ ብርቱ ጠላት የነበረ ሰው እስልምናን ከተቀበለ በኋላ በአንድ ወቅት ስለተከሰተ ታሪካዊ ክስተት ተርኮልናል፡፡ ይኸውም ወደ እስልምና ጥሪ ያደረጉበት የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ደብዳቤ ለሮማ ንጉስ እ.ኤ.አ በ628 ዓ.ል ለሄራቅላጦስ ይደርሰዋል፡፡ ሄራቅላጦስ በዚህ ደብዳቤ በመገረም ከተላከው ነቢይ ጋር ቅርበትና ትውውቅ ያለው አረባዊ ሰው እንዲመጣለት ያዛል፡፡ ባዘዘውም መሰረት በንግድ ምክንያት ሻም ውስጥ የነበረው አቡሱፍያን (በወቅቱ ከቁረይሽ ጎሳ ባላበቶች መካከል አንዱ ስለነበር) እሱና ከእሱ ጋር ያሉት ሰዎች ወደ ንጉሱ ቤተ- መንግስት እንዲመጡ ተደረገ፡፡ ሄራቅላጦስ እነአቡሱፍያን ከቀረቡ በኋላ ስለ መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እውነተኛነት ለመረዳትና ለማወቅ ጥበብና እውቀት የተላበሱ ጥያቄዎችን በአስተርጓሚው በኩል አቡሱፍያንን ጠየቀ፡፡አቡሱፍያን ለጥያቄዎቹ መልስ ከሰጠ በኋላ ሄራቅላጦስ ለአቡሱፍያን እንዲህ አለው፣

ስለ ዘር ሐረጉ ጠየቅኩህ በመካከላችሁ ከሆነ የዘር ሐረግ እንደሆነ ነገርከኝ፡፡ መልዕክተኞችም የሚላኩት በሕዝቦቻቸው ዘር ውስጥ ነው፡፡ከእናንተ መካከል ይህን ቃል የተናገረ ሰው አለን? በማለት ጠየቅኩህ ማንም እንደሌለ ገለጽክ፡፡ ከእናንተ መካከል ይህን ቃል ከርሱ በፊት የተናገረ ቢኖር ኖሮ እሱ የዚያን የቀደመውን ሰው ቃል እያመሳሰለ ነው እል ነበር፡፡

ይህን የሚናገረውን ቃል ሳይናገር በፊት በሐሰት ትወነጅሉት ነበርን? ብዬ ጠየቅኩህ፡፡በፍጹም አልከኝ፡፡ ስለዚህ ይህ ሰው ሰዎችን ሳይዋሽ አላህን ፈጽሞ ሊዋሽ እንደማይችል አወቅኩኝ፡፡

የተከተሉት ሰዎች የተከበሩ ናቸው ወይስ አቅመ- ደካሞች? ብዬ ስጠይቅህ የሚከተሉት አቅመ-ደካሞች እንደሆኑ ነገርከኝ፡፡ እነዚህ ዓይነቶቹ ደግሞ የመልዕክተኞች ተከታዮች ናቸው፡፡ ቁጥራቸው ይጨምራል ወይስ ይቀንሳል? ብዬ ጠየቅኩህ ይጨምራሉ ብለህ ተናገርክ የእምነትም ሁኔታ እስኪሞላ ድረስ እንዲሁ ነው፡፡

አንድ ሰው ወደ ሃይማኖቱ ከገባ በኋላ ጠልቶት ይወጣልን? ብዬ ጠየቅኩህ፡፡ በፍጹም አይወጣም አልከኝ፣ይህ ደግሞ እምነት ከልብ ጋር ሲቀላቀል እንዲሁ ነው፡፡

ቃሉን ያጥፋልን? ብዬ ጠየቅኩህ፡፡ በፍጹም አያጥፍም አልከኝ፡፡ መልዕክተኞችም እንዲሁ ቃላቸውን አያጥፉም፡፡

በምን ላይ ነው የሚያዛችሁ? ብዬ ስጠይቅህ፣አላህን ብቻ እንድታመልኩና በእሱ ላይም አምልኮትን እንዳታጋሩ፣በስግደት፣በምጽዋት እንዲሁም ራሳችሁን ርካሽና ውድቅ ከሆኑ ነገሮች እንድትጠብቁ እንደሚያዛችሁ፣ጣኦታትን ከማምለክ እንደሚከለክላችሁ ነገርከኝ፡፡

ይህ የምትናገረው በእርግጥ እውነት ከሆነ የእነዚህ እግሮቼን ማረፊያ (ስልጣኔን) በእርግጥ ይቆጣጠራል፡፡ ይህ ነቢይ እንደሚመጣ በእርግጥ አውቅ ነበር፡፡ ነገር ግን ከናንተ መካከል ይሆናል ብዬ አልጠረጠርኩም፡፡ እሱ ዘንድ መድረስ የምችል መሆኔን ባውቅ ኖሮ ከእሱ ጋር ለመገናኘት ጥረቴን ሁሉ አደርግ ነበር፡፡ (ቡኻሪ 7)፡፡



# ከመልዕክተኛው ሙሐመድ የሕይወት ታሪክና ስነ-ምግባራት

# በከፊል



# የአላህ

የአላህ መልእክተኛ (ዐ.ሰ) ለሰብአዊ ስነ-ምግባራት የላቁ ተምሳሌት ነበሩ፡፡ በዚህም ምስራቃዊያኑም ሆኑ ምዕራባዊያኑ እንዲሁም ጠላቶቻቸው መስክረውላቸዋል፡፡ ቁርአንም ስነ-ምግባራቸውን በላቀ ስነ-ምግባርነት ገልጾታል፡፡



ባለቤታቸው ዓኢሻህ (ረ.ዐ) ስለአላህ መልእክተኛ ሙሐመድ ስነ-ምግባር ስትጠየቅ ይህ ነው ብላ በረቀቀ ሁኔታ የምትገልጽበት ቋንቋ ባለማግኘቷ፤ «ስነ-ምግባራቸው ቁርአን ነበር፡፡) ብለዋል፡፡ ይህ ማለት የቁርአንን አስተምህሮዎችና ስነ-ምግባራት በተግባር ለማሳየት ተምሳሌት ነበሩ ማለት ነው፡፡ ይህ ታሪካቸው ና ከስነ-ምግባራቸው መካከል በአጭሩ የቀረበ ነው፡፡

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ማንም ሰው ለክብራቸው ብሎ ከተቀመጠበት ቦታ እንዲነሳላቸው ፈጽሞ አይወዱም ነበር፡፡ እንዲያውም ባልደረቦቻቸው እንዲህ እንዳያደርጉላቸው ይከለክሉ ነበር፡፡ ባልደረቦቻቸውም ይህን ስላወቁ ከማንም አስበልጠው ቢወዷቸውም መምጣታቸውን ከሩቅ ቢመለከቱ ከቦታቸው አይነሱም ነበር፡፡እሳቸው ይህን ያደርጉ የነበሩት ለባልደረቦቻቸው ይህ እንዲደረግላቸው እንደማይወዱ ሊያሳውቋቸው እንጂ ለሌላ አይደለም (አሕመድ 12345)

ዐዲይ ኢብን ሓቲም እስልምናን ሳይቀበል ከዐረብ ባላባቶች መካከል አንዱ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን የአላህ መልዕክተኛ ጥሪ እውነተኛነት ለማወቅ ወደ እሳቸው ዘንድ መጣ፡፡ ዐዲይ ወደ እሳቸው ዘንድ ከመጣ በኋላ የተመለከተውን ክስተት እንዲህ በማለት ተርኮታል፡፡ «ወደ እሳቸው ዘንድ ስሄድ እሳቸው ዘንድ አንዲት ሴትና ሁለት ወይም አንድ ሕጻን ነበሩ፡፡ ዐዲይ በዚህ ንግግሩ ሴትዬዋና ሕጻናቱ ከእሳቸው ጋር የነበራቸውን ቅርበት ጠቅሷል እሳቸው እንደ የፋርስና የኮንስታንኖፕል ንጉስ እንዳልሆኑ አወቅኩኝ፡፡» (አህመድ 19381)፡፡ መተናነስ የነቢያት በአጠቃላይ ስነ-ምግባር ነው፡፡

> የኢስላም መልእክተኛ የግል መገልገያዎቻቸውን ራሳቸው ይጠግኑ፣ ቤተሰቦቻቸውንም ያገለግሉ፣ በቤት ውስጥ ስራዎች በመሳተፍ ያግዟቸው ነበር፡፡

እሳቸው ከባልደረቦቻቸው ጋር ሲቀመጡ እንደ አንዱ የይሆኑ ነበር፡፡ይኸውም ከባልደረቦቻቸው ጋር ሲቀመጡ ማንም ባይተዋር ሰው ከመጣ እሳቸውን በቀላሉ ሊለያቸው አይችልም ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ከእናንተ ውስጥ ሙሐመድ ማንነው? ብሎ ይጠይቅ ነበር፡፡ ምክንያቱም እሳቸው በቀላሉ ሊለዩበት የሚችሉበት ልዩ ስፍራና መቀመጫ ስለሌላቸው ነው (ቡኻሪ 63)፡፡

አንዳንድ ባልደረቦቻቸው እንደሚናገሩት ምንም ያህል እሳቸው በጉዳዮች የተጠመዱ ቢሆኑም የሰዎች ጉዳይ ትንሽ ነው የሚባል ቢሆንም እሱኑ ከመፈጸም፣በሰዎች መካከል እርቅንና ሰላምን ከመፍጠር ወደኋላ ብለው አያውቁም፡፡ አንዲት የመዲና ሰዎች አገልጋይ የሆነች ሴት የአላህ መልዕክተኛን (ሰ.ዐ.ወ) እጅ ይዛ ጉዳዮችዋን እስኪፈጸሙላት ድረስ እስከፈለገችበት ስፍራ ይዛቸው ትዞር ነበር (ቡኻሪ 5724)

ታላቁ የመልዕክተኛው ባልደረባ ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ ከእለታት አንድ ቀን ወደ መልዕክተኛው ሙሐመድ ቤት ገቡና የምንጣፍ አሻራ በመልዕክተኛው የጎን አካል ላይ ተመለከቱና በጣም አለቀሱ (ምንጣፉ ከቴምር ዛፍ ዝንጣፊ ቅጠሎች የተሰራ ነበር)፡፡ እሳቸውም ዑመር ያለቀሱበትን ምክንያት ለማወቅ፣ ‹‹ምንድን ነው የሚያስለቅስህ?›› አሏቸው፡፡ ዑመርም፣ ‹‹የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! የፋርስና የኮንስታንትኖፕል ንጉሦች ባሉበት ነገር ላይ እያሉ (በክህደታቸው በድሎታቸው ውስጥ እያሉ) እርስዎስ የአላህ መልዕክተኛ!›› አሏቸው፡፡ መልዕክተኛውም፣ ‹‹ለእነሱ ምድራዊ ዓለም ለእኛ ደግሞ የወዲያኛው ዓለም እንዲሆንልን አትሻምን?›› አሏቸው፡፡ (ቡኻሪ 4629)፡፡

የግላቸውን ስራ በራሳቸው ይፈጽሙ የነበሩ ከመሆናቸውም በሻገር ቤተሰቦቻቸውን በቤት ውስጥ ስራዎች ያግዙ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ባለቤታቸው ዓኢሻህ መልዕክተኛው ቤታቸው ውስጥ ስለነበራቸው ሁኔታ ተጠይቀው ሲመልሱ ‹‹ቤታቸው ውስጥ በቤተሰባቸው ሥራ ውስጥ ይሆኑ ነበር፡፡›› ብለው ነበር፡፡ (ቡኻሪ 644)፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ቤተሰባቸውን ያገለግሉ ነበር ማለት ነው፡፡ ዓኢሻህ አክለው እንዲህ ብለዋል፣ (አንዳችሁ እንደሚሰራው ይሰሩ ነበር፡፡ ጫማቸውን ይጠግናሉ፣ልብሳቸውን ይሰፋሉ፡፡›› (አሕመድ 24749)፡፡

የአላህመልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፣ ‹‹በልቦናው ውስጥ ቅንጣት ኩራት ያለበት ሰው ጀነት አይገባም፡፡›› (ሙስሊም 91)፡፡

## እዝነት

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፣ «አዛኞችን እጅግ በጣም ሩሕሩሕ የሆነው ጌታ ያዝንላቸዋል፡፡ በምድር ላይ ላለው እዘኑ በሰማይ ያለው ያዝንላችኋል፡፡» (አቡዳዉድ 4941)፡፡

የነቢዩ እዝነት በብዙ ሁኔታዎች ይገለጻል፡፡ከእነርሱ መካከል የተውሰኑትን እነሆ፡-

### ለሕጻናት የነበራቸው እዝነት፡-

- ስግደት የእስልምና መሰረት ከመሆኑ ባሻገር በስግደት ውስጥ ተኩኖ ምንም ዓይነት ንግግርም ሆነ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ፈጽሞ አይቻልም፡፡ ነገር ግን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንድ ቀን የሴት ልጃቸው ልጅ የሆነችውን ኡማማህ ቢንት ዘይነብን ይዘዋት ሰግደዋል፡፡ በግንባራቸው መሬት ላይ ሲደፉ እሷን መሬት ላይ ያስቀምጧት ነበር፡፡ እንደገና ሲቆሙ ይሸከሟት ነበር (ቡኻሪ 494)፡፡
- የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ስግደት ጀምረው ቢሆን እንኳ ድንገት የሕጻን ልጅ ለቅሶ ከሰሙ ስግደታቸውን ያፈጥኑት ወይም ቀለል ያደርጉ ነበር፡፡ይህን አስመልክተው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንዲህ ብለዋል፣ «እኔ ስግደት ስጀምር ስግደቱን ማርዘም እፈልጋለሁ፡፡ የሕጻን ልጅ ለቅሶ ስሰማ፣እናቱ ላይ ችግር እንዳይሆን በመጥላት ስግደቴን ማስረዘሙን አልፈዋለሁ፡፡» (ቡኻሪ 675)፡፡

## ለሴቶች የነበራቸው እዝነት፡

- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሴት ልጆችን በመንከባከብና ለእነሱም መልካም በመዋል ላይ አደራ ብለዋል፡፡ እንዲህም ብለዋል፣ «አንዲት ሴት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሴት ልጆች ተሰጥቶት፣የማሳደግ ሃላፊነቱን ተቀብሎ መልካም የዋለላቸው ከሆነ እነሱ ከእሳት ግርዶ ይሆኑለታል፡፡» (ቡኻሪ 5649)
- በዚህ ብቻም አልተወሰኑም የሚስትን መብቶች በመጠበቅ፣ለጉዳዮቿ ትኩረት በመስጠትና እሷንም በመንከባከብ ላይ አጥብቀው አደራ ብለዋል፡፡ እነሱንም አስመልክተው ሰዎች አደራ እንዲባባሉ አዝዘዋል፣ «በሴቶች ጉዳይ ላይ መልካም አደራ ተባባሉ፡፡» (ቡኻሪ 4890)፡፡
- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለቤተሰባቸው በነበራቸው ርሕራሔ ታላቅ ተምሳሌት አስቀምጠዋል፡፡ ይኸውም እሳቸው በእንስሳቸው ላይ በሚፈናጠጡበት ወቅት ታፋቸውን አመቻችተው በማስቀመጥ ሚስታቸው ሰፊያህ (ረ.ዐ) እንስሳው ላይ እንድትፈናጠጥ ያደርጉ ነበር፡፡ (ቡኻሪ 2120)፡፡
- ሴት ልጃቸው ፋጢማህ ወደርሳቸው ስትመጣ እጇን ይዘው ይስሟት፣በተቀመጡበት ቦታ ላይ እንደትቀመጥ ያደርጉ ነበር፡፡ (አቡዳዉድ 5217)፡፡

## ለአቅመ - ደካሞች የነበራቸው እዝነት፡

- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሙት ሕጻናትን (አባቶቻቸውን በሞት ያጡ ሕጻናትን) ሰዎች ይንከባከቧቸው አደራ ብለዋል፡፡ እንዲህም ብለዋል፣ «እኔና የሙት ሕጻንን የሚንከባከብ ሰው ጀነት ውስጥ እንዲህ ነን» ካሉ በኋላ በአመልካችና በመሐል (የቀለበት) ጣቶቻቸው መካከል ትንሽ

በማለያየት ለሰዎች ያለውን ርቀት አመላከቱ፡፡ (ቡኻሪ 4998)፡፡

- ለድሃና ባሏን በሞት ላጣች ሴት የሚለፋን ሰው ለሃይማኖቱ ሲል በአላህ መንገድ ላይ ከሚታገል እንዲሁም ቀኑን በጾም በሚያሳልፍና ሌሊቱን ሲሰግድ ከሚያነጋ ሰው ጋር አመሳስለውታል፡፡ (ቡኻሪ 5661)፡፡
- ለአቅመ-ዳካሞች መራራትና የሚገብቧቸውን መብቶች መስጠት ሲሳይን ለማግኘትና በጠላት ላይ ድል ለመቀዳጀት ምክንያት መሆኑን እንዲህ በማለት ገልጸዋል፣ «አቅመ- ደካሞችን ፈልጉ፡፡ በእርግጥ ድልን የምትቀዳጁትና ሲሳያችሁን የምታገኙት በአቅመ-ደካማዎቻችሁ ነው፡፡» (አቡዳዉድ 2594)፡፡



> መልእክተኛው ሙሐመድ ደካሞችን ማቅረብና ለእነሱም መልካም መዋል ድል ለመቀዳጀትና ሲሳይ ለማግኘት አድርገዋል፡፡

## ፍትሕ፡

- የአላህ መልእክተኛ (ዐ.ሰ) ፍትሐዊ ነበሩ፡፡ በቅርብ ዘመዶቻቸው ላይ ቢሆንም የአላህን ፍርድ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ ይህም፤ «እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በትክክል (ፍትሕ) ቀዋሚዎች በነፍሶቻችሁ ወይም በወላጆችና በቅርብ ዘመዶች ላይ ቢኾንም እንኳ ለአላህ መስካሪዎች ኹኑ፡፡» የሚለውን ትእዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡

- ከእለታት አንድ ቀን አንዲት በጎሳ አባላት ዘንድ ትልቅ ስፍራ ያላት ሴት ሰረቀችና እጇ እንዳይቆረጥ የነቢዩ ባልደረቦች ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጡ፡፡ እሳቸው ግን እንዲህአሉ፣ «ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ! የሙሐመድ ሴት ልጅ ፋጢማህ ብትሰርቅ በእርግጥ እጇን እቆርጣለሁ፡፡» (ቡኻሪ 4053)፡፡

- ወለድን በሰዎች ላይ ክልክል ሲያደርጉ የክልክልነቱን ውሳኔ በመጀመሪያ ተግባራዊ ያደረጉት በአጎታቸው ዐባስ ላይ ነበር፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፣ «ከሁላችንም ወለድ መጀመሪያ የምከለክለው የዐብባስ ኢብን አብዱልሙጠሊብ ወለድ ነው፡፡ እሱ የሁሉም መጀመሪያ ነው፡፡»(1218)

- አንድ አቅመ-ደካማ ምንም ሳይፈራና ሳያቅማማ የሚገባውን መብት ከባለ ጉልበተኞቹ ላይ የመውሰዱን ሂደት እንደ ሕዝቦች እድገትና ስልጣኔ መለኪያ አድርገውታል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፣ «ከሚንተባተብ ውጭ በውስጧ ያለ አቅመ-ደካማ መብቱን ማይወስድባት ሕዝብ አልተቀደሰችም ፡፡» (ኢብን ማጃህ 2426)፡፡

## ትዕግስታቸውና ቻይነታቸው፡

- ከእለታት አንድ ቀን የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጭንቀት ይዟቸው (ከመካ 90 ኪሎ ሜትር ከምትርቅ ተራራማ ወደ ሆነች) ጧኢፍ ወደምትባል ከተማ ሄዱ፡፡ እዚያ ሄደውም ወደ እስልምና ጥሪ አደረጉ፡፡ ነገር ግን የጧኢፍ ነዋሪዎች መጥፎ ምላሽ ሰጧቸው፡፡ ከዚያች ዘመዶቻቸው ካሉባትና ጉዳት ካደረሱባቸው ጧኢፍ ተመልሰው ወደ መካ እያመሩ ሳለ ጧኢፍን ያጠፉላቸው ዘንድ እንዲጠይቋቸው አላህ ሁለት መላእክትን ወደ እሳቸው ዘንድ ላከ፡፡እሳቸውም፣ ‹‹አላህን በብቸኝነት የሚገዛና በርሱ ላይም ምንም ዓይነት ነገር የማያጋራ ሰውን ከእነርሱ መካከል እንዲያወጣ እሻለሁ›› አሉ፡፡ (ቡኻሪ 3059)

- ከዚህ የሚበልጠው ክስተት ደግሞ ከእነዚያ ከጎዷቸውና ከሀገራቸው ካወጧቸው ከመካ ነዋሪዎች ጋር ሳሉ የተከሰተው ክስተት ነው፡፡ ይኸውም የመካ ነዋሪዎች እንደዚያ በአንደበታቸውና በሰይፎቻቸው ጉዳት ማድረሳቸው ሳያንስ ለረዥም ዓመታት ከእሳቸው ጋርም ሆነ ከባልደረቦቻቸው ጋር ምንም ዓይነት የሰላም ስምምነት ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው ነበር፡፡ ሆኖም ልዕልና ከተገባው አላህ ዘንድ ድል መጣ፣በመካ መከፈት ክብርን ሲያጎናጽፋቸው በሁሉም ጠላቶቻቸው ላይ ድልን ከተቀዳጁ በኋላ፣ ‹‹እኔ በናንተ ላይ ምን እንድሰራ ትጠብቃላችሁ?›› አሏቸው፡፡ እነርሱም፣ ‹‹መልካም ትፈጽማለህ፡፡ አንተ የተከበርክ ወንድም፣የተከበረው ወንድማችን ልጅ ነህ፡፡›› አሏቸው፡፡ እሳቸውም፣ ‹‹ወንድሜ ዩሱፍ እንዳለው እላለሁ፡፡ (ይህ ማለት የነቢዩ ያዕቁብ ልጅ ነቢዩ ዩሱፍ እንደዚያ ላሰቃዩትና በውሃ ጉድጓድ ውስጥ ለወረወሩት

ወንድሞቹ ይቅር እንዳላቸው ይቅር እላችኋለሁ ማለታቸው ነው)፡፡ ዩሱፍ ብሏቸዋል፣ «ዛሬ በናንተ ላይ ወቀሳ የለባችሁም፤አላህ ለናንተ ይምራል፤እርሱም ከአዛኞች ሁሉ ይበልጥ አዛኝ ነው፥» (12፡92) ሂዱ እናንተ ነጻ ናችሁ፡፡» አሏቸው፡፡ (አልበይሀቂይ 18275-18276)፡፡

## መልካምነት

- አንድ ሰው መጣና ገንዘብ ጠየቃቸው፡፡እሳቸውም ‹‹የፈለግከውን ግዛ እዳውን መክፈሉ በእኔ ላይ ነው፡፡» አሉት፡፡ ባልደረባቸው ዑመር፣ ‹የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አላህ ከሚችሉት በላይ አላዘዝዎትም፡፡› አሏቸው፡፡ ሰውዬውም፣ ‹ለግስ ከዙፋኑ ባለቤት ትንሽም ብትሆን አትፍራ፡፡» አላቸው፡፡ ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) ፈገግ አሉ፡፡ደስታቸውም ከፊታቸው ታወቀባቸው፡፡ (አል-አሐዲሡ -ል- ሙኽታራህ 88)፡፡
- ሰማንያ ሺህ ዲርሃም የብር ሳንቲሞች መጣላቸው፡፡ መሬት ላይ በሰሌን ላይ አስቀመጡት፡፡ ከዚያም ዞር አሉና ለሰዎች አከፋፈሉት፡፡ እስኪጨርሱ ድረስ ለጠየቃቸው ይሰጡ ነበር፡፡ (አል-ሓኪም 5423)፡፡

> የኢስላም ነቢይ በሕይወት ሳሉ ገንዘብ እንዳልሰበሰቡ ድርሳናት ጠቅሰዋል፡፡

## በምድር ላይ ቀለል ያለሕይወት፡

- የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ‹‹ዓይኖችህንም ፥ከነርሱ (ከሰዎቹ) ክፍሎችን በርሱ ልንፈትናቸው ወደ አጣቀምንበት፥ ወደ ቅርቢቱ ሕይወት ጌጦች አትዘርጋ፡፡ የጌታህ ሲሳይም፥ በጣም በላጭ ዘውታሪም ነው፡፡›› (20፡131) ለሚለው የጌታቸው ቃል ቅን ታዛዥ ነበሩ፡፡

- (ከእሳቸው ሕልፈት በኋላ ሁለተኛው የሙስሊሞች መሪ) ዑመር (ረ.ዐ) ከእለታት አንድ ቀን ወደነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤት ገቡ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በርሳቸውና በሰሌኑ ላይ ፍራሽ በሌለበት የተነጠፈ ሰሌን ላይ ተኝተው አገኟቸው፡፡ ሰሌኑ በጎናቸው ላይ ምልክት አውጥቶ ነበር፡፡ ከዚያስ.. ዑመር እንዲህ በማለት ይተርኩልናል፡፡ ‹‹ዓይኔን ወደ ቤታቸው ቀና አደረግኩ፡፡ በአላህ እምላለሁ! በቤቱ እይታ ውስጥ የሚገባም ነገር አላየሁም፡፡ እናም፣ ‹ለሕዝቦችህ ሲሳያቸውን ያስፋላቸው ዘንድ አላህን ይጠይቁት፡፡ በእርግጥ ፋርሶችና ሮማዊያን አላህን ሳያመልኩት ሲሳያቸውን አስፍቶላቸዋል› አልኳቸው፡፡ እሳቸውም፣ ‹‹የአል-ኸጣብ ልጅ ሆይ! በጥርጣሬ ውስጥ ነህን? እነዚያ መልካሞቻቸው በምድር ላይ የተፋጠነችላቸው ሕዝቦች ናቸው›› አሉ፡፡›› (ቡኻሪ 2336)፡፡



- «ለምድራዊ ዓለም እኔ ምን አስጨነቀኝ፡፡ እኔ እኮ በምድር ላይ ልክ ጉዞ ላይ እንዳለና ደክሞት በአንዲት ዛፍ ስር ካረፈ በኋላ ትቷት እንደሚሄድ ሰው ነው፡፡» (አት-ቲርሚዚይ 2377)፡፡

- በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ቤት ውስጥ እሳት ሳይነድ ወር ወይም ሁለት ወራት ወይም ሦስት ወራት ያልፉ ነበር፡፡ እሳት ሲባል ምግባቸውን የሚያበስሉበትን እሳት ነው፡፡ በእነዚህ ወቅቶች ውሃና ቴምር ብቻ ነበር የሚመገቡት፡፡ (ቡኻሪ 2428)፡፡ ምናልባትም ሆዳቸውን የሚሞሉበት የደረቀ ቴምር እንኳ አጥተው ርቧቸው የሚውሉበት ቀን ነበር፡፡ (ሙስሊም 2977)፡፡ እስከሞቱበት ዕለት ድረስ ለሶስት ተከታታይ ቀናት የስንዴ ዳቦ ጠግበው አልበሉም ነበር፡፡ አብዛኛው ዳቧቸው የሚሰራው ከገብስ ነበር፡፡ (ሙስሊም 2976)፡፡

> የኢስላም ነቢይ በምድር ላይ የሚኖራቸውን ቆይታ አንዲት ጥላ ያላትን ዛፍ በጉዞው ላይ አግኝቶ ከጸሐዩ ሙቀት እንደሚጠለልባትና ድካሙ ከለቀቀውና የጸሐይዋ ሙቀትም ሲቀዘቅዝ ትቷት እንደሚሄድ መንገደኛ ነው፡፡

## ቅንነት፡

- ቅንነት ከታላላቅና ከተከበሩ ስነ-ምግባራት መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ የሚፈጸመው መልካም ነገርን ለመመለስ ወይም በሁለት ወገኖች መካከል አስገዳጅ ቃል ኪዳን ከሌለ በሕይወት ውስጥ ትልቅ ክብርን ይጨምራል፡፡ በእርግጥ ይህ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ፈለግ ነበር፡፡ ለመልካም ውለታ ከእርሱ ይበልጥ ይመልሱ ነበር፡፡ ቃል-ኪዳኖችም ሆኑ ሰነዶች በዚህ ላይ ኖሩም አልኖሩም ምን ቸገረህ፡፡

- ክርስቲያኑ ንጉሥ ሄራቅላጦስ የመካ ከሐዲያንን የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) መገለጫ አስመልክቶ፣ ‹ቃሉን ያጥፋልን?› በማለት ሲጠይቃቸው፣ እነሱ የሰጡት መልስ፣ ‹በፍጹም› የሚል ነበር፡፡ እሱም፣ ‹መልዕክተኞች እንዲሁ ቃላቸውን አያጥፉም፡፡» ብሏቸዋል፡፡ (ቡኻሪ 7)፡፡

- ለመጀመሪያ ሚስታቸው ለኸዲጃህ ታላቅ ቅን ነበሩ፡፡ ክብራቸውን ይጠብቁላቸው ነበር፡፡ ለሚናዎቻቸው እውቅና ይሰጡ ነበር፡፡ ቤተሰቦቿንና ወዳጆቿን በማክበር የላቀ ትኩረት ይሰጡ ነበር፡፡

- የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)ሚስት ዓኢሻህ የአላህ መልዕክተኛ ከመላከቻው የመጀመሪያ ዘመናት አካባቢ ለሞተችው የመጀመሪያ ሚስታቸው ለኸዲጃህ የነበራቸውን ቅንነት ዓኢሻህ በወጉ ባታውቃትም እንዲህ በማለት ተርካለች፣ ‹የአላህ መልዕክተኛ በብዛት ያውሷት ነበር፡፡ ምናልባትም አንዲት ፍየል ካረዱ የተወሰነ አካሏን ይቆርጡና ለኸዲጃህ ወዳጆች ይልኩ ነበር፡፡ ምናልባትም ‹በምድር ላይ ከኸዲጃህ ሌላ ሴት የለችምን?» እላቸው ነበር፡፡ እሳቸውም፣ ‹በእርግጥ እሷ እንዲህ.... እንዲህ ... እንዲህ ነበረች፡፡› እያሉ መለያዋን ይዘረዝሩ ነበር፡፡» (ቡኻሪ 3607)፡፡

- ከእለታት አንድ ቀን የነጃሺ (በእስልምና የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ሙሰሊሞችን ይደርስባቸው ከነበረው ጭቆና ከለላ በመስጠት የታደገ የሐበሻ ንጉሥ ነው) ዘንድ ልዑካኖች እሳቸው ዘንድ መጡ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከተቀመጡበት በመነሳት ራሳቸው ያስተናግዷቸው ጀመር፡፡ ይህን ጊዜ ባልደረቦቻቸው፣ ‹እኛ እንበቃዎታለን› ሲሏቸው፡፡ እሳቸውም፣ ‹እነሱ ባልደረቦቼን አክባሪዎች ነበሩ፡፡ ስለዚህ ውለታቸውን ልመልስ እወዳለሁ፡፡› አሉ፡፡ (ሹዐቡ-ል- ኢማን 8704)፡፡

ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የአላህን ትዕዛዝ ለመፈጸም፣ ከእሳቸው በፊት የነበሩትን የቀደምት ነቢያትን ፈለግ ለመከተል ሲሉ በርካታ ወደር የማይገኝላቸውን ታላላቅ ስብእናዎችንና መልካም ተምሳሌቶችን አስቀምጠዋል፡፡

መዲና ወይም ሙስሊሞች መዲቱ-ልሙነወራህ በሚጠሯት ከተማ ውስጥ ነቢዩ ሙሐመድ የገነቡት መስጂድ በአንገብጋቢነቱ ከመካ በመቀጠል ሁለተኛው ቅዱስ ሰፍራ ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ ወደዚህ ስፍራ ተሰደዋል፡፡ በውስጧም መስጂዳቸውን ገንብተዋል፤ እዚያው ተቀብረዋልም፡፡ በየአመቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ይህን መስጂድ ይጎበኙታል፡፡



# ከሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግሮች መካከል





## ሙስሊሞች

ሙስሊሞች የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ንግግሮች በማዳመጥና በመጻፍ፣ ሙሰሊም ምሁራንም ጥንቃቄ የተሞላበት እርማት በማድረግና በማብራራት እንደተጠበቀ ለትውልድ እንዲተላለፍ ከማድረጋቸው ባሻገር ለዓለም የዘመናዊ ምርምር ስርአትን አሳውቀዋል፡፡ በተለይ ንግግሮች በጽሑፍ ሲቀመጡ ከቃላት አንስቶ እስከ ሃሳብ እንዴት መሰደር እንዳለበት እንዲሁም ከንግግሮች መካከል በትክክል መስፈር ያለበትንና የሌለበትን ለይቶ የማውጣትን ጥበብ አሳውቀዋል፡፡

ከእነዚህ የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድ ከተናገሯቸው ነቢያዊ ንግግሮች መካከል ለአብነት የሚከተሉት ተቀምጠዋል፡

- ‹‹በእርግጥ ስራዎች በሙሉ የሚመነዱት በልበ-ውሳኔ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው በልቡ-በወሰነው በእርግጥ ይመነዳል፡፡›› (ቡኻሪ 1)፡፡
- ‹‹መልካም ነገር ማለት ስነ-ምግባር ነው፡፡ ሐጢአት ደግሞ በውስጥህ ኖሮ ሰዎች እንዳይመለከቱት የምትጠላው ነገር ነው፡፡›› (ሙስሊም 2553)፡፡
- ‹‹የትም ቦታ ሆነህ አላህን ፍራ፡፡ ከመጥፎ ስራ በኋላ መልካም ስራ አስከትል፡፡ እሷ መጥፎ ስራውን ታጠፋለችና፡፡ ሰዎችንም በመልካም ስነ-ምግባር ተኳዳኝ፡፡›› (አት-ቲርሚዚይ 1987).
- ‹‹ለዚህች ምድር ደንታ የሌለህ ሁን አላህ ይወድሃል፡፡ በሰዎች እጅ ላይ ባለ ነገር ላይ ደንታ የሌለህ ሁን ሰዎች ይወዱሃል፡፡›› (ኢብን ማጀህ 4102)፡፡
- ‹‹የእኔና ከእኔ በፊት የነበሩት ነቢያት ምሳሌ ልክ አንድ ቤት ሕንጻ አሳምሮ ገንብቶ አንዲት ጥግ ላይ አንዲት ሸክላ እንደተወና ሰዎችም ቤቱን እየዞሩ ከተመለከቱ በኋላ ምናለ ያችን ሸክላ ብታስቀምጣት! እንደሚሉት ሰው ነው፡፡ እኔ ሸክላዋ ነኝ፡፡ እኔም የነቢያት መደምደሚያ ነኝ፡፡›› (ቡኻሪ 3342)፡፡



«እስካላመናችሁ ድረስ ገነት አትገቡም፡፡ ፈጽሞ አታምኑም እስካልተዋደዳችሁ ድረስ፡፡ ከፈጸማችሁት ጀነት የሚያስገባችሁን ነገር ልንገራችሁን? በመካከላችሁ ሰላምታን አሰፍኑ፡፡» (ሙስሊም 54)

- «ከአንድ አማኝ አንዳች ምድራዊ ጭንቅን ያስወገደ አላህ በትንሳኤ ቀን ጭንቀቶቹን ያስወግድለታል፡፡ ለተቸገረ ሰው ነገርን ቀላል ላደረገ አላህ በምድርም በመጪው ዓለምም ያሉትን ነገሮች ቀላል ያደርግለታል፡፡ አንድ ሙስሊምን ከነውሩ የሸፈነ አላህም በምድርና በመጪው ዓለም ነውሩን ይሸፍንለታል፡፡ አንድ ሰው በወንድሙ እገዛ ላይ እስካለ ድረስ አላህ በባሪያው እገዛ ላይ አለ፡፡ እውቀት ለመፈለግ ጉዞ ለጀመረ አላህ ወደገነት የሚወስደውን መንገድ ገር ያደርግለታል፡፡ ... ተግባሩ የዘገየበት ድርሻው አይቸኩልለትም፡፡» (ሙሰሊም 2699)፡፡

- «ማናችሁም ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ አያምንም፡፡» (ቡኻሪ 13)፡፡.

- «ሙሰሊም ማለት ሙሰሊሞችን ከምላሱና ከእጁ የጠበቀ ነው፡፡ ተከልካይ ማለት አላህ ከከለከለው ነገር የሚርቅ ነው፡፡» (ቡኻሪ 10)፡፡

- «አዋጅ! ሙስሊመ ያልሆነን የበደለ ወይም ካቅሙ በላይ ያዘዘ ወይም ሳይፈልገው አንዳች ነገር የወሰደበት እኔ በትንሳኤ እለት ተሟጋቹ ነኝ፡፡» (አቡ ዳዉድ 3052)

- «ለአዛኞች እጅግ በጣም ሩሕሩሕ የሆነው ጌታ ያዝንላቸዋል፡፡ በምድር ላይ ላሉት እዘኑ በሰማይ ያለው ያዝንላችኋል፡፡» (አቡ ዳዉድ 4941)፡፡

- «ያታለለ ከእኛ አይደለም፡፡» (አት-ቲርሚዚይ 1315)፡፡

- «የአማኞች ውዴታቸው፣ እዝነታቸውና ችሮታቸው ምሳሌ ልክ እንደ አንድ አካል ነው፡፡ ይኸውም አንዱ ኣከል ሲታመም ሌሎቹ አካላት በሙሉ እንቅልፍ በማጣትና በትኩሳት እንደሚያሳልፉት ነው፡፡» (ሙስሊም 2586)፡፡



«ለትንሻችን የማያዝን፣ የታላቃችንንም መብት የማያውቅ ከእኛ አይደለም፡፡» (አት-ቲርሚዚይ 1920)፡፡

- «ሁላችሁም እረኞች ናችሁ ሁላችሁም ተጠያቂዎች ናችሁ፡፡ መሪ እረኛ ነው እርሱም ተጠያቂ ነው፡፡ አንድ ሰው በቤተሰቡ ላይ እረኛ ነው፡፡ እሱም ተጠያቂ ነው፡፡ አንዲት ሚስት በባሏ ቤት ላይ እረኛ ነች፡፡ እሷም ተጠያቂ ነች፡፡ ሁላችሁም እረኞች ናችሁ፤ ሁላችም ተጠያቂዎች ናችሁ፡፡» (ቡኻሪ 4892)፡፡
- «ምሉእ አማኝ ማለት መልካም ስነ-ምግባር ያለው ነው፡፡ ከእናንተ መካከል መልካማችሁ ለሴቶቻቸው (ሚስቶቻቸው) መልካም የሆኑት ናቸው፡፡» (አት-ቲርሚዚይ 1162)
- «ከእናንተ መካከል መልካማችሁ ለቤተሰቡ መልካም የሆነ ነው፡፡ እኔ ለቤተሰቤ ከናንተ በላይ መልካማችሁ ነኝ፡፡» (አት-ቲርሚዚይ 3895)፡፡

- ‹‹አላህ በሁሉም ነገሮች ላይ ርህራሄን ይወዳል፡፡›› (ቡኻሪ 5678)

- እንዲህም ብለዋል፣ ‹‹ርህራሄን የሚከለክል መልካም ነገርን ይከለከላል፡፡›› (ሙስሊም 2592)፡፡

- ‹‹የመናፍቅ ሰው ምልክቶች ሶስት ናቸው፡፡ ሲናገር ይዋሻል፡፡ ቃል ከገባ ቃሉን ያጥፋል፡፡ አደራ ከተባለ ይክዳል፡፡›› (ቡኻሪ 33)፡፡

- ‹‹የአንድ ሰው የእስልምናው መልካምነቱ የማይመለከተውን መተዉ ነው፡፡›› (አት-ቲርሚዚይ 2317)፡፡

- ‹‹አንድ ሰው መንገድ ላይ ሳለ ጥም በረታበት፡፡ ምንጭ አገኘና ወደርሷ ወርዶ ውሃ ጠጥቶ ወጣ፡፡ ሲያማትርም አንድ ውሻ በጥም ምክንያት እያለከለከ መሬት ሲልስ ተመለከተ፡፡ ‹ይህ ውሻ እኔ የደረሰብኝ ጥም ደርሶበታል› አለና ዳግመኛ ወደ ምንጬ ወርዶ በጫማው ውሃ ከቀዳ በኋላ ውሻውን አጠጣው፡፡ አላህም ሰውየውን አመሰገነውና ማረው፡፡›› አሉ፡፡ ባልደረቦቻቸውም፣ ‹የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በእንስሶቻችን ምንዳ አለን?› በማለት ጠየቋቸው፡፡ እሳቸውም፣ ‹‹እርጥበት በነካት የውስጥ አካል ሁሉ ምንዳ አለ›› አሉ፡፡ (ቡኻሪ 2466)፡፡



## የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ቁርአን የገለጻቸው እንዴት ነው?

ቁርአን የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) አስደናቂ ስብእናና በዙሪያቸው ከሚኖሩ ሰዎች ጋር የነበራቸውን መልካም ግንኙነት ይገልጽልናል፡፡ በዚህም መልካም ስነ-ምግባራቸውን፣ ስብእናቸውንና ገድላቸውን በአንድ ላይ ይፋ አድርጓል፡፡

- እሳቸው ለሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን ለዓለማትም እዝነት ናቸው (21፡107)፡፡
- በላቀ ስነ-ምግባር ላይ ያሉ ናቸው (68፡4)፡፡

- የእሳቸው ሃላፊነት ጥሪውንና መልዕክቱን ማዳረስ ብቻ እንደሆነና አላህም የሚፈልገውን ሰው ወደ ቀናው መንገድ እንደሚመራ በተደጋጋሚ በቁርኣን ላይ ቢያረጋግጥም ሰዎች ቀናውን መንገድ ይከተሉ ዘንድ ዘውትር ይጨነቁ ነበር፡፡ ሰዎች ቀናውን መንገድ ሲስቱ በጣም ያዝኑ ነበር፡፡(11፡12፣ 6፡107፣ 18፡ 127)፡፡
- ሰዎች ለሌሎች ይቅር እንዲሉና ስህተቶቻቸውንም እንዲያልፉ አደራ ይሉ ነበር (9፡43)፡፡
- እስከሚከለከሉ ድረስ ለጠላቶቻቸው ምህረት ይጠይቁ ነበር (9፡80)፡፡
- በአማኞች ላይ የሚከብድ ነገር ሁሉ በርሳቸውም ላይ ይከብድ ነበር፡፡ እሳቸው ለአማኞች ቸርና አዛኝ ነበሩ (9፡128)፡፡
- ምናልባትም አንዳንድ ሰዎች እሳቸው ቤት ውስጥ መቆየት ሲያበዙ ይጎዱ ነበር፡፡ ይህን ጉዳታቸውን ግን ለሰዎቹ ካላቸው መተናነስ የተነሳ ሊነግሯቸው አይፈልጉም ነበር (33፡53)፡፡
- ልበ- ለስላሳና ቀለል ያሉ ነበሩ፡፡ ባልደረቦቻቸውን በለዘብታ ይጎዳኙ፣ ያማክሩ እንዲሁም በአንገብጋቢ ክስተቶችና ጊዜያት ሃሳቦቻቸውን ይቀበሉ ነበር (3፡159)

# ቁርኣን ዘላለማዊ
# የእስልምና
# ትእምር





በዓለም ላይ በብዛት የሚሸጠውና የሚከፋፈለው ከአንድ ነጥብ አምስት ቢሊየን በላይ ሰዎች የሚያምኑበት መጽሐፍ ቁርአን ምንድን ነው?

## ቁርአን የሙስሊሞች ቅዱስ መጽሐፍ ሲሆን እሱም፣

- ለሰዎች መመሪያና ብርሃን ይሆን ዘንድ አላህ በመልዕክተኛው ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የተወረደ የአላህ ንግግር ነው፡፡
- የቀደምት መለኮታዊ መጽሐፍት መደምደሚያ፣
- ከመበረዝና ከመደለዝ የተጠበቀ የሆነ፣
- እሱን ማንበብ፣ በቃል ማጥናት፣ ሕግጋቱንና ድንጋጌዎቹን ተግባራዊ ማድረጋቸው እንደአምልኮታዊ ነው ብለው የሚያምኑበት የሆነ መጽሐፍ ነው፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) 40 ዓመት ከሞላቸው በኋላ በመልአኩ ጅብሪል (ዐ.ሰ) አማካኝነት ቁርአን መውረድ ጀመረ፡፡ በመጀመሪያ የወረደችው አንቀጽ «አንብብ፣ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም፡፡» የሚለው ሲሆን በክስተቶችና በአጋጣሚዎች ሳቢያ ለ23 ዓመታት በተለያዩ ጊዜያት ወርዷል፡፡

ቁርአን በ114 ምዕራፎች ሲከፋፈል የእነዚህ ምዕራፎች ርዕሰ ጉዳይና የአቀራረብ ስልት ይለያያል፡፡ ሆኖም ግን በቋንቋ ጥበብ፣ ምጥቀት፣ አጠቃቀምና የዐረብኛ ሰዋሰው አሰካክ ሁሉም በአብዛኛው ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ሁሉም የሰው ልጆችን ወደ ቀጥተኛው መንገድና አላህ በብቸኝነት ይጣራሉ፡፡

> ከቁርአን በመጀመሪያ የተወረደው አንቀጽ፤ [አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም፡፡] የሚለው ነው፡፡ ቁርአን ከአጋጣሚዎችና ከክስተቶች አንጻር ለ23 አመታት በተለያየ ጊዜ ወርዷል፡፡

## ቁርአን ከሚዳስሳቸው ዋና ዋና ምህዋሮች በከፊል

1. የአላህን ብቸኝነት ማረጋገጥና አምልኮ አጋሪዎች የሚያቀርቡትን ማስመሰያዎች ማዋደቅ፡፡
2. የነቢያትና የቀደምት ሕዝቦች ታሪክ መተረክ
3. ሰፊ የሆነውን ፍጥረተ-ዓለም ወደማስተንተንና በዙሪያችን የሚገኙ ፍጥረታትን ወደመመልከትና አላህ የለገሰንን ጸጋዎች መጠን ወደመቁጠር ሰዎችን መጥራት፡፡
4. የሃይማኖት ትዕዛዞችን፣ ክልከላዎችንና ድንጋጌዎችን ማብራራት፡፡
5. የአማኞችን ባህሪያትና ስነ-ምግባራት መግለጽና ከእኩይ ስነ-ምግባራት ማስጠንቀቅ፡፡
6. ስለመጨረሻው ቀን፣ በዚያ ቀን ለመልካምና ለመጥፎ ሰዎች ስለሚኖረው የምንዳ አሰጣጥ ሂደት መናገር፡፡
7. በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ በሚደርሱ ክስተቶች አማኞች እውቀት እንዲቀስሙ ማድረግ፡፡

የሚከተሉት ከቁርአን መለያዎችና መገለጫዎች ናሙናዎች ናቸው ፡፡





## ተጠብቆ የመኖሩ ተአምር

አላህ የመጨረሻውን መለኮታዊ መጽሐፍ ቁርአን ብሎ የሰየመው በልቦና ውስጥ እንደሚነበብ ለማመልከት ነው፡፡ በብዙ ቦታዎች ላይ መጽሐፍ ብሎ የሰየመው እንደሚጻፍና በመጽሐፍ መልክ ተዘጋጅቶ እንደሚጠበቅ ለማመልከት ነው፡፡ ቁርአን በሁለቱም መንገዶች ተጠብቋል፡፡ በእሳቸው ላይ ማንኛውም አንቀጽ ከወረደ እሳቸው ፊት ይጻፋል፣ ከእሳቸው አንደበትም ይጠናል፡፡ በቃል ያጠኑ ሰዎች ቁጥር ምንም ያህል ቢበዛም በቃላቸው ያጠኑት በጽሑፍ ከሰፈረው ጋር እንዲሁም የተጻፈው ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አንደበት ላይ በቃል ከተጠናው ጋር እስካልተመሳሰለ ድረስ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

የክርስትና እምነት ምሁራን በወንጌል ውስጥ የተፈጠረው ግጭት ቀድሞውኑ ሊከሰቱ እንደሚችሉ የሚጠበቅ ነበር ምክንያቱም ወንጌልን የጻፉት ጸሐፊያን ቁጥር በርካታና ታሪካቸውም የተለያየ እንዲሁም የመለኮታዊው ርእይ በተዘዋዋሪ ለጸሐፍቱ የደረሰ ነው በማለት ማረጋገጫ ይሰጣሉ፡፡ እንደ እነሱ አስተያየት ይህ መጽሐፍ በውስጡ ለሰው ልጆች መመሪያን ይዟል፡፡

እውነታው ግን ፍትሐዊ የሆነ አንባቢ ቁርአን ሲያነብ በቁርኣን ውስጥ ምንም ዓይነት የሀሳብ መጋጨት አሊያም መቃረን እንደሌለና ቁርአን ከዚህ ሁሉ ሙሉ ለሙሉ የጸዳ ነው ብለው ያረጋግጣሉ፡፡ ምክንያቱም ቁርአን ቃሉም ትርጉሙም ከአላህ ዘንድ የወረደ ነው፡፡ ከዚያ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንደበት በቃል እየተጠናና በጽሑፍ እየሰፈረ በጥንቃቄ ሊጠበቅ ችሏል፡፡ የአላህ መልዕክተኛም ልክ እንደወረደላቸው ምንም ሳይጨምሩና ሳይቀንሱ ለሌሎች ያስተምሩ ነበር፡፡ ሙስሊሞች ምንም ያህል በመካከላቸው የሃሳብና የአመለካከት ልዩነት ቢኖራቸውም ቁርአንን አስመልክቶ ግን በአንዲት ቃልም ቢሆን ፍጹም አይለያዩም፡፡

በታሪክ ሂደት የቁርአን አጠባበቅና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሽግግር በላቀ የአጠባበቅ ስርአት፣ እውቀት፣ ረቂቅ የአጻጻፍ ስልት፣ የአነባበብ ስርአት፣ በቃል ጥናት፣ በመጽሐፍ ላይ አቀማመጥ ደረጃ ተጠብቋል፡፡ አንዲት ፊደል ከእርሱ አይቀንስም፣ ከተቀመጠው ውጭ አንዲት አናባቢም በርሱ ላይ አይጨመርም፡፡ ከአንድ ሺህ ዓመት በፊት በእጅ ከተጻፈው የቁርአን ቅጽ ጋር ለማነጻጸር ማንኛውም ሰው አንድ የቁርአን ቅጽ ከቻይና አንስቶ እስከ መካከለኛው አፍሪካ ድረስ ቢገዛ ወይም ቤተ-መዘክሮች ውስጥ ካሉት ጋር ቢያነጻጽር አንዳች ግርምት ነገር ያገኛል፡፡ ይኸውም የቁርአኑ

የአነባብ ዘይቤ፣ የቃላቱ አሰካክ፣ የሰዋሰዉ አሰዳደርና ሌሎችም ከጊዜ ርዝማኔና በቋንቋ ልዩነት አንጻር ምንም ሳይቀየሩና ሳይለወጡ ያገኛቸዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ቁርአንን በቃሉ የሚያጠና አንድ ኢንዶኔዥያዊ ጩቅላ ወይም በማንኛውም እስላማዊ ሐገር የሚኖር ጩቅላ የሚያነበው የቁርአን አቀራር ከአንድ ሺህ ዓመት በፊት መካ ላይ ሲሰጥ ከነበረው የቁርአን ትምህርት ጋር ፍጹም ልዩነት የለውም፡፡ በቁርአን ላይ እንዲህ የሚል ሰፍሯል፤ «ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ በርሱ ውስጥ ብዙን መለያየት ባገኙ ነበር፡፡» (አን-ኒሳእ ፡ 82)፣ «እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡» (አል-ሒጅር ፡ 9)



## አገላለጻዊና መንፈሳዊ ተአምር

ቁርአንን በጥሞና የሚያነብ ሰው በቀጥታ እሱንና ስብእናውን እንደሚያናግር፣ ውይይቱና ፊት ለፊት መነጋገሩ በቶሎ እንደማያቆም ይረዳል፡፡ ከዚህ በላይ በጣም የሚደንቀው ቁርአን የእሱን (የአንባቢውን) ሃሳብ እንደሚቀድምና ሳያነበው በፊት ሃሳቡን ግልጽ እንደሚያደርግለት ማግኘቱ ነው፡፡

አንድ ሰዓሊ ዓይንን ምናልባት ተመልካቹ የትም ቢሄድ እንደምትመለከተው አድርጎ ሊስል ይችል ይሆናል፡፡ በጽሑፍ ግን እንዴት ሆኖ ነው የአንባቢውን አስተሳሰብ ሊከተል የሚችለው፣ የአንባቢያኑ ባህልና ወግ እንዲሁም የአኗኗር ሁኔታ መለዋወጥ እንዳለ ሆኖ አንባቢው በግልጽ ሳያነሳቸው በፊት አስቀድሞ ወደፊት ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጠው!

ቁርአን የዚህ ስልት ባለቤት ከመሆኑ ሌላ ይህን ስልት በሚገርም ሁኔታ የሰው ልጅን ዝንባሌ፣ ምስጢር፣ ደካማነት ለመመርመር ይጠቀምበታል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን የሚያነብ ማንኛውም ሰው ግር ሊሰኝ ይችል ይሆናል፡፡ ይህ የሚሆነው ግን አእምሮንና ውስጣዊ ማንነትን ለማንቀሳቀስና ጥያቄዎችን አንስቶ ምላሽ እንዲያገኝ ለማድረግ እንጂ ለሌላ ዓላማ አይደለም፡፡

ከመካከላችን አንዱ ቁርኣንን በሚያነብበት ጊዜ የተለያዩ ሰዎችን ታሪክና መገለጫዎች ያወቃል፡፡ ከአስተሳሰባቸው ምስጢሮች፣ ከነፍሳዊ ፍላጎቶቻቸው፣ ከጅማሮዎቻቸው መነሻ ነጥብ፣ ከጥመታቸውና ከስኬታቸው ጋርም ይኖራል፡፡ ላፍታ ከራሱ ጋር አዛምዶ ያብሰለስላል፡፡ ቀስ በቀስም እነዚያ ታሪኮችና ተምሳሌቶች ቁርአን ለራስ መስታወት እስኪሆን፣ እውነታውንና እንከኑን እስኪያወጣ ድረስ ስሜትን ምንም ሳይነኩ ወደ አንባቢው ልቦና

ይቀርባሉ፡፡ ከዚያ በኋላ የአንባቢው ነፍስ ቁርኣንን በጥልቅ እያወቀ በመምጣት በእርግጥ ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው አምላክ እንደሌለ ያረጋግጣል፡፡

አንባቢው ጭንቀትና ተስፋ መቁረጥ ሲያካብበው ፣ «በላቸው፡- እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ፤ አላህ ኃጢአትን በመላ ይምራልና እነሆ እርሱ መሓሪውና አዛኙ ነውና፡፡» (39፡53)

አንድ ሰው አንድ ነገር ለመስራት ግራ በተጋባ ወይም ከፍተኛ የሆነ ውስጣዊ ትግል ሲሰማው በእርሱ ላይ የሚመካበትንና ወደርሱ የሚጠጋበትን አካል ይፈልጋል፡፡ ቸርነትን በዚህ የአላህ ቃል ውስጥ ያገኛል፡- « ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው)፡- እኔ ቅርብ ነኝ፡፡ የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ፡፡ ስለዚህ ለኔ ይታዘዙ፤ በኔም ይመኑ፤ እነሱ ሊመሩ ይከጀላልና፡፡» (አል-በቀራህ ፡ 186)

ማንኛውም ሰው ሕይወቱ ከተቀመጠላት ወሰን ማለፏን ሲያስብና ይህን ለመሸከምና ለመቆጣጠር ሲያቅተው ከዚህ ሁሉ ሊያድነው የሚያስችል መድሃኒት፣ ቋሚ የሆነ አጋዡን በቁርአን ውስጥ በሰፈረው የአላህ ቃል ውስጥ ያገኛል፡፡ ((አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም፡፡ ለርስዋ የሠራችው አላት፡፡ በርስዋም ላይ ያፈራችው (ኀጢአት) አለባት፡፡ (በሉ)፡- ጌታችን ሆይ! ብንረሳ ወይም ብንስት አትያዘን፤ (አትቅጣን)፡፡ ጌታችን ሆይ! ከባድ ሸክምን ከእኛ በፊት በነበሩት ላይ እንደጫንከው በእኛ ላይ አትጫንብን፡፡ ጌታችን ሆይ! ለኛም በርሱ ችሎታ የሌለንን ነገር አታሸክመን፡፡ ከእኛም ይቅርታ አድርግ ለእኛም ምሕረት አድርግ፡፡ እዘንልንም፤ ዋቢያችን አንተ ነህና፡፡ በከሓዲዎች ሕዝቦች ላይም እርዳን፡፡)) ( አል-በቀራህ ፡ 286)

በስልጣኔ ላይ ከሚጽፉ የታሪክ ሰዎች አንዱ ሆነው ዌል ዱራንት ቁርአን ለለው ተጽእኖና በሁሉም ሰዎች ዘንድ ላለው የላቀ ስፍራ እውቅና ሰጥቷል እንዲህም ብሏል፤

‹‹በእርግጥ ባለፉት ዘመናት ውስጥ የነበሩና በአሁኑ ዘመን ላይ ያሉ ምሁራንና የአስተሳሰብ መሪዎች በቁርአን አምነዋል፡፡ በአስተሳሰባቸውና በአመለካከታቸው በሰፋት የተለያዩ የሆኑ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች ሳይቀሩ በቁርአን አምነዋል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው ቁርአን ግልጽ፣ ትክክለኛና ሰዎች ሊቀበሉት የሚችሉት እምነት ይዞ ስለመጣ ነው፡፡ እምነቶቹ በጣም ቀላል፣ ከአምልኮዎች ጋር የተጣመሩ፣ ድብቅ የሆኑት ቀጥራቸው አናሳ የሆነ፣ አብዛኛዎቹ ከጣኦተኛነትና ከአማልክትነት ነጻ የሆኑ ናቸው፡፡ እስልምና የሰው ልጆች የሕይወትን ከባድነት ሳይማርሩና ሳይሰለቹ እንዲጋፈጡ፣ እስራቷንም እንዲችሉ አስተምሯል፡፡ ሃይማኖቱን አሳውቋቸዋል፡፡ ወሰኑንም ወስኖላቸዋል፡፡ ትክክለኛ የሆነ ክርስቲያንም ሆነ አይሁድ ትክክለኛ እምነት ከመቀበል የሚያግደው ነገር የለም፡፡ ‹‹*መልካም ሥራ፥ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፤ ግን መልካም ሥራ፥ በአላህና በመጨረሻው ቀን፥ በመላእክትም፥በመጽሐፍትም፥ በነቢያትም ያመነ ሰው፥ ገንዘብንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች -(አባታቸው የሞተባቸው ሕጻናት)- ፥ለምስኪኖችም፥ ለመንገደኞችም፥ ለለማኞችም፥ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቅ) የሰጠ ሰውና ሶላትንም ደንቡን ጠብቆ የሰገደ፥ ዘካንም የሰጠ፥ ቃል ኪዳንም በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች ሥራ) ነው፤ በችግር በበሺታና በጦር ጊዜም ታጋሾችን (እናወድሳለን)፤ እነዚህ እውነትን የያዙ ናቸው፤ እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡›› (2፡ 177)፡፡››* Story of Civilization ቅጽ ፡ 13 ገጽ ፡ 68-69

ዌል ዱራንት እንዲህ ብሏል፤

“በርካታ ምሁራንና የአስተሳሰብ ልሂቃን እንደአእምሮዎቻቸውና አስተሳሰብ እድል መለያየት ሆኖ በቁርአን አምነዋል፡፡ ይህ ሁሉም ሊቀበለው ከሚችለው እውነተኛ እምነት የመጣ ቢሆን እንጂ በሌላ አይደለም፡፡ እምነቶቹ እጅግ ቀላልና ግልጽ ያልሆነው ደግሞ እጅግ ጥቂት ነው፡፡”

# ቁርአን ከየት ነው የመጣው?





ስለሙስሊሞች ቅዱስ መጽሐፍ ቁርኣንና ስለሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አንዳች ነገር ሲነገረን በቀጥታ በአእምሯችን ውስጥ የሚነሳ ሎጂካዊ ጥያቄ አለ፡፡ ይኸውም ሙስሊሞች ይህን አስመልክተው ሲናገሩ ለምን ዝም ብለን እንቀበላቸዋለን? በእነርሱ ዙርያ ጥያቄዎችን መጠየቅ የለብንምን? የሚለው ነው፡፡



የታሪክ ዘጋቢዎች ቁርአን በስድስተኛው ክፍለ-ዘመን መካ ውስጥ በተወለደ፣ ስሙ ሙሐመድ የአብደላህ ልጅ በተሰኘና ማንበብና መጻፍ በማይችል ዓረብ ሰው ላይ እንደወረደ ካለልዩነት የሚስማሙበትና በተለያየ ጊዜ የመጣ በመሆኑ ላይ ምስክርነታቸው የሚያረጋግጡበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህን እውነታ ቁርኣንን በጥሞና ስናነብ የእሳቸው ቃል ሳይሆን በእሳቸው ላይ የተወረደ የአላህ ቃል እንደሆነ በግልጽ እንረዳለን፡፡ የሙሐመድ ተግባርና ተልእኮ ሳይቀንሱና ሳይጨምሩ እንዳለ እሱን ለሰዎች ማስተላለፍ፣ ማብራራትና ግልጽ ማድረግ ነው፡፡

የእስልምና መልዕክተኛ የሆኑት ሙሐመድ በእርግጥ ከራሳቸው ፈጥረው የጻፉት ወይም ቀድሞውኑ ከሌሎች የቀሰሙትን ትምህርት በሌላ አገላለጽ ቀይረውና አሻሽለው ለሰዎች ያቀረቡት ነው ተብሎ ሊነገር የሚችል ነውን?

እንደዚህ ዓይነቶቹ ጥያቄዎች ቁርአንን አንብቦ በማያውቅ፣የሙሐመድን የሕይወት ታሪክ ባላጠናና አዋቂ ባልሆነ ሰው አእምሮ ውስጥ ቶሎ የሚፈጠሩ የተለመዱ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

> *የኢስላም መልእክተኛ ማጭበርበር ቢፈልግ ኖሮ ንግግሮቹን ወደአላህ በማዞር በሰዎች ላይ ያለውን ስልጣን በዘረጋ ነበር፡፡ ታዲያ ለምንድነው ንግግሮቹ ሁሉ ከአላህ ዘንድ እንደሆኑ ያልተናገረው?*

ሁላችንም እንደምናውቀውና ታሪክም በብዙ አጋጣሚዎች የሚያረጋግጠው እውነታ በርካታ የሥነ-ጽሑፍ ሰዎች የሌሎችን ሥራዎች በመስረቅ እንደራሳቸው ሥራዎች አድርገው ያቀርቡ እንደነበር ነው፡፡ ለምንድን ነው አንድ ሰው የራሱ አእምሮ ውጤት የሆነውን ለሌሎች ማቅረብ የማይፈልገው?

ጥያቄ የሚያስነሳው ነገር አንድ ሰው በእርግጥ ማታለል ቢፈልግ ኖሮ ከአላህ ዘንድ የመጣ ከመሆኑ የተነሳ ከቁርአን የወሰደውን ሃሳብ የራሱ እንደሆነ በማቅረብ በሰዎች ላይ ጫናውን ባሳረፈ ነበር፡፡ ግን ከሰው አእምሮ የሚወጣ አይደለም ለምንድን ነው ግን ሁሉም ንግግሩ ከአላህ እንደመጣ አያከራክርም የሚባለው?

በመጽሐፉ ውስጥ በበርካታ ቦታዎች ላይ ተናጋሪው ሙሐመድን በቀጥታ ጠቅሷቸው፣መመሪያ ስጥቷቸውና ስህተቶቻቸውን አርሞላቸው እያየን፣ሙሐመድ ይህን መጽሐፍ ራሳቸው ናቸው የጻፉት፣ያዘጋጁት፣በሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘትና ክብሩም ከፍ ይል ዘንድ ፈልገው ያዘጋጁት ነው ተብሎ ሲነገር በእውነት አእምሮ የሚቀበለው ነገር ነውን?

-ያነበበው ሰው እንደሚያውቀው- በተለየ አጋጣሚም ይሁን በአጠቃላይ፣ በነቢዩ ግላዊ ሕይወትም ይሁን በሌላ ክስተት እንዲሁም የአመራር ውሳኔያቸውም ሆነ ሰዎችን ወደ እስልምና በሚጠሩበት ስልት ዘዴ) ላይ አንዳች ስህተት ከተፈጸመ ቁርአን እሳቸውን ከመምከርና ከመገሰጽ ወደኋላ አይልም፡፡

ለአብነት ያህልም  አንድ ቀን ከሙሐመድ (ሰ.0.ወ) ባልደረቦች መካከል አንድ ዓይነ-ስውር እሳቸው ሙስሊም ያልሆኑ የቁረይሽ ጎሳ ባላባት አንዱ የሆነውን ሰው ወደእስልምና በመጥራት ላይ  በነበሩበት ወቅት ወደእሳቸው ዘንድ መጣ፡፡ይህ ዓይነ-ስውር ሙሐመድ (ሰ.0.ወ) በእንዲህ ሁኔታ ላይ እንደሆኑ ስላላወቀ፣ ‹አላህ ካሳወቅዎ እውቀት ያሳውቁኝ!›› በማለት ወተወታቸው፡፡ እየደጋገመም ጠየቃቸው፡፡ ይህን ጊዜ እሳቸው በሁኔታው ስለተበሳጩ በንዴት ፊታቸውን አጨፈገጉ፡፡  ምንም ምላሽ ሳይሰጡት ፊታቸውን ከዓይነ-ስውሩ ዘወር አደረጉ፡፡ ቁርአን ይህን ድርጊት ዘግቦ አስቀመጠው፡፡ ሙሐመድ (ሰ.0.ወ) እንዴት አድርገው ፊታቸው እንዳጨፈገጉና ለዓይነ-ስውሩ ምንም ምላሽ ያለመስጠታቸውን ጭምር ሳይቀር ክስተቱን በግልጽ አስቀመጠው፡፡ በዚህ ብቻም አልተገደበም ክስተቱን ከገለጸ በኋላ እሳቸውን በመገሰጽና ዳግም ይህን መሰሉን ድርጊት መፈጸም  እንደሌለባቸው ክስተቱን በሚተርክ፣ በሚያረጋግጥና በድርጊታቸው በተሰየመ  (አንድ ሙሉ የቁርአን ምዕራፍ ውስጥ 80፡1-11) አስገነዘባቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ይህ ዓይነ-ስውር ወደእሳቸው ዘንድ ከመጣ የአላህ መልዕክተኛ፣ ‹‹በእሱ ምክንያት ጌታዬ የገሰጸኝ ሰው እንኳን ደህና መጣህ›› ካሉት በኋላ ሽማቸውን አንጥፈው ይቀበሉት ነበር፡፡

ስለመልእክተኛው ወቀሳ በርካታ ታሪኮችን ቁርአን አረጋግጦልናል፡፡ ለራሱ የላቀ ስፍራንና ክብርን ቢፈልግ ኖሮ ታዲያ አንድ ሰው የራሱን ስሕተቶች በታሪክ መዝገብ ውስጥ በእንዲህ ያለ ሁኔታ  ያሰፍራልን?

እንደዚሁ ታሪክ የሚያረጋግጥልን እውነታዊ ክስተት አለ፡፡ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መለኮታዊ ርእይ ወርዶ እውነተኛነታቸውንና ነቢይነታቸውን እንዲሁም የቤተሰባቸውን ከእኩይ ተግባር መጽዳት እንዲያረጋግጥላቸው የተመኙባቸው የጭንቅና የመከራ አጋጣሚዎች ያለፉባቸው ቢሆንም ለጥቂት ጊዜያት ቁርኣን ሳይወርድ የቀየባቸው አጋጣሚዎችም ነበሩ፡፡

ከእነዚህ አጋጣሚዎች መካከል ጠላቶቻቸው የነበሩ ሕዝቦች ብዙ ጉዳቶችንና መከራዎችን አድርሰውባቸዋል፡፡ ጥሪያቸውንም ለማብጠልጠል የቀደምት ሕዝቦችን መጽሐፍት ጠንቅቀው የሚያውቁ ምሁራንን እውቀቶችን ተጠቅመዋል፡፡

ምሁራኑም ‹ሶስት ጥያቄዎችን ጠይቁት፡፡ ሁሉንም ከመለሰላችሁ በእርግጥ እሱ ነቢይ ነው፡፡ ካልመለሰላችሁ ግን ነቢይ አይደለም› አሏቸው፡፡ ሰዎቹም ወደ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ሄደው ሶስቱንም ጥያቄዎች ጠየቋቸው፡፡ እሳቸውም፣ «ነገ እመልስላችኋለሁ» አሏቸው፡፡

> አንዳችን አንዳንድ ጊዜ እንደሚገሰጸው ቁርኣን በበርካታ ታሪኮች ላይ ለመልእክተኛው ማስተካከያዎችና ገሰጻዎች እንደተደፈጸመ አረጋግጦልናል፡፡

ይሁን እንጂ ለተወሰኑ ቀናት መለኮታዊው ርእይ ለሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሳይወርድላቸው ቀረ፡፡ ጥያቄያቸውን ባለመመለሳቸው ምክንያት ጠላቶቻቸው ወደእሳቸው በተደጋጋሚ እየመጡ ይሳለቁባቸው ነበር፡፡ ይህን ጊዜ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሃሳብ ገባቸው፡፡ መለኮታዊው ርእይ በቁርአን ውስጥ ሳይመጣ አስራ አምስት ቀናት አለፉ፡፡ ከአስራ አምስት ቀናት በኋላ ግን ቁርአን ለጥያቄዎቹ አጥጋቢ መልሶችንና ለሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መመሪያን ይዞ ወረደ፡፡ ‹‹የአላህን መሻት ከነገሩ ጋር ሳታስተሳስር እኔ ይህን ነገር ነገ እሰራለሁ ብለህ እርግጠኛ አትሁን፡፡ ያን ጊዜ በመልስህ ላይ አላህ ቢሻ ማለት ነበረብህ፡፡ ምላሽህ የዘገየበት ምክንያት አላህ ይህን ሊያስተምርህ ስለፈለገ ነው›› አላቸው (18፡24)፡፡



## ተደጋጋሚ ውንጀላዎች፡

የሚገርመው ከሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ገሃዳዊ የሕይወት ታሪክ ማስረጃዎች በመነሳት እውነተኛነታቸውን በቀላሉ ማረጋገጥ መቻሉ ነው፡፡

ምንም መጻፍና ማንበብ ከማይችል፣ በእለታዊ ግንኙነቶቹ በመሀይማን ሕዝቦች መካከል ከሚኖርና በስብሰባዎቻቸው ላይ ከሚገኝ፣ እለታዊ ሲሳዩን ለመፈለግ ከሚታትር፣ እየተከፈለው በጎችና ፍየሎችን ይጠብቅ ከነበረ፣ በሰው ገንዘብ ለሰው እየነገደ ይተዳደር ከነበረ፣ ከምሁራን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነትና ቁርኝት ካልነበረውና አርባ ዓመቱን በዚህ ሁኔታ ከገፋ ሰው  እንዴት ተብሎ አባቶቻቸውና አያቶቻቸው እንኳ ፈጽሞ የማያወቁትን ይህን ሁሉ እውቀት ለሰዎች በአንድ ጊዜ ያመጣላቸዋል? ያለፉትን ሕዝቦች ሁኔታ፣ የፍጥረተ-ዓለሙን አጠቃላይ ታሪኮች፣ የነቢያትን ዝርዝር የሕይወት ታሪክ እንዲሁም በእያንዳንዱ የሕይወት ዘርፍ ሊያስፈልጉ የሚችሉ እሴቶችን፣ ሕግጋትና ስርአቶችን በአንድ ጊዜ ሊነግራቸው  አእምሮ የሚቀበለው ነገር ነውን?

እንደነዚህ ያሉ እውነታዎች በጊዜያቸው የነበሩትን የሙሐመድ ጠላቶች በእጅጉ ከማስገረም አልፈው ዱብዳ ሆነውባቸዋል፡፡ የነበረውን ክስተት ለመናገር እስከሚያቅታቸው ድረስ አፋቸውን አዘግቷቸዋል፡፡ ታዲያ ሰዎችን ለማስጠንቀቅ የሚጋብዙት ሁኔታዎችና መሰረተ-ቢስ ውንጀላዎችን ለመሰንዘር የሚያስችሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

> ጉዳዩ እንግዲህ በአጠቃላይ ነቢያት ጋር በእነሱ ላይ ሰላም ይሁን  እንዲህ ነው፡፡ ጠላቶቻቸው እነሱ ላይ የሰነዘሩባቸው ውንጀላዎች ሁሉ ፈጽሞ አልተገኙም፡፡ ድግምተኞች ወይም እብዶች ብለውም ወንጅለዋቸዋል፡፡

ቁርኣን የሙሐመድ ፈጠራ ነው ብሎ መናገር እጅግ የሚከብድ ነው፡፡ ይህን ደግሞ ቁርአንን ያነበበ ሰው ያውቀዋል፡፡ ይገነዘበዋል፡፡ ሙሐመድ ከሌሎች የተማሩት ነገር ቢሆን ኖሮ እስከአሁን ድረስ ከኛ ጋር አብሮ ሊኖር አይችልም ነበር፡፡ የእሳቸውንም ዝርዝር የሕይወት ታሪክ አናውቅም ነበር፡፡ በማይሆንና እውነታውን በሚቃረን ነገር ወንጅለዋቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከእሳቸው በፊት ከነበሩት የገለበጡት ወይም የወሰዱት ነው ይሏቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከራሳቸው በልበ-ወለድ ፈጥረው የጻፉት ነው ይሏቸዋል፡፡ ሲላቸው ደግሞ በሕልማቸው ያዩዋቸውን ታሪኮች ነው የጻፉት ይሏቸዋል፡፡ እነዚህን መሰረተ-ቢስ ውንጀላዎች በማስረጃ ማሳመን ሲያቅታቸው፣ ድግምተኛ፣ ገጣሚ ወይም እብድ ነው ይሏቸዋል፡፡

ሰያሜዎቹ ይለያዩ እንጂ እነዚህ ክስተቶች በሌሎች ነቢያት ላይም ይለጠፉ ነበር፡፡ ለምሳሌ ነቢዩ ሙሴ (ዐ.ሰ) በድግምት እንዲሁም ኢየሱስ (ዐ.ሰ) በእብደት አልተወነጀሉምን?

ይህ መሰሉ ውንጀላ በአጠቃላይ በቀደምት ነቢያትም (ዐ.ሰ) የተፈጸመ ነው፡፡ ጠላቶቻቸው ማስረጃ አሰደግፈው ነቢያቱን መወንጀል ሲያቅታቸው ድግምተኞች ወይም እብዶች ናቸው ይሏቸዋል፡፡ ሐሰተኛ ምስክርነት የሚሰጥ ሰው ጠባይም እንደዚህ ነው፡፡ ለምስክርነቱ ማስረጃ ሲያጣ፣ ጭንቀት ሲሰማውና የሚያመልጥበት ዘዴ ሲጠፋበት ሊያመልጥበት ወደሚችላቸው አቅጣጫዎች መሯሯጡ አይቀርም፡፡ ምን ዓይነት መጥፎ ውርደት ነው!

## ለምን ነገሩን ተፈጥሯዊ ተሰጥኦ ነው አንልም?

አላህ በሰው ልጆች አእምሮ ላይ የማይቻል ነው ተብሎ የሚታሰብ ነገርን ሰዎች አእምሯቸውን በመጠቀም እንዲፈጥሩ የሚያስችል ልዩ ልዩ ችሎታዎችን እንደቸራቸው ሁላችንንም የሚያስማማ ነጥብ ነው፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ አእምሮ ምንም ዓይነት ችሎታ ቢኖረውም ለችሎታው ገደብ ተቀምጦለታል፡፡ የሰው ልጅ አእምሮ ሁሉን ቻይ ፈጣሪ እንዳለ ከመረዳቱ በተጨማሪ የዚህ ፈጣሪ ፍትሕ ከምድራዊ ሕይወት በኋላ ሁሉም ሰው መጥፎም ይሥራ መልካም የሥራውን ምንዳ በትክክል የሚያገኝበትን ዓለም እንዲኖር አድርጓል፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ ምንም ዓይነት ማስረጃዎች ሳይኖሩት እንዲያው በደፈናው በጣም ግኡዝ የሆኑ ሁኔታዎን ማረጋገጥና በስፋት ማወቅ ይቻለዋልን?

ቁርአንን የሚያነብ ሰው ቁርአን የእምነትን ወሰን እንዴት እንደሚያብራራልን፣ ፍጥረታት እንዴት እንደተፈጠሩና ፍጻሜያቸውም ምን እንደሚሆን ፣ ገነትንና ጸጋዎቿን፣ የገሃነምን አስከፊነትና ቅጣት፣ የበሮቿን ቁጥር፣ በርሷ ላይ የተሰየሙትን መልአክት እንዴት እንደሚገልጽልን፣ የፍጥረተ-ዓለሙንና የሰው ልጅን እውነታዎች በግልጽና በስፋት ያገኛል፡፡ ታዲያ ይህ ሁሉ ዝርዝር ዳሰሳና ዘገባ በየትኛው ረቂቅ አእምሮ ሃሳብ ላይ ነው የተመሰረተው?

ይህ ሁሉ እንግዲህ በተሰጥኦ ወይም በአእምሮ ምጥቀት አይገኝም፡፡ አይመጣም፡፡ ሐሰት ወይም ምናባዊ እውቀት የሚገኝ እውነታ ካልሆነ በስተቀር በሌላ የሚገኝ አይደለም፡፡



የዘመናችን ሳይንስ ካገኛቸው እውነታዎች ጋር ፍጹም ተቃርኖ የሌላቸውን መረጃዎች ቁርአን ውስጥ አግኝቷል፡፡ እንዲሁም በቀደምት ሰማያዊ መጽሐፍት ውስጥ ከተጠቀሱ ስውር ክስተቶች ጋር በትክክል ተስማምቷል፡፡

## ምናልባት አገላለጻቸው ላይ ለውጥ የተደረገባቸው መጽሐፍት ናቸው?

ላፍታ ቆም ብለን ብናስተነትን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በትንሹም ቢሆን መረጃዎችን ከቀደምት ነቢያት መጽሐፍት ሰብስበዋልን?

ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ምንም ማንበብና መጻፍ የማይችሉ መሐይም የሆኑ፣ ሕዝቦቻቸውም እንደሳቸው መሐይም ነበሩና እነዚህን እውቀቶች የሚያውቁበትና የሚያገኙበት ምንም ዘዴ አልነበራቸውም፡፡ እንዲሁም በጉዞ ላይ ካልሆነ በስተቀር እሳቸው (ሙሐመድ)ጋር ምንም ዓይነት ጉድኝት ያልነበራቸው ሰው ነበሩ የሚለውን እውነታ ብንተወው እንኳ በጊዜያቸው የነበሩ የቀደምት መለኮታዊ መጽሐፍት ባለቤቶች የነበራቸውን ክብርና የላቀ ስፍራ ላለማጣት እውነታውን ለሰዎች አውጥተው ከመናገር ይቆጠቡ እንደነበር ታሪክ ያረጋግጣል፡፡



ይህን ሁሉ ብንተወው እንኳ ቁርአንን ለሚያነብና ለሚያጠና ማንኛውም ሰው ቁርአን በቀደምት መለኮታዊ መጽሐፍት ውስጥ ከሰፈሩት ነገሮች ጋር ፈጽሞ እንደማይስማማና እንዲያውም (አንዳንድ የሃይማኖት ሰዎች የቀየሯቸውንና የበረዟቸውን) የተሳሳቱ አስተምህሮዎችና መረጃዎች ለማረም፣ ያልተሟሉ ከፊል ታሪኮችን ለማሟላት፣ ሰዎች ሲደብቋቸው የነበሩ እውነታዎችን ይፋ ለማውጣት፣ የተሳሳቱ እምነቶችንና አንዳንድ የሃይማኖት ሰዎች ከነቢያት ያስጠጓቸውን እኩይ ስነ-ምግባራትን ግልጽ ለማድረግ የመጣ መጽሐፍ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ቁርአን በዚህ ዓይነቶቹ ምሳሌዎች የተሞላ ነው፡፡ ከነዚህ አንጻር እንግዲህ ሙሐመድ መረጃዎቹን ከእነርሱ የወሰደ የእነዚህ ሰዎች ተማሪ ነበር ለማለት ያስደፍራልን?

## ልዩ የሆኑ ታሪካዊ እውነታዎች

Lፍትሐዊ አጥኚ (ተመራማሪ) የሆነ ሰው ብዙ የማይቆይበት ነጥብ የእስልምና መልዕክተኛ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አረብ አይደሉምን? የሚለው ነው፡፡

ጎሳዎቹ የነበሩት ዐረቦች በዚያ ወቅት ከርቱእ አንደበት በስተቀር አንዳችም ጥበብ እንዳልነበራቸውና የጥበብ ባለቤቶችም እንዳልነበሩ ታሪክ አልነገረንምን? በጊዜው የነበረው ስልጣኔ ስነ-ግጥምና ስነ-ጽሑፍ ነበር፡፡ ለዚህም ክበቦችንና ስብሰባዎችን ያዘጋጁ ነበር፡፡ በዚህ ትእይንትም አንዱ ጎሳ በእሱ ላይ ሌላው ጎሳ በተናገረው ይዋረዳል፡፡

የሥነ-ጽሑፍ ጥናትና እነዚሁ የታሪክ ድርሳናት እንደሚነግሩን ዓረቦች የጎደለውን የሚያሟሉለት፣ ያለፈውን የሚያመጡለት፣ ባቀረበው ስነ-ጥበብ ምላሽና ትችት የሚያቀርቡበት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው በዓረቦች ፊት ግጥምም ሆነ አንዳች ሥነ-ጽሑፋዊ ሥራ ፈጽሞ አያቀርብም ነበር፡፡ ታዲያ የዚያ ጊዜ ዓረቦች መታወቂያ፣ መገለጫና ጉልበት ይህ አልነበረምን!

የነርሱ አካል የነበረ፣ኋላ ላይ ግን በጠላትነት የፈረጁት ሰው ፈጽሞ የማይችሉትን ቁርአንን የመሰለ ካልቻሉ ከዚያ ያነስ ተመሳሳይ ነገር እንዲያመጡ ተፈታትኗቸዋል፡፡ ግና መሰሉን በማምጣት ለመፎካከር ፈጽሞ አልቻሉም፡፡ ሽንፈታቸውን በዝምታ ከመግለጽ ውጭ ያደረጉት ነገር አልነበረም፡፡

ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በዚህ ሁኔታ ዐረቦች ትንሹንም ሆነ ትልቁን ችሎታቸውን በማውጣት የቁርአንን ከንቱነትና ሐሰተኛነት ለሰዎች ለማስረገጥ በነጠላም ሆነ በቡድን እንዲፎካከሩ ሲያደርጉ ምንም ዓይነት ፍራቻ አልነበራቸውም፡፡

ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የሕዝቦቻቸውን ችሎታ ስለሚያውቁ እነሱን ለመፈታተን ይህን በጊዜው ፈጽመዋል ብለን ብናስብ ሊነሳ የሚችል ጥያቄ አለ፡፡ ይኸውም እስከትንሳኤ እለት ድረስ ያለው ትውልድ ሁሉ በአንድነት ቢሰባሰቡ እሱን (ቁርአንን የሚመስል) ወይም የእሱን ትንሽ ክፍል ማምጥት ይሳናቸዋል ብለው ፍርድ ሊሰጡ ይችላሉ? የሚለው ነው፡፡

በሚናገር ነገር ላይ የራስ መተማመንና ትምክህት ያለው ልቡ የተሞላ ጀግና ካልሆነ በስተቀር በዚህ ላይ ማንም አይጋፈጥም፡፡ ሁኔታውም እንዲህ ነበር፡፡ የቁረይሽ ጎሳ አባላትም ሆኑ አንደበተ ርቱእ ሰዎችን ቁርአንን የሚመስል አንዳች ንግግር ሊሰድሩ አልደፈሩም፡፡ እንኳን ሙሉን አይደለም ከፊሉንም ማምጣት አልቻሉም፡፡ ይህ ከዚያን ዘመን አንስቶ እስከአሁን ድረስ ያለ እውነታ ነው፡፡ በታሪክ ሂደት ይህን ዓይነት ሙከራ የሞከረ ወይም ለመሞከር ያሰበ አሳፋሪ ሽንፈትን ተከናንቧል፡፡ በሕዝቦቹ መካከልም መሳቂያና መሳለቂያ፣ የውርድትና የምሳሌያዊ አነጋገር ዘውግ ሆኗል፡፡

## የአል-ፋቲሐ ምዕራፍ

ይህች ምዕራፍ በቁርአን ውስጥ ትልቋ ምዕራፍ ስትሆን አንድ ሙስሊም በስግደቱ ውስጥ ሁልጊዜ ይደጋግማታል፡፡ ትርጉሟ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

## ከአል-ፋቲሐ ምዕራፍ ጋር

*[በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው፡፡]*

ስርአት በመያዝና እሱን በማላቅ አንደበት በአላህ ስም እጀምራለሁ፡፡ በርግጥ እሱ ሁሉንም በሚያዳርስ እዝነት የተገለጸ ጌታ ነው፡፡

*[ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለኾነው]*

በሁሉም መገለጫዎቹ፣ ተግባራቱ፣ ግልጽና ድብቅ በሆኑት ጸጋዎቹ ከውዴታና ከማላቅ ጋር አላህን አወድሰዋለሁ፡፡ በርግጥ እሱ ፈጣሪ፣ የሁሉም ነገር ባለቤት፣ ሁሉን ነገር እንዳሻው የሚከውን፣ ለሁሉም የፍጥረታት ዓለም ጸጋን ሰጪ የሆነ ጌታ ነው፡፡

*[እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ ]*

አላህ የእዝነት ቃል በውስጡ በያዛቸው አጠቃላይ ትርጓሜዎችና ሁኔታዎች የሚገለጽ፣ በፍጥረተ-ዓለሙ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ነገሮች የሚያጠቃልል የሆነ እዝነት ባለቤት ነው፡፡ እዝነቱም በተለየ ሁኔታ አማኝ ለሆኑት ባሪያዎቹ የሚዳረስ የሆነ ጌታ ነው፡፡

*[የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው፡፡]*

ምንዳ የሚሰጥበትና የሚተሳሰቢያው ቀን ባለቤት

*[አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን፡፡]*

ጌታችን ሆይ! በአምልኮ አንተን ብቻ አንወስናለን፡፡ ካንተ ውጭ ሌላን አካል በማንኛውም የአምልኮ ተግባር አናጋራም፡፡ ካንተም ብቻ በሁሉም ጉዳያችን እገዛን እንጠይቃለን፡፡ ሁሉም ጉዳይ ባንተ እጅ ነው ያለው፡፡ ከጉዳዩን ቅንጣት ታክል ጉዳይ አንድም አካል አይዝም፡፡

*[ቀጥተኛውን መንገድ ምራን፡፡]*

አላህ ሆይ! ቀጥተኛውን መንገድ መንገድ አመላክተን፤ ምራን፡፡ ንንተን እስክንገናኝ ድረስም በእሱ ላይ አጽናን፡፡

*[የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን]*

ቀጥተኛውን መንገድ በመምራትና በእሱም ላይ ቀጥ በማድረግ መልካም ነገር ያጎናጸፍካቸውን፤ የእነዚያ እውነትን አውቀው የተከተሉትን የነቢያትንና መልካም ባሮችን መንገድን

*[በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ]*

ከተቆጣህባቸውና እርግማንህን ካወረደክባቸው ሰዎች መንገድ አርቀን፤ ጠብቀንም፡፡ ምክንያቱም እነሱ እውነቱን አወቁ ነገር ግን አልተከተሉትም፡፡ ከእነዚያም እውነተኛውን መንገድ በመሐይምነታቸውና እሱን ለማወቅ በማጓደላቸው ከሳቱትም ሰዎች መንገድ እንዲሁ አርቀን፤ ጠብቀንም፡፡

*አሚን*

አላህ ሆይ! ጸሎቱን ተቀበል፡፡



## ለሁሉም መቋጫ ቃል አለው

ከዚህ ሁሉ በኋላ የሚቀረው ነገሩን ማጠቃለያ ቃል ነው፡፡ ሁላችንም ትርጉሙን በወጉ በማወቅ ቁርአንን በማንበብ የደረስንበት እውቀት፣ ተሞክሮ፣ ትምህርትና የማይረሳ አጋጣሚ ሊኖረን ይችላል፡፡ ቁርአንን ያወቅንበት ቋንቋ ዐረቢኛ ቋንቋ ባይሆንም እንኳ ማለታችን ነው፡፡

በአእምሯችንና በልቦናችን ቁርአንን ስናነብ የምናገኘው ሆነ ትልቅ አስረጅ በቁርአን ውስጥ የሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ነብይነት የሚያረጋግጥ አለ፡፡ ይህም እንዲህ በሚለው የአላህ ቃል ተቀምጧል፣ «እኛ መጽሐፉን በነሱ ላይ የሚነበብ ኾኖ ባንተ ላይ ማውረዳችን አይበቃቸውምን? በዚህ ውስጥ ለሚያምኑ ሕዝቦች ችሮታና ግሣጼ አለበት፡፡» (29፡51)፡፡

አላህ፣ ሰዎች በአጠቃላይ ቁርአንን እንዲያነቡ፣ እሱን እንዲያስተነትኑና ትርጉሙን በጥሞና እንዲረዱ ጥሪ አቅርቧል፡፡ በእርግጥ ልቦናውንና አእምሮውን የቆለፈ ሰው ካልሆነ በስተቀር ቁርአንን ከማንበብ እንቢ የሚል ማንም ሰው የለም (47፡24)፡፡



# በእስልምና የአምልኮታዊ ተግባራት ተልእኮ ምንድን ነው?



## እውን አላህ እሱን እንድናመልከው ይፈልጋልን?

እጅጉን የላቀውና የተከበረው አላህ አምልኮታችንንና ተግባራቶቻችንን ፈላጊ አይደለም፡፡ በእስልምና ሃይማኖዊ ቀኖናዎች፣ አካላዊ ተግባራትና ገንዘብ ልገሳዎች የነጻነትና ጽድቅ ምልክቶች አይደሉም፡፡ እነዚህ ነገሮች ነጻነትና ጽድቅ ሊሆኑ የሚችሉት ከልብ ከመነጨ እውነታዊ የሆነ ወደ አላህ መጠጋትና በእርሱም በማመን ነው፡፡ በገሃድ በላቀ መንፈስና ስነ-ምግባር፣ የሰው ልጅን በሚጠቅም ሥራና ለልማት በተግባር መተርጎሙ ግድ ይላል፡፡



በቁርአን ላይ አላህ እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡ ከነርሱም ምንም ሲሳይ አልፈልግም፡፡ ሊመግቡኝም አልሻም፡፡ አላህ እርሱ ሲሳይን ሰጪ የብርቱ ኀይል ባለቤት ነው፡፡›› (አዝ-ዛሪያት ፡ 56-58)

አንዳንድ ሰዎቸ ትክክለኛው ፊትን ወደከዕባ አቅጣጫ ማዞር ግራ በሚገባቸው ወይም ፊትን ወደ ካዕባ የማዞርን ምስጢር ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ የዚህ ትክክለኛ ምክንያቱ በእስልምና ስግደት የሚፈጸመው ፊትን ወደመካ አቅጣጫ በማዞር ስለሆነ ነው ስለዚህ ትክክለኛ ሃይማኖተኛነት ከልብ ከመነጨ እምነት፣ ልቦናን ወደአላህ በማዞር፣ ጽድቅ ተግባራትን በመፈጸምና የሰው ልጆችን በመጥቀም እንጂ ፊትን ወደምስራቅ ወይም ወደምዕራብ አቅጣጫ በማዞር ብቻ እንደማይወሰን አላህ እንዲህ በማለት መልስ ሰጥቷቸዋል፤ «መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፡፡ ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም፣ ያመነ ሰው ገንዘብንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች ለምስኪኖችም፣ ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቅ) የሰጠ ሰውና ሶላትንም ደንቡን ጠብቆ የሰገደ፣ ዘካንም የሰጠ፣ ቃል ኪዳንም በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች ሥራ) ነው፡፡ በችግር በበሽታና በጦር ጊዜም ታጋሾችን (እናወድሳለን)፡፡ እነዚህ እነዚያ እውነትን የያዙ ናቸው፡፡ እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡» (አል-በቀራህ ፡ 177)

በአምልኮታዊ ተግባር ላይና በሃይማኖተኛነት ላይ ጥረት የሚያደርግ ሰው ይህ ጥረቱ ራሱን ለመጥቀምና ራሱን ነጻ ለማውጣት እንደሚጠቅም፤ ያስተባበለ (የካደ) ሰው ደግሞ ብቸኛው ክስረቱን ተሸካሚ እሱ ብቻ እንደሆነ እንዲሁም አላህ ከሁሉም ነገሮች የተብቃቃ እንደሆነ ቁርአን እንደገና እንዲህ በማለት ያረጋግጥልናል፡፡ «የታገለ ሰውም የሚታገለው ለነፍሱ ነው፡፡ አላህ ከዓለማት በእርግጥ ተብቃቂ ነውና፡፡» (አል-ዐንከቡት ፡ 6)



> የተወሰኑ ሰዎች ስግደት ላይ ትክክለኛው ፊትን ወደካዕባ ማዞርን በተመለከተ አንዳንድ ጥያቄዎች ሲያድርባቸው ትክክለኛው ሃይማኖት እምነትን በማረጋገጥ፣ ፊትን ቀጥ ወዳለው መንገድ በማዞር፣ በመልካም ተግባራት በመፈጸምና የሰው ልጅን በመጥቀም እንደሆነ እንጂ ፊትን ወደምስራቅ ወይም ወደምዕራብ ዝም ብሎ ማዞር እንዳልሆነ ተረጋግጦላቸዋል፡፡

## የእስልምና መሰረቶች፡

በእስልምና የታዘዙ ከሆኑት አምልኮታዊ ተግባራት የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡-




በእርግጠኛነትና በቅንነት እንዲሁም በእምነት አምልኮታዊ ተግባራትን መፈጸም፣ ለመልዕክተኛው ሙሐመድ ተከታይ መሆን፡፡ ይኸውም በእርግጥ ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው ሌላ አምላክ የለም፣ በእርግጥ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ብለህ መመስከርህ ነው፡፡ (ገጽ (53)ን ተመልከት)




ግዴታ የሆኑ ስግደቶችን መፈጸም፡፡ (ገጽ (172) ን ተመልከት)




ምጸዋት ለሚገባቸው ሰዎች መስጠት (ገጽ (180) ን ተመልከት)

4



የረመዳንን ወር መጾም (ገጽ (186) ን ተመልከት)

5



በአካልም በገንዘብም ለሚችሉ የተከበረውን የአላህ ቤት መጎብኘት (ገጽ (189)ን ተመልከት)



## ትእዛዙና መፈተኑ ለምንድን ነው?

ይዘቱና አቀራረቡ ቢለያይም ምንጊዜም የሚደጋገመው ጥያቄ የሚከተለው ነው፡፡ እንመገብ ዘንድ አላህ፣ አፍ፣ ጥርሶችና ሆድ ፈጥሮልን ሳለ ለምንድን ነው ጹሙ የሚለን? ውበትንና ስጋዊ ስሜትን ፈጥሮልን ሳለ ለምንድን ነው ዓይኖቻችሁ ክልክል የሆኑ ነገሮችን እንዳይመለከቱ ጠብቁ፣ እናንተም ጥብቅ ሁኑ የሚለን? ከዚህ ከፍ ሲልም አንዳንዶች በመዳፈር ዓይነት ለምንድን ነው ጉልበትን ወይም ሃይልን ከከገሰን በኋላ በሌሎች ላይ ጠላትነትንና በደልን እንዳንፈጽም የሚከለክለን?

በእስልምና እይታ አውነታው በጣም ግልጽ የሆነ ነገር ነው፡፡ አላህ እነዚህን ችሎታዎችና ሃይሎች የሰጠን እንቆጣጠራቸው ዘንድ እንጂ እነሱ እንዲቆጣጠሩን አይደለም፡፡ ለምሳሌ እንድትጋልበውና እንድትሄድበት አላህ ፈረስን ይሰጠሃል እንጂ እሱ እንዲጋልብህ አይሰጥህም፡፡ በዚህም መሰረት የሰውነት አካላትንና ጉልበታችን እኛን ለማገልገል፣ እንድንጋልባቸው፣ እንድንመራቸው፣ በጊዜ፣ በቦታና በትክክለኛው መንገድ እንድንገለገልባቸው የተፈጠሩልን ፈረሶቻችን ናቸው እንጂ ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መንገድ የተፈጠሩ አይደሉም፡፡

ስለዚህ የሰው ልጅ ከሌሎች የሚሻልበት አብይ ነጥቡ ስሜቶቹን በመቆጣጠር ብቃቱ፣ ስሜቱን በመምራቱና ጉልበቱን በሚጠቅም ስፍራ ላይ በማዋሉ ነው፡፡ በዚህም አላህ የሰው ልጅን ልዩ ከማድረጉ ባሻገር የሙከራ ሜዳዎችንም አመቻችቶለታል፡፡ ለዚህም ነው አላህ የፈጠረን፡፡

> የሰው ልጅ ብልጫ የሚታወቀው ስጋዊ ፍላጎቱን በመቆጣጠር፣ ስሜታዊ ፍላጎቱንና ነፍሱን በቅጡ በመምራት ላይ ባለው ችሎታውና ይህን ጉልበቱን በሚጠቅም ነገር ላይ በማዋሉ ላይ ነው፡፡

ቁርአን እንዲህ ብሏል፡- «እኛ ሰውን (በሕግ ግዳጅ) የምንሞክረው ስንኾን ቅልቅሎች ከኾኑ የፍትወት ጠብታ ፈጠርነው፡፡ ሰሚ ተመልካችም አደረግነው፡፡ እኛ ወይ አመስጋኝ ወይም ከሓዲ ሲኾን መንገዱን መራነው፤ (ገለጽንለት)፡፡» (አል-ኢንሳን ፡ 2 -3)፡፡

የሰው ልጅ የሚያጋጥሙት ችግሮችና መከራዎቸ ራሳችንን፣ መንፈሳዊውን፣ ስነ-ምግባራዊውንና እምነታዊውን ሁኔታችን እናሻሽል እንዲሁም በዚህች ምድራዊ ሕይወት የተገኘንበትን ዓላማ ዘወር ብለን እንድናስታውስና እንድናስተውል ዘንድ ነው፡፡ ቁርአን ውስጥ እንዲህ የሚል አንቀጽ ሰፍሯል፤

‹‹ከፍርሃትና ከረኃብም በጥቂት ነገር፣ ከገንዘቦችና ከነፍሶችም፣ ከፍራፍሬዎችም በመቀነስ በእርግጥ እንሞክራችኋለን፡፡ ታጋሾችንም (በገነት) አብስር፡፡ እነዚያን መከራ፤ በነካቻቸው ጊዜ «እኛ ለአላህ፤ ነን እኛም ወደርሱ ተመላሾች» ነን የሚሉትን (አብስር)፡፡›› (አል-በቀራህ ፡ 155 -156)

እምነታችንንና ስነ-ምግባራችንን እንድናርቅና እናጎለብት ዘንድ የተዘጋጀልን ምድራዊ ሕይወት በእንዲህ ባለ ሁኔታ ነው የተዘጋጀልን፡፡ ከከንቱ ንግግሮች በእጅጉ የጠራው አላህ ራሳችንን ወደቅኑ መንገድ እንድንመራና እንድናስተካክል ተደጋጋሚ የሆኑ አጋጣሚዎችን ሰጠን እንጂ አላስገደደንም ይልቁንም የምርጫ በሮችን ክፍት አድርጎልናል፡፡

ምድርን የምናለማበትን፣ ሰዎችን የምንጠቅምበትን፣ ሁልጊዜ እየተሳሳትን በንሰሐ ወደርሱ እንዳንመለስ ከስሕተቶቻችንና ከጥረቶቻችን የምንማርበትን መንገዱን አመላክቶናል፡፡ አዛኝ የሆኑት ነቢይ ሙሐመድ (ዐ.ሰ) እንዲህ ብለዋል፤ *‹‹ሃጢአት ባትሰሩ አላህ እናንተን አጥፍቷችሁ ሃጢአት እየሰሩ ከአላህ ምሕረትን የሚጠይቁ እሱም የሚምራቸው የሆኑ ሕዝቦችን በእርግጥ ያመጣል፡፡›› (ሙስሊም 2749)*





# ስግደት

ሙስሊሞች ወደተወሰነ አቅጣጫ ፊታቸውን አዙረው በመቆም፣ በመጎንበስና በግንባራቸው ተደፍተው በመስገድ ስግደታቸውን ልክ ከዓለማዊ ሕይወት የተቆራረጡ ሆነው ሲጀምሩ ምናልባት ይህንን አስገራሚ የሆነ ትእይንት በቀጥታ ወይም በመገናኛ ብዙሃን መስኮቶች በኩል ስትመለከት በጣም ተደንቀህ ይሆናል፡፡

## የሙስሊሞች ስግደት ምንድን ነው?

ስግደት በእስልምና ሃይማኖት አስፈላጊ የሆነ ትልቅ ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም ስግደት ወደአላህ ይበልጥ መቃረቢያ፣ አላህን መለመኛና ለእሱ መተናነስን የምታመለክት የሆነች ድልድይ ነች፡፡ ይህም አላህ ለነቢዩ፤ «ስገድም፤ (ወደ አላህ) ተቃረብም፡፡»(አል-ዐለቅ ፡-19) በማለት እንዳዘዛቸው ዓይነት ነው፡፡ ስለዚህ ስግደት ከሁለቱ የምስክርነት ቃላት በመከተል ሁለተኛው የእስልምና መሰረት ተደርጋ የተወሰደችው፡፡

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፣ «እስልምና በአምስት ነገሮች ላይ ተመስርቷል፡፡ -እነርሱም- በእርግጥ ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው ሌላ አምላክ የለም ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር፣ ስግደትን መፈጸም ...» (ቡኻሪ 8)

እስልምና እንደሚያስተምረን ማንኛውም የሚሰግድ ሙስሊም ሲሰግድ በሚኖረው የልቦና ንጽሕናና ይህን እውን ለማድረግ በሚያደርገው ጥረት፣ ሃሳቡን በመሰብሰቡ፣ ትኩረቱንና እይታውን ወደ አንድ ሰፍራ በማድረጉ፣ በእውነት ወደአላህ በመዞር በፍራቻ ስሜት በመተናነሱና ወደአላህ ይበልጥ ቅርብ እንደሆነ በማሰቡ፣ ብሎም በማመኑ በስግደቱ መልካም ምንዳን ያገኛል፡፡ ስግደት ለነፍስ መረጋጋትንና እርካታን ያጎናጽፋል፡፡ ለዚህም ነው ስግደት በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ከፍተኛ ለዛ የነበረው፡፡

ከዚህ በመነሳት ቁርአን ስግድትን ወደመፈጸም ያመላክተናል፡፡ ይህ ሲባል ግን ስግደትን መፈጸም ስላልብን ብቻ መፈጸም አይደለም፡፡ በመሆኑም በስግደት ውስጥ ሁሉንም የሰውነት አካሎቻችንን ከአእምሮ፣ ከልቦናና ከመንፈስ ጋር ማሳታፍ አለብን፡፡ ይህን ከፈጸምን ስግደት መልካም ተግባራትን ለመፈጸምና ከመቅሰፍትና ከወንጀሎች

ለመራቅ ሁነኛ ድጋፍ ይሆነናል፡፡ አላህን ማወደስና ወደርሱም መጠጋት ከሰው ልጅ ተግባራት መካከል ትልቁ ተግባር ነው፡፡

አላህ እንዲህ ብሏል፡- «ከመጽሐፍ ወደ አንተ የተወረደውን አንብብ፡፡ ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ፡፡ ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና፡፡ አላህንም ማውሳት ከሁሉ ነገር በላጭ ነው፤ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ያውቃል፡፡» (አል-ዐንከቡት ፡ 45)

አንድ ሰው ስግደትን በማቃለል ‹እንዲያው ሰውነትን መታጠብ ቀዳሚው የሆነ አካላዊ እንቅስቃሴ (ስፖርት) ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ፣ እነዚህ የሚያስተውላቸው እንቅስቃሴዎችና ንግግሮች በልቦና ውስጥ አላህን ማላቅና ማክበር እንደሆነ ዘንግቷል ማለት ነው፡፡ አንድ የሚሰግድ ሰው እጆቹን ከማንሳት ጋር መጀመሪያ የሚናገረው ቃል /«አላሁ አክበር» አላህ የታላቆች ታላቅ ነው/ የሚል ነው፡፡ ከዚያም በሙሉ ተመስጥኦ የአላህን ትልቅነት በልቦናው ውስጥ እያሰላሰለ ከወደ ወገቡ ጎንበስ ይላል፡፡ አጎንብሶም፤ /«ሱብሓነ ረብቢየ-ል-ዐዚይም» ከሁሉም የላቀው ጌታዬ በእርግጥ በእሱ ላይ ከሚባሉት ከንቱ ንግግሮች በእጅጉ ጠራ/ ይላል፡፡ ከዚያም ወደጌታው በጣም መቅረብንና የዱዓውን ተቀባይነት በመፈለግ ግንባሩንና አፍንጫውን መሬት ላይ በመድፋት /‹‹ሱብሓነ ረብቢየ-ል-አዕላ›› /ከሁሉም በላይ የላቀው ጌታዬ በእርግጥ በእሱ ላይ ከሚባሉት ከንቱ ንግግሮች በእጅጉ ጠራ/ ይላል፡፡ በዚህ ጊዜም ጌታውን ይጠይቃል፣ ይለምናልም፡፡ እንዲህ ነው እንግዲህ እያንዳንዱ የስግደት ተግባር፡፡ ቃላቱ ካለምንም ፋይዳ ምላስን ማንቀሳቀስና ማጉረምረም አይደለም፡፡ በተቃራኒው ትርፋማ የሆነ ትልቅ አጋጣሚ ነው፡፡ ይህ ተግባር አንድን ሰጋጅ ደስታውና ሲሳዩን ከሚሰጠው ጌታው ጋር የሚያገናኝ ድልድይ ነው፡፡

አላህ በቀንና በማታ እንዲሁም በማንኛውም ስፍራ የሚሰገዱ የአምስት ወቅት ስግደቶቸን ግዴታ አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጫማሪ የሙስሊሞችን ግንኙነት ለማጠናከር፣ በሃይማኖታቸውና በዓለማዊ ጉዳዮቻቸው ላይ ይረዳዱ ዘንድ ሙስሊሞች ስግደታቸውን መስጊድ ውስጥ እንዲፈጽሙ አናሳስቷቸዋል፡፡

እስልምና ግዴታ ባልሆኑ ስግደቶች ላይ ጥረት በማድረግ ላይ አነሳስቷል፡፡ ይኸውም ማንኛውም ሙስሊም ንቃት ሲያገኝና ሲኖረው ብቻ ነው የዚህ ዓይነቶቹን ስግደቶች የሚፈጽመው፡፡

ሙስሊሞች ስግደታቸውን ሲፈጽሙ ፊታቸውን ወደካዕባ አቅጣጫ በመዞር ነው፡፡ ይህ ቤት አምልኮታዊ ቤት ሲሆን የአራት ማእዘን ቅርጽ ያለው ሕንጻ ነው፡፡ በመጀመሪያ የገነቡትም የነቢያት አባት ተብለው በተገለጹት ነቢዩ አብራሃም (ኢብራሂም) (ዐ.ሰ) ናቸው፡፡ የተገነባውም በምዕራባዊው የዐረቢያ የባሕር ወሽመጥ መካ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ ሁሉም ነቢያት (ዐ.ሰ) መንፈሳዊ ጉዞ ወደ ዚህች ከተማ አድርገዋል፡፡ ሙስሊሞች ባጠቃላይ ይህ ቤት ከድንጋይ የተሰራ ወይም የታነጸና ምንም የማይጠቅምና የማይጎዳ መሆኑን ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ነገር ግን አላህ ሙስሊሞችን አንድ ለማድረግ በስግደት ወቅት ወደአንድ አቅጣጫ ፊታቸውን እንዲያዞሩ በማዘዙ ፊታቸውን ወደዚህ ያዞራሉ፡፡

> ስግደት በነቢዩ ሙሐመድ -በእሳቸው ላይ የአላህ ሰላምና እዝነት ይሁን- ትልቅ ጣእም ያለው አምልኮታዊ ተግባር ነው፡፡



# አዛን

ለሙስሊሞች የስግደት ወቅት እንደደረሰ የሚያሳውቃቸውና ወደመስጊድ እንዲመጡ የሚያደርጋቸው ጥሪ አዛን ይሰኛል፡፡



አዛን አላህ ከሚወሳበትና ከሚላቅበት መንገዶች መካከል አንዱ ከመሆኑ ባሻገር ሙስሊሞች ወደስግደት ለመምጣት የሚዘጋጁበት ቃል ነው፡፡ ቃሉም የሚከተለው ነው፡፡

1. አላሁ አክበር፣ አላሁ አክበር፣ አላሁ አክበር፣ አላሁ አክበር፡፡
2. አሽሀዱ አን ላ ኢላሀ ኢልለላህ፣ አሽሀዱ አን ላ ኢላሀ ኢልለላህ፡፡
3. አሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ረሱሉላህ፣ አሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ረሱሉላህ፡፡
4. ሐይየ ዐለ-ስሰላህ፣ ሐይየ ዐለ-ስሰላህ፡፡
5. ሐይየ ዐለ-ል-ፈላሕ፣ ሐይየ ዐለ-ል-ፈላሕ፡፡
6. አላሁ አክበር፣ አላሁ አክበር፡፡
7. ላ ኢላሀ አልለላህ፡፡

LAUNCHING CURiOSiTY
CLICK HERE



መስጂዱ-ልሐራም በሙስሊሞች ዘንድ ትልቁ የሆነው መስጂድ ነው፡፡ በውስጡም ነቢዩ ኢብራሂም የገነቡት ካዕባህ ይገኛል፡፡ ይህ ካዕባ የአራት ማአዘን ቅርጽ ያለው ሕንጻ ሲሆን ሙስሊሞች ይህ ሕንጻ ምንም ጥቅምና ጉዳት እንደሌለው በማመን ከየተኛውም የዓለማችን ክልል ስግደት ለመፈጸም ወደዚህ ሕንጻ ፊታቸውን እንዲያዞሩ በቁርአን ውስጥ ታዘዋል፡፡



## ምጽዋት

ሁሉም ሰው በጣም በተትረፈረፈ ሐብትና በጣም አሳፋሪ በሆነ ድህነት መካከል ያለው ተቃርኖ የግድ መጥፋት እንዳለበት ያምናል፡፡ ይህም በተቻለ መጠን በሐብታሞችና በድሆች መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት ለማጥበብ ነው፡፡ ይህን ማድረግ በማሕበረበሰቡ ውስጥ ዝቅጠት፣ ውርደት፣ ወንጀልና የቤተሰብ መበታተንን ይከላከላል፡፡ በእርግጥ ይህን ችግር ለመቅረፍ የምጣኔ-ሐብት ስርአቱ ፣ የፍልስፍና አስተሳሰቡና ሕግና ደንቦች ተለያይተዋል፡፡ ይህን ችግር ታዲያ እስልምና እንዴት አስተናግዶት ይሆን?

ሙስሊም የሆኑ ባለሀብቶች ካላቸው አጠቃላይ የራሳቸው የተጣራ ትርፍና ገቢ የሐብት መጠን ላይ 2.5% የሚሆነውን በዓመት አንድ ጊዜ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ምስኪኖች፣ ድሆችና ወ.ዘ.ተ ለመሳሰሉት ይሰጥ ዘንድ ለምጽዋት እንዲያወጡ ግዴታ አድርጎባቸዋል፡፡ ይህን ተግባር እስልምና ከእስልምና መሰረቶች መካከል በሶስተኛ ደረጃ ላይ አስቀምጦታል፡፡

የምጽዋት ዋና ዓላማ በሐብታምና በድሃ መካከል ልዩነት ወይም መበላለጥ እንዲኖር ማድረግ ሳይሆን ከሐብታሙ ለድሃው ጉዳይ ማስፈጸሚያ የሚሆን ገንዘብ በመውሰድ ድሃው ሳይለምን ድጋፍ እንዲያገኝ ማገዝ ነው፡፡

ይህ ቀለል ያለ የገንዘብ መጠን ነው እንግዲህ በሙስሊም ሐብታም ላይ ግዴታ የሆነው፡፡ ከዚህ የበለጠውን ለመለገስ ለሚፈልጉ የውድድር በሩ ምንጊዜም ክፍት እንደሆነ እስልምና ለሰዎቹ ግልጽ አድርጎላቸዋል፡፡ ሰጪዎቹ የዚህን የመለገስ ትሩፋቶች በምድራዊ ሕይወታቸው ጤንነትን፣በረከትን፣መልካም እድልንና ደስታን በማግኘት ሲያጣጥሙ በመጪው ዓለም ደግሞ እጥፍ ድርብ ምንዳንና ጸጋን ይጎናጸፋሉ፡፡

በቁርአን ላይ እንደሰፈረው አላህን ለማስደሰት ገንዘባቸውን የሚሰጡ ምሳሌያቸው ልክ አንድ ስንዴ ከተዘራች በኋላ አዝመራው ሲደርስ በእያንዳንዱ የስንዴ ዘለላ ላይ ሰባት ዘለላዎችን እንደምታፈራ ዓይነት ነው፡፡ እያንዳንዱ ዘለላ ደግሞ አንድ መቶ ፍሬዎች ይኖሩታል፡፡ ይህ ፍሬ በሰባት መቶ እጥፍ እንደሚባዛ ዓይነት ነው፡፡ ይህን አላህ በሰጪው ልቦናዊ ተነሳሽነትና ጥረት አንጻር ነው የሚፈጽመው፡፡ አላህ ሲሳየ ሰፊና እያንዳንዷን እውነታ ጥልቅ ዐዋቂ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ላይ እንዲህ ብሏል፣ ‹‹እነዚያ ገንዘቦቻቸውን በአላህ መንገድ ላይ የሚለግሱ ሰዎች (ልግስና) ምሳሌ፥ በየዘለላው ሁለት መቶ ቅንጣት ያለባቸውን ሰባት ዘለላዎች እንደአበቀለች አንዲት

ቅንጣት ብጤ ነው፤ አላህም ለሚሻው ሰው (ከዚህ በላይ) ያነባብራል፤ አላህም ችሮታው ሰፊ ዐዋቂ ነው፡፡» (2፡261)

ለቸገረው ሰው ገንዘብ መስጠት ነፍስን እንደሚያጠራና እንደሚያስወድስ አላህ (ሱ.ወ) የተከበሩ መልዕክተኛውን እያናገረ እንዲህ ብሏል፣ «ከገንዘቦቻቸው ስትኾን በርሷ የምታጠራቸውና የምታፋፋቸው የኾነችን ምጽዋት ያዝ፤» (9፡103)

እንዲሁም በገንዘቡ የሚሰስት፣ከመስጠትና ድሆችን ከመርዳት የሚከለክል ሰው እሱ ኪሳራዎች ላይ ከሚወድቁት የመጀመሪያዎቹ ሰዎች መካከል አንዱ እንደሚሆን ነግሮናል፡፡ምክንያቱም ነፍሱን ከምድራዊና ከመጪው ዓለም ደስታ ከልክሏልና ነው፡፡

ቁርአን ውስጥ እንዲህ የሚል አንቀጽ ሰፍሯል፤ « ንቁ! እናንተ እነዚያ በአላህ መንገድ ትለግሱ ዘንድ የምትጥጠሩ ናችሁ፡፡ ከእናንተም ውስጥ የሚሰስት ሰው አልለ፡፡ የሚሰስትም ሰው የሚሰስተው በራሱ ላይ ብቻ ነው፡፡ አላህም ከበርቴ ነው፡፡ እናንተም ድኾች ናችሁ፡፡ ብትሸሹም ሌሎችን ሕዝቦች ይለውጣል፡፡ ከዚያም (ባለመታዘዝ) ብጤዎቻችሁ አይኾኑም፡፡» (ሙሐመድ ፡ 38)

ይህን ከእስልምና ምሰሶዎች መካከል የላቀ የሆነውን ምሰሶ በትክክለኛው አረዳድ መተግበር ማሕበራዊ ዋስትናን ማረጋገጥና በማሕበረሰቡ መካከል የሚስተዋለውን ልዩነት ሚዛናዊ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ምጽዋትን ለተገቢው ሰው መስጠት ማለት በተወሰነ የማሕበረሰቡ ክፍል ውስጥ ገንዘብ ያለጥቅምና ያለአግባብ እንዳይከማች ያደርጋል፡፡ ይህ ተግባራዊ ሰለተደረገ ነው በእስልምና ታሪክ ገንዘቦች ተሰብስበው ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ይሰጡ ተብሎ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች የታጡበት አጋጣሚ የተከሰተው፡፡

ተገቢውን ምጽዋት መስጠት በማሕበረሰቡ አባላት መካከል ያለውን ማሕበራዊ ትስስር ይበልጥ ከማጠናከሩ ባሻገር የወዳጅነት መንፈስን ያጎለብታል፡፡ ምክንያቱም የሰው ልጅ መንፈስ መልካም የዋለላትን እንድትወድ ተደርጋ ተፈጥራለችና ነው፡፡ ይህ በአግባቡ ተፈጻሚ የሚሆን ከሆነ በሙስሊሙ ማሕበረስብ መካከል የሚኖረው ግንኙነት ሙስሊሞች እርስ በእርስ ተሰካክቶ በጥንካሬ እንደተገነባ ግንብ ዓይነት ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህም የስርቆት፣ የዘረፋና የብዝበዛ ወንጀሎች ሊቀረፉ ይችላሉ፡፡



በዘካ ላይ በድሃ ላይ የሐብታም የበላይ መሆን ሁኔታ የለም፡፡ እንዲያውም ዘካ ሐብታም ከሆነ ሰው ገንዘቦች ላይ የሚወሰድ ድሃ የሆነ ሰው መብት ነው፡፡ በዚህም ሐብታም የሆነው ሰው ጠያቂ የሆነን ሰው ሳይፈልግ ገንዘቡ ወደሚፈልጉት ሰዎች ዘንድ ይደርሳል፡፡





> የአላህን ውዴታ ለማግኘት ሲሉ ገንዘባቸውን የሚያጠፉትን ሰዎች ልክ በተዘራች የስንዴ ዘርና ይህች የስንዴ ዘር ካደገች በኋላ ሰባት ቀንዘሎችን እንደምታፈራና በእያንዳንዱ ቀንዘል መቶ ፍሬዎችን እንደሚገኙበት፣ እነዚህ ፍሬዎች እስከ ሰባት መቶ እጥፍ እንደሚደርሱ በሚመስል ሁኔታ መስሏቸዋል፡፡



# ፆም

አንድ ሰው ጤንነቱን ለመጠበቅ ወይም ክብደቱን ለመቀነስ ወይም ከሐኪም የተሰጠውን ትእዛዝ ለማክበር ራሱን በመቆጣጠር ከምግብና ከምግብ ዓይነቶች ሲከለከል ይገርመናል፡፡ ይህንንም ተግባር እንደስኬትና ግብ እንዲሁም ስሜታዊ ፍላጎቶችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ልዩ ችሎታ አድርገን እንወስደዋልን፡፡

አንድ ሙስሊም በመጾሙ ምክንያት ራሱን የሚያሰለጥንበትን፣ ስሜቱን የሚቆጣጠርበትን እንዲሁም የአስተዳዳሪዎች ሁሉ የበላይ የሆነውን የአላህን ትእዛዝ በመፈጸም ረገድ ከዚህም የላቀ ተግባር መፈጸም ይችላል፡፡

ጾም ከእስልምና መሰረቶች መካከል አራተኛው መሰረት ነው፡፡ እስልምና መጾም በሚችል ሰው ላይ ጾምንና ጾምን ከሚያስፈስኩ (ከሚያበላሹ) ነገሮች መቆጠብን ግዴታ ያደርጋል፡፡ እነዚህ ጾምን የሚያበላሹ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡ በኢስላማዊው የቀን መቁጠሪያ ቀመር ዘጠነኛ በሆነው በረመዳን ወር በእየለቱ ጎህ ከቀደደበት ጊዜ ጀምሮ ጸሐይ እስከትጠልቅ ድረስ ከምግብ፣ ከመጠጥና ከሚስት ጋር የግብረ-ስጋ መፈጸም መታቀብ ናቸው፡፡

ፆም በቀደምት ሕዝቦች ላይ በተለያዩ የአፈጻጸም ሁኔታዎች ተደንግጎ እንደነበር፣ ዓላማውና ግቡ አንድና ተመሳሳይ እንደነበር፣ ፈጽሞም እንደማይለወጥና ዓላማውና ግቡ አምልኮትንና ፍራቻን ለአላህ ማረጋገጥ እንደሆነ ቁርአን ይነግረናል፡፡

በቁርአን ላይ አላህ እንዲህ ብሏል፤ «እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡» (አል-በቀራህ ፡ 183)

አንድ ሙስሊም በተፈቀደለት ስጋዊ ስሜት ላይ ለተወሰኑ ሰዓታትና ቀናት ድልን ሲቀዳጅ የነፍሱ ንጉሥ ለመሆን ከመቻሉ ባሻገር ስሜቱን በአግባቡ ለመቆጣጠርና ስሜቱ ክልክል በሆኑ ስፍራዎች ላይ እንዳይውል ለመለጎም አቅም ይኖረዋል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ትክክለኛ ሁኔታውና ስነ-ምግባሮቹ ከፆም በኋላ የማይቀኑለት ሰው ከጾሙ ምንም ነገር እንዳልተጠቀመ እንዲህ በማለት አስጠንቅቀዋል፣ «እኩይ ንግግሮችንና በእነርሱም መስራትን የማይተው ሰው፣ ምግቡንና መጠጡን በመተዉ አላህ ምንም ጉዳይ የለውም፡፡» (ቡኻሪ 1804)፡፡

አንድ ሰው ሲጾም ምንም ዓይነት ምግብና መጠጥ የማያገኙ ድሆችንና ረሃብተኞችን ረሃብና ጥም እንዲሁም ችግር በእጅጉ አውቆ እነርሱን ለመርዳት የላቀ እንቅስቃሴ እንዲያደርግና እነርሱ እንዲህ የሆኑት በራሳቸው ፍላጎት እንዳልሆነ እንዲረዳ ፆም አብይ ሚና ይጫወታል፡፡

> የኢስላም ነቢይ ከጾም በኋላ ስነ-ምግባራቱና ሁኔታው የማይቀየር ሰው ከጾሙ ምንም ጥቅም እንደማያገኝ አስጠንቅቃል፡፡

እስልምና በአንድ ሙስሊም በሆነ ሰው ላይ ጾምን ግዴታ ሲያደርግ ድሆች የሚሰማቸውን ረሐብንና የምግብ ፍላጎታቸውን ያስታውሰዋል፡፡





# ሐጅ

አብዛኛዎቹ ሃይማኖቶች ፈጣሪያቸውን ማምለካቸውንና እሱንም መማጸናቸውን የሚያሳዩበት ጉዞ አሏቸው፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ ሃይማኖታዊ ጉዞዎች መካከል በየዓመቱ በሚሄዱ ተጓዦች ቁጥር ትልቅነት አንጻር በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ የሚፈጸመውን አምልኮታዊ ጉዞን (ሐጅ) የሚስተካከል የለም፡፡ በዚህ አምልኮታዊ ጉዞ ከሶስት ሚሊዮን የሚበልጡ ሰዎች ያንን የተቀደሰ ጉዞ ለመፈጸም በትንሽ ስፍራ ላይ ይሰበሰባሉ፡፡

## እስላማዊው አምልኮታዊ ጉዞ ምንድን ነው?

ሐጅ ከእስልምና መሰረቶች መካከል አራተኛው መሰረት ነው፡፡ አካላዊና የገንዘብ አቅም ላለው ሰው በእድሜ አንድ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር ግዴታ አይደለም፡፡

ይህ ጉዞ በሰው ልጆች መካከል ያለው የመደብ፣ የዘር፣ የሐብትና የባህል ልዩነቶች የሚጠፉበት ጉዞ ነው፡፡ በዚህ ጉዞ ሁሉም ሰዎች አንድ ዓይነት ልብስ፣ አንድ ዓይነት ቃል፣ አንድ ዓይነት ጥሪ ያንጸባርቃሉ፡፡ «ለበይከ አላልላሁምመ ለበይክ፣ ለበይከ ላ ሸሪከ ለከ ለበይክ፣ ኢንነ-ል-ሐምደ ወንኒዕመተ ለከ ወልሙልክ ላ ሸሪከ ለክ» በማለት በሰው ልጅና በጌታው መካከል ያለውን የግንኙነት እውነታ ይፋ ያደርጋሉ፡፡ የዚህ ቃል ትርጓሜ፣ ‹ አላህ ሆይ! ጥሪህን ሰምተናል ምላሽም ሰጥተናል፡፡ ላንተ አጋር የሌለህ አላህ ሆይ! ጥሪህን ሰምተናል ምላሽም ሰጥተናል፡፡ በእርግጥ ምስጋናም ጸጋም ላንተ ነው፡፡ ንግስናም እንዲሁ ላንተ ነው፡፡ በእርግጥ ላንተ አጋር የለህም፡፡» ማለት ነው፡፡

ሐጅ አንድ ሙስሊም በሁኔታዎች፣ በተግባራትና በንግግሮች መካከል ልውውጥ የሚያደርግበት እምነታዊ ጉዞ ነው፡፡ ሁሉም ተጓዥ ዓላማውንና ግቡን አላህን በማውሳትና በመፍራት፣ ድህነቱንና መፈለጉን ወደላቀው አላህ ማስጠጋት፣ ምሕረትና ምንዳን ከአላህ በመፈለግ ላይ ያደርጋል፡፡ ሙሐመድ (ዐ.ሰ) እንዲህ ብለዋል፤ «በቤቱ (በከዕባ) ዙርያ መሽከርከርና በሐጅ ላይ መሮጥ የተደረገው አላህን ለማስታወስ እውን ለማድረግ ነው፡፡» (ኢብን አቢ ሸይባህ 15334)

የሐጅን አምልኮታዊ ተግባር ለማድረግ ያለመ ሰው የከት ልብሱን ካወለቀ በኋላ የሚለብሰው ልብስ ነው፡፡ ይህ ልብስ ለአላህ መተናነስን የሚገልጹና የሐጅ አምልኮታዊ ተግባርን አልመው ከመጡት ሌሎች ሰዎች ጋር ያለን እኩልነትን ለመግለጽ የሚያስችሉ ሁለት ጨርቆች ናቸው፡፡





# ቤተሰብ በእስልምና



በአሁን ዘመን ቤተሰብ የሚለውን ቃል ትርጓሜ እውነታ የሚያደርገው አገላለጽ፡- አንድ ቤትን ለመክፈት አንድ ቁልፍ ያላቸው የብዙ ሰዎች ስብስብ ሆኗል የቤተሰብ ትርጓሜ፡፡

የሚያሳዝነው በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች እውነተኛውን የሚስትንና የልጆችን ሃላፊነት ላለመሸከም ይሸሹ ጀምረዋል፡፡ ታዲያ ይህን ትልቅ ሃላፊነት ሳይሸከም እንዴት አድርጎ ነው ደስታውን ሊያጣጥም የሚችለው?

በዚህ ባለንበት ዘመን ይህ ሁኔታ ይፋ ይሁን እንጂ በሰው ልጆች ታሪክ መጀመሪያ አንስቶ ይህን ሁኔታ የሚያናፍሱ ሰዎችም ነበሩ፡፡ በእርግጥ ይህ ሁኔታ መሰረቱ ግላዊ ጥቅም፣ ራስ ወዳድነት፣ በግልሰቦችና በማሕበረሰቡ ላይ የሚፈጥረውን ተጽእኖ አለማየት ነው፡፡

ከዚህ በመነሳትም እስልምና ለዚህ ዓይነቱ ቤተሰባዊ ሕይወት ልዩ ትኩረትና ድጋፍ ለማድረግ መጥቷል፡፡ ሥርአቶችን፣ መብቶችን፣ ግዴታዎችን በግለሰብ ደረጃ አስቀምጧል፡፡ ምክንያቱም በእስልምና ቤተሰብ የተመሰረተበት ቤት አእምሯዊ ትኩረትን፣ አስተዳደግንና ብልጽግናን የያዘ ማእከል ተደርጎ ስለሚወሰድ ነው፡፡ በቤተሰብ ግንባታ፣ ጥሩ መሆንና ተልእኮ መወጣት ለማሕበረሰቡ መልካም መሆን ወሳኝ ነው፡፡

ይህ እስላማዊ አትኩሮት በዝርዝር በማይዘለቁ በርካታ ጥበቦች ግልጽ ሊሆን የሚችል ቢሆንም ከዚህ እንደሚከተለው የተወሰኑትን እንመልከት፡-

# 1



## እስልምና የጋብቻን መሰረተ-ሃሳብና የቤተሰብ ምስረታ አረጋግጧል፡፡

- እስልምና ጋብቻንና የቤተሰብ ምስረታን ከላቁ ተግባራትና ከመልዕክተኞች ፈለጎች መካከል አንዱ እንዲሆን አድርጓል፡፡ አንዳንድ የተከበሩት መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ሙሉ ሕይወታቸውን በአምልኮ ተግባራት ላይ ለማዋል፣በስግደትና በፆም ለማሳለፍና ጋብቻን ለመራቅ ሲወስኑ የተከበሩት መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ይህ አግባብ እንዳልሆነና ትክክለኛው መንገድን ሲያመላክቷቸው እንዲህ ብለው ነበር፡፡ ‹‹እኔ ግን እፆማለሁ፣ እፈስካለሁም፡፡ እሰግዳለሁ፣እተኛለሁም፡፡ ሴቶችን አገባለሁም፡፡ ከእኔ ፈለግ ያፈነገጠ ከእኔ አይደለም፡፡›› (ቡኻሪ 4776)

- ቁርአን በሰው ልጅ ላይ የዋላቸውን ጸጋዎችና ተአምራት ሲጠቅስ በቀደምትነት አላህ በባልና በሚስቱ መካከል የፈጠረውን እርጋታ፣ ውዴታ፣ እዝነትና ደስታ ይጠቅሳል፡፡ በቁርአን ላይ እንዲህ የሚል አንቀጽ ሰፍሯል፤ «ለእናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደ እነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉ፡፡» (አር-ሩም ፡ 21)

- እስልምና የጋብቻ ሁኔታ ቀላል እንዲሆን አዟል፡፡ ጋብቻ መመስረት ለሚፈልግ እገዛውንም ለማድረግ ቃል ገብቷል፡፡ መልእክተኛው (ዐ.ሰ)፡- «ሶስት ሰዎች አላህ እንዲረዳቸው በአላህ ላይ የተገቡ ናቸው፡፡» አሉና ከእነርሱ መካከል፡- «ጥብቅነትን በመፈለግ ጋብቻ የሚፈጽም ነው፡፡» በማለት ጠቀሱ፡፡ (አት-ቲርሚዚይ 1655)

- ጋብቻ ውስጥ የተረጋጋና የሰከነ መኖሪያ ከመኖሩ ባሻገር ለስሜታዊ ፍላጎትና ሃይል ፍቱን ሸሪዓዊ መፍትሔ ያለ በመሆኑ፣በትኩስ ጉልበታቸውና ሃይላቸው ላይ እያሉ እንዲያገቡ እስልምና ወጣቶችን አዟል፡፡

ቁርአን የሰው ልጅ ስለተጎናጸፉቸው ጸጋዎችና ተአምራት ሲያወሳ ከእነሱ መካከል በቅድሚያ በአንድ ባልና ሚስት መካከል አላህ የፈጠረውን እርጋታ፣ ውዴታ፣ እዝነትና ተድላ ይጠቅሳል፡፡



# 2



## እስልምና ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ሴትም ሆነች ወንድ ተገቢውን ክብር ሰጥቷል፡፡

ልጆችን በማሳደግ ረገድ እስልምና አባትና እናትን ትልቅ ሃላፊነት አሸክሟቸዋል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፣‹‹ሁላችሁም ጠባቂዎች ናችሁ፣ ጠባቂ በሆናችሁበት ነገርም ተጠያቂዎች ናችሁ፡፡ መሪ ጠባቂ ነው እሱም ተጠያቂ ነው፡፡ የቤት አባወራ በቤተሰቦቹ ላይ ጠባቂ ነው እሱም ተጠያቂ ነው፡፡ አንዲት ሚስት በባሏ ቤት ላይ ጠባቂ ነች እሷም ተጠያቂ ነች፡፡ ባሪያ በአስተዳዳሪው ንብረት ላይ ጠባቂ ነው እሱም ተጠያቂ ነው፡፡ አዋጅ! ሁላችሁም ጠባቂዎች ናችሁ ሁላችሁም ተጠያቂዎች ናችሁ፡፡›› (ቡኻሪ 853)

# 3

## እስልምና ለአባቶችና እናቶች የሚፈጸመው ክብርና የማላቅ መንፈስ፣ እነሱንም የመንከባከብና የመታዘዝ መንፈስ እስከሞት ድረስ በሰዎች ዘንድ እንዲሰርጽ ልዩ ትኩረት አድርጓል፡፡

ወንድ ልጅ ወይም ሴት ልጅ ምንም በእድሜ ቢገፉም ወላጆቻቸውን የማክበርና ለእነርሱም መልካም የመዋል ግዴታ አለባቸው፡፡ አላህ ይህን ሁኔታ እርሱን ከማምለክ ተግባር ጋር አቆራኝቶታል፡፡ በእነሱ ላይም በቃል፣ በተግባር እንዲሁም እነሱ ላይ ቁጣ የሚፈጥር ይዘት ያለውን ድምጽ ወይም ቃልን በማውጣት ድንበር ከማፈለፍ አስጠንቅቋል፡፡ በቁርአን ላይ አላህ እንዲህ ብሏል፡ - ‹‹ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ፡- እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ፡፡ በወላጆቻችሁም መልካምን ሥሩ፡፡ በአንተ ዘንድ ኾነው አንዳቸው ወይም ሁለታቸው እርጅናን ቢደርሱ ፎህ አትበላቸው፡፡ አትገላምጣቸውም፡፡ ለእነርሱም መልካምን ቃል ተናገራቸው፡፡›› (አል-ኢስራእ ፡ 23)

# 4



## የልጆችን መብቶች በመጠበቅና በመካከላቸው በሚደረግ ወጪ ላይ ፍትሐዊ መሆን እንዳለበት እስልምና አዟል፡

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፣ ‹‹አንድ ሰው የሚያስተዳድራቸውን ሰዎች ማጥፋቱ ለሐጢአት በቂው ነው፡፡›› (አቡዳዉድ 1692)፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በተለይ ሴት ልጆችን መንከባከብንና ለእነርሱም ተገቢውን ወጪ ማድረግን አስመልክተው እንዲህ ብለዋል፣ ‹‹ከእነዚህ ሴት ልጆች አንዳች ሃላፊነት ወስዶ መልካም የዋለላቸው እንደሆነ ከእሳት ግርዶ ይሆኑለታል፡፡›› (ቡኻሪ 5649)

# 5



## እስልምና ዝምድናን መቀጠል በማንኛውም ሰው ላይ ግዴታ አድርጓል፡

ይህ ማለት አንድ ሰው በአባቱ እና በእናቱ በኩል ካሉት ቤተ-ዘመዶቹ ጋር ግንኙነት መፍጠር ማለት ነው፡፡ አላህ ይህን ተግባር መፈጸምን ወደእሱ ከሚያቃርቡ ታላላቅ ተግባራት መካከል ከመፈረጁም በላይ ሰዎች ይህን ግንኙነት እንዳያቋርጡና እንዳያበላሹ አስጠንቅቋል፡፡ ግንኙነቱን ማቋረጥና ማበላሸት ከታላላቅ ወንጀሎች መካከል አስቀምጦታል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፣ ‹‹የዝምድና ግንኙነቱን የሚቆርጥ ገነት አይገባም፡፡›› (ሙስሊም 2556)፡፡



እስልምና በወላጆች ላይ በቃላትም ይሁን በተግባራት ወሰን ማለፍን ከልክሏል፡፡ እነሱ ላይ መጮህን በምታመለክት አንዲት ቃል ወይም ድምጽ ቢሆንም እንኳ ይህ ወሰን እንዳይታለፍ ከልክሏል፡፡

# በእስልምና የሴቶች ስፍራ



በቴሌቭዥን ወይም የመንገድ ላይ ግዙፍ ማስታወቂያዎችን ወይም የመጽሔቶችን ውጫዊ ሽፋን ላፍታ ብንመለከት የዘመኑ ስልጣኔ በሴቶች ላይ እየፈጸመ ያለውን ወንጀል እንመለከታለን፡፡ ከዚህ ባሻገር ሴት ልጅ በአብዛኛው እንደ አሻንጉሊት ወይም እንደ ሸቀጥ ወይም ወሲባዊ ስሜት በመቀስቀስ በእብደታዊ ምናብ ስሜትን እንደማርኪያ ወ.ዘ.ተ እንደምትቆጠርና እንደምትታይ ያረጋግጥልናል፡፡



ም ምናልባትም እንደቀደምት ያለፉ ዘመናት አይምሰል እንጂ በአሁኑ ዘመን የሴትን ልጅ ሰብአዊ ክብር ማዋረድና እሷን እንደ አንድ የደስታ ምንጭ፣ እንደሚሸጥና እንደሚገዛ ሸቀጥ አድርጎ መመልከት የስልጣኔ ምልክት ተደርጎ እየተቆጠረ ነው፡፡

ሴት ልጅ ከቀደምት ዘመናት አንስቶ እስከ አሁን ድረስ የሚደርስባትን መከራ፣ስቃይና በደል እየቀመሰች እዚህ ብትደርስም ከዚህ ሁሉ መከራ፣ስቃይና በደል በኋላ ራሷን በትንሹም ቢሆን ወደሰብአዊነት ለመቀየር ሙሉ ለሙሉ ነጻነቷን ልታገኝና ከሚደርሱባት ነገሮች ሁሉ ልትወጣ አልቻለችም፡፡

ከአንድ ሺህ ዓመታት በፊት እስልምና ከመጣ በኋላ በሴት ላይ የሚደርሰውን ሁሉ ከመሰረቱ ገርስሶ ለመጣል ትክክለኛው አብዮት ተጀመረ፡፡ ለሴት ልጅ ክብሯንና መብቶቿን የሚያስጠብቁላት፣ በወንዶች መካከል ታፍራና ተከብራ እንድትኖር የሚያደርጓትንና በሕይወት ውስጥ ያላትን ተልዕኮና ግብ በወጉ ዳር ታደርስ ዘንድ የሚያስችሏትን ድንጋጌዎችና ስርአትን በግልጽ አስቀመጠላት፡፡ በዚህም የተነሳ ረዣዥም ከሆኑት የቁርአን ምዕራፎች መካከል የሴቶችን ጉዳይ የሚዳስሰው ምዕራፍ በሴቶች የወል መጠሪያ ተሰይሟል፡፡ ቁርአን የበርካታ ቀደምት መልካም እንስቶችን ታሪክ በውስጡ አስፍሯል፡፡ ከእነዚህ መልካም ሴቶች መካከል አንዱን ምዕራፍ በኢየሱስ እናት በድንግል ማርያም /መርየም/ (ዐ.ሰ) ስም ሰይሟል፡፡

እስልምና ቀድሞ በወንዶች ዘንድ ለሴቶች ይሰጥ የነበረውን ዝቅተኛ አመለካከትና ስፍራ ለማረቅና እሷን ከሸቀጥነት እይታ ወደሰብአዊ ፍጡር፣ ከአንዲት ሌሊት የደስታ አጋርነት ወደሕይወት አጋርነት፣ ከወሲባዊ እርካታ ምንጭነት ወደፍሰሐ፣ እርጋታ፣ የፍቅርና የውዴታ ምንጭነት ለመቀየር መጥቷል፡፡

## እስልምና ለሴቶች ካጎናጸፋቸው ክብሮች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ:

- አንዲት ሴት ለጋብቻ የሚሆናትን ባል እንድትመርጥ ነጻነቱንና መብቱን ሰጥቷታል፡፡ ልጆችን በመንከባከብና በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ የሃለፊነት ድርሻ አሸክሟታል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፣ «አንዲት ሚስት በባሏ ቤት ላይ ጠባቂ ነች እሷም ተጠያቂ ነች፡፡» (ቡኻሪ 853)፡፡
- ከጋብቻ በኋላም ቢሆን ምንጊዜም በአባቷና በቤተሰቦቿ ስም እንድትጠራ ሙሉ ስሟንና ክብሯን ጠብቆላታል፡፡ ይህ ማለት በአንዳንድ ሀገራትና ባህሎች አንዲት ሴት ጋብቻ ከመሰረተች በኋላ የምትጠራው በባሏ ስም ነው፡፡ ነገር ግን እስልምና ይህን ስርአት ውድቅ በማድረግ የሴቷን ክብር ጠብቋል፡፡
- በበርካታ ጉዳዮች ላይ እስልምና ሴቶችን ከወንዶች እኩል አድርጓቸዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል ገንዘብ ነክ ጉዳዮች በአብነት ይጠቀሳሉ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፣ «ሴቶች የወንዶች አካላት ናቸው፡፡» (አቡ ዳዉድ 236)፡፡
- አንዲት ሴት ሚስትም ትሁን ልጅ ወይም እናት ማገኛውም ወንድ እሷን የመርዳት ሃላፊነት እስከተጣለበት ድረስ እሷን የመንከባከብና የመጠበቅ ግዴታ አድርጎበታል፡፡

- እስልምና ሴት ልጅን በማክበር እንደተከበረችው የመውረስ መብቷን አስከብሮላታል፡፡ አንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ከወንድ እኩል የውርስ ድርሻ ስታገኝ፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ደግሞ ከፍ ወይም ዝቅ ይላል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ቅን አመለካከት የሌላቸው ወንዱ በሴቷ ላይ ያለበትን ግዴታዎች ዘወር ብለው ሳያስተውሉና ሳይመለከቱ ሴቷ ከወንድ ያነሰ ድርሻ መውሰዷን በመመልከት ብቻ እስልምና ሴቷን በድሏታል ብለው ያወራሉ፡፡ ነገር ግን እውነታው ይህ ሳይሆን ወንዱ የሴቷን ማንኛውንም ገንዘብ ነክ ወጪዎችን የመሸፈንና የማሟላት ግዴታ አላህ ስለደነገገበት ነው፡፡ ይህ ማለት ሴቷ በውርስ ከወሰደችው የውርስ ድርሻ በተጨማሪ ማለታችን ነው፡፡
- ዘመዷ ባይሆኑ ከጎኗ ረዷና አጋዥ የሌላትን ሴት እንኳ መርዳትና ማገዝ ከጎኗ ሆኖ አለሁሽ ማለት በእስልምና ታላቅ የጽድቅ ስራ ከመሆኑ ባሻገር ታላቅ ክብር ያለው ተግባር ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፣ «ባሏ ለሞተባት ሴትና ለምስኪን ጉዳይ የሚሯሯጥ ሰው፤ በአላህ መንገድ ላይ እንደሚጋደል፣ ሌሊት ቢሰግድ እንደማይደክመውና ፆሞ እንደማይፈስክ ሰው ዓይነት ነው፡፡» (ቡኻሪ 5661)፡፡

> እስልምና ለሴት ልጅ በተከበረው ፍትሐዊ ክፍፍል የውርስ መብቷን አጎናጽፏታል፡፡ ሴት ልጅ በተወሰኑ የውርስ ክፍፍል ሁኔታዎች ላይ ከወንዱ እኩል ስትሆን በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ ደግሞ የውርስ ድርሻዋ ከፍና ዝቅ በማለት ከወንዱ የውርስ ድርሻ ጋር ይለያያል፡፡

እስልምና የሴቶችን መብት ይረግጣልና እነሱንም ይጨቁናል እየተባለ በእስልምና ላይ መሰረተ-ቢስ ትችት እየተሰነዘረ፣ ጣት እየተቀሰረ፣ በመገናኛ ብዙሃን ላይ እየተጻፈና እየተለፈፈ ባለበት በአሁኑ ዘመን ወደእስልምና ከሚገቡት 75% የሚሆኑት ሴቶች በስልጣኔ ሌሎች ቀድመዋል ከሚባሉት ሀገራት ውስጥ እንደ እንግሊዝ ካሉ ሀገራት የተገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ወደ እስልምና የገቡ ሴቶች የነበሩበትን ሃይማኖት በመተው እስልምናን የመረጡት ሃይማኖቱ ቤተሰብንና ሴቶችን አስመልክቶ ያስቀመጣቸውን ድንጋጌዎችን በጥልቀት በማጥናት ነበር፡፡ (ኢንዲፔንደንት ጋዜጣ እ.ኤ.አ 6/11/2011 ዓ.ል እትም)፡፡



## እስልምና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ያረጋገጠላቸው ሴቶች፡



**እናት፡** አንድ ሰው ወደአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣና፣ ‹‹የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ከሰዎች መካከል በመልካም መወዳጀቴ የተገባው ሰው ማን ነው?›› በማለት ጠየቃቸው፡፡ እሳቸውም፣ ‹‹እናትህ›› አሉት፡፡ ‹‹ከዚያስ?›› አላቸው፡፡ እሳቸውም፣ ‹‹እናትህ›› አሉት፡፡ አሁንም፣ ‹‹ከዚያስ?›› አላቸው፡፡ እሳቸውም፣ ‹‹እናትህ›› አሉት፡፡ አሁንም፣ ‹‹ከዚያስ?›› አላቸው፡፡ እሳቸውም፣ ‹‹አባትህ›› አሉት፡፡ (ቡኻሪ 5626)፡፡



**ሴት ልጅ፡** የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፣ ‹‹ሶስት ሴት ልጆች ኖረውት በእነርሱ ላይ ትእግስት ካደረገ፣ ካበላቸው፣ ካጠጣቸውና ከሚያገኘው ካለበሳቸው በትንሳኤ ቀን ከእሳት ግርዶ ይሆኑለታል፡፡›› (ኢብን ማጀህ 3669)፡፡



**ሚስት፡** የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፣ ‹‹ከእናንተ መካከል መልካሙ ለቤተሰቡ መልካም የሆነ ነው፡፡ እኔ ለቤተሰቤ መልካም ነኝ፡፡›› (አት-ቲርሚዚይ 3895)፡፡



> በእስልምና የወንድና የሴት ግንኙነት ሙስሊም ማሕበረሰብ በመገንባት ረገድ አንዳቸው የአንዳቸውን ክፍተት የሚሞሉበት ግንኙነት እንጂ የጦርነት ግንኙነት አይደለም፡፡

## በሁለቱ ጾታዎች መካከል የሚደረግ ግብግብ በእስልምና ቦታ የለውም፡

በሁለቱ ጾታዎች መካከል የሚደረግ ግጭትና ግብግብ በእስልምና ቦታ የለውም፡፡ ለምድራዊ ዓለም ጥቅም የሚደረግ ሽቅድምደም ትርጉም አልባ ነው፡፡ ለወንዶች ወይም ለሴቶች ተብሎ የሚደረግ ሩጫና ከአንዳቸው ጥቅም ለማግኘት ወይም አንዳቸውን ለማቅለል ድክመታቸውን መከታተል በእስልምና ቦታ የለውም፡፡

እንዴት ሆኖ ነው የሰው ልጅ የእሱን ግማሽ አካል ከሆነ ነገር ጋር የሚጣላው? እንዴትስ ሆኖ ነው አካል ከአካሉ ጋር ግብግብ የሚፈጥረው? የተከበሩት መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንደተናገሩት ሴት የወንድ ሌላኛዋ ግማሽ አካል ነች፡፡ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት ሙስሊም ማህበረሰብ ለመፍጠር አንዱ የአንዱን ጉድለት እያሟላ የሚኖርበትና አንዱ የሌላውን ክፍተት የሚዘጋበት ነገር ነው፡፡

ቁርአን ይህን ሁኔታ ውብ በሆነ አገላለጽ እንዲህ ያስቀምጠዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፣ ‹‹እነርሱ ለናንተ ልብሶች ናቸው፤ እናንተም ለነርሱ ልብሶች ናችሁ፡፡›› (2፡187)፡፡

አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት ላይ በቅድሚያ የሚመለከተው ደካማነቷን ነው፡፡ ነገር ግን ቤተሰቡ በሙሉ ከእሷ የሚፈለገው እሱ የማያውቀው በርካታ ጠንካራና ብርቱ ሃይል ሊኖራት ይችላል፡፡ እሷ ከወንዱ ላይ የምትመለከተው ድክመት ምናልባት ለእርሷ የማይመጥኑ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ካለ እሷ ሕይወትም ማህበረሰብም ሊስተካከል አይችልም፡፡

አላህ ለሰው ልጅ አፈጣጠር (ወንድና ሴት) የሚል ሁለት ዓይነት ጾታ ከፈጠረ በኋላ ሁለቱም በሁሉም ነገሮች ፍጹም ተመሳሳይ መሆናቸው የግድ ነው ብሎ መናገር ቀልድ ነው፡፡

አንዳንድ ወንዶች ለሴቶች የተሰጣቸውን መብቶች መመኘት ሲጀምሩ በአንጻሩ አንዳንድ ሴቶች ለወንዶች የተሰጧቸውን መብቶች እንዲሁ መመኘት ሲጀምሩ እንዲህ የሚል የቁርአን አንቀጽ ወረደ፣«ለወንዶች ከሠሩት ሥራ እድል አላቸው፡፡ ለሴቶችም ከሰሩት ሥራ እድል አላቸው፡፡ አላህንም ከችሮታው ለምኑት፡፡» (4፡32)፡፡ ለሁሉም የየራሱ ተግባራት፣መለያዎችና ክብሮች አሉት፡፡ ሁሉም የአላህን ውዴታና ችሮታ ለማግኘት በየፊናው በተሰጠው ሚና ላይ ይተጋል፡፡ ይህ የእስልምና ድንጋጌ ለወንዶች ወይም ለሴቶች ብቻ አልተደነገገም፡፡ በአንጻሩ ለሰው ልጆች፣ለቤተሰብና ለሙስሊሙ ማህበረሰብ በሙሉ ነው፡፡

## በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚኖር ግንኙነት፡

በወንዶችና በሴቶች መካከል ሊኖር የሚችለውን ግንኙነት ስርአት ያለው ለማድረግ በርካታ ሕጎችና ስርአቶች ሲቀረጹና ሲደነገጉ ቆይተዋል፡፡ በታሪክ ሂደት የሰው ልጆች ምርጫዎችና ፍላጎቶች እየጨመሩ ሲሄዱ ግንኙነቶቹን መወሰንና መገደብ እየከበደ መጣ፡፡ ነገር ግን የታሪክ ድርሳናትና የአንትሮፖሎጂ ጥናቶች እርቃን ሆኖ መታየትን፣ ጾታዊ ልቅነትንና ግልጽ ወሲባዊ ግንኙነትን የሚደግፉና የሚያራምዱ እንዲሁም ለሴት ልጅ በመፍራት እሷን በእግረ-ብረት የሚያስሩ ሕዝቦች እንደነበሩ ይነግሩናል፡፡ ከዚህ ሌላ ሴቶች ሳይሆኑ ወንዶች ብቻ እንዲሸፈኑ ወይም የተወሰነውን የሰውነት አካል እንዲሸፈን የሚያደርጉና ሌሎች ለመግለጽ የሚያስችግሩ ድርጊቶችን የሚፈጽሙ ሕዝቦችም ተከስተው እንደነበር እንዲሁ ይነግሩናል፡፡

ከእነዚህ ሕዝቦች መካከል -በተለይ በስልጣኔ ቀደምት ናቸው የሚባሉት- የሰው ልጅ ከሰውነት ወጥቶ ወደእንስሳነት እንዳይቀየርና በሰው ልጅና በእንስሳት መካከል ምንም ልዩነት የለም የሚባለው ደረጃ ላይ እንዳይደረስ በመፍራት ይህን ሁኔታ ፈርና ስርአት ለማስያዝ ሕግ እንደሚያስፈልግ ያምኑ ነበር፡፡

LAUNCHING
CURiOSiTY
CLICK HERE




" ከእነዚህ ሕዝቦች መካከል -በተለይ በስልጣኔ ቀደምት ናቸው የሚባሉት- የሰው ልጅ ከሰውነት ወጥቶ ወደእንስሳነት እንዳይቀየርና በሰው ልጅና በእንስሳት መካከል ምንም ልዩነት የለም የሚባለው ደረጃ ላይ እንዳይደረስ በመፍራት ይህን ሁኔታ ፈርና ስርአት ለማስያዝ ሕግ እንደሚያስፈልግ ያምኑ ነበር፡፡



## በወንድና በሴት መካከል የሚኖር ተፈጥሯዊ ግንኙነት በእስልምና፡

በእስልምና የሴቶችና የወንዶች ግንኙነት በታሪክና በመልከአ- ምድራዊ የተከለለ የሰው ልጅ የጥረት ውጤት ሳይሆን ለሁሉም ስፍራና ጊዜ የሚያገለግል አላህ ያወረደውና የተከበሩት መልዕክተኛ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ለሰዎች ያስተማሩት ስርአት ነው፡፡ ወንዶችና ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ካላቸው ስፍራዎች አንጻር በሁለቱ ጾታዎች መካከል ያሉት እነዚህ የግንኙነት ጠባዮችና ወሰኖች ይለያያሉ፡፡

እስልምና ግልጽ አድርጎ እንሚያስቀምጠው ይህ ግንኙነት ጠባዩና ወሰኑ ሴቶች ከወንዶች አንጻር ካላቸው ስፍራ አንጻር ይለያያል፡፡

በእስልምና ወንዶች ከሴቶችጋር ካላቸው ግንኙነት አንጻር በተለያዩ ደረጃዎች ይከፈላሉ፡

1. ወንዱ ባሏ መሆን አለበት፡-

በባልና ሚስት መካከል ሊኖር የሚችለውን ደስታ፣ እርካታ፣ መተዛዘን የተሞላበትንና አካላዊ ቁርኝት የሰፈነበትን የተባረከ ግንኙነት እንደ ቁርአን ባማረና ርቱእ በሆነ የቋንቋ አገላለጽ ያስቀመጠ ማንም የለም፡፡ ይኸውም አላህ ባልን ለሚስቱ ልብስ ነው በማለት ሲሰይም፣ ሚስትንም እንዲሁ ለባሏ ልብስ ነች በማለት ሰይሟል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፣ «እነርሱ ለናንተ ልብሶች ናቸው፤ እናንተም ለነርሱ ልብሶች ናችሁ፤» (2፡187)

2. ከሙሕሪሞቿ መካከል አንዱ መሆን አለበት፡

ክልከላዎች የሚለው ሃሳብ የሚያመለክተው በዝምድና ግንኙነት ሳቢያ እስከወዲያኛው ከእሷ ጋር ጋብቻ መፈጸማቸው ክልክል የሚሆንባቸው ወንዶች ሲሆኑ በቁጥር 13 ናቸው፡፡ እነርሱም፡- አባት፣ እናት፣ ልጅ፣ ወንድም፣ አኅት በአባት በኩል፣ አኅት በእናት በኩል፣ የወንድም ወይም የእህት ልጅ፣ የወንድ ልጅ ልጅ ወይም የሴት ልጅ ልጅ ወ.ዘ.ተ ናቸው፡፡ አንዲት ሴት ክልክል በሚሆኑት ዘመዶቿ ፊት ሙሉ ሒጃብ ሳታደርግ ልትታይ የምትችል ሲሆን ይህም ሐፍረተ-ገላዋን ሳትገልጥ በተፈጥሯዊ ሁኔታዋ ነው፡፡

3. ወንዱ ለእሷ ባዕድ የሆነ ወንድ መሆን አለበት፡

ባዕድ ወንድ ማለት ለሴቷ ሙሕሪም ያልሆነ ወንድ ማለት ነው፡፡

ባይተዋር በሆኑ ሴቶችና ወንዶች መካከል ለሚኖር ግንኙነት እስልምና ሕግና ስርአቶችን በሚገባ አስቀምጧል፡፡ ይህን ያደረገውም ክብርን ለመጠበቅና ሰይጣን በሰው ልጅ ላይ የሚሰርጽበትን መንገድ ቀድሞውኑ ለመዝጋት ነው፡፡ ከፈጠረው አላህ ይበልጥ ለሰው ልጅ የሚበጀውን የሚያውቅ ይኖር ይሆን? ቁርአን እንዲህ አስፍሯል፤ ‹‹የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀት ረቂቁ፣ ውስጥ ዐዋቂው ሲኾን (ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን?›› (አል-ሙልክ ፡ 14)



## እስልምና ባዕድ ወንዶች ፊት ሒጃብን ለምን ደነገገ?

- ሴቷ በሕይወት፣ በማህበረሰቡ፣ በሥራና በዕውቀት መስኮች ውስጥ ያላትን ተልዕኮ ክብሯንና እሷነቷን ጠብቃ ከግብ እንድታደርስ ነው፡፡

- በአንድ በኩል ማህበረሰቡን ከስሜታዊና ግብታዊ እንቅስቃሴዎች ለማጥራት ዋስትና ለማስቀመጥ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሴት ልጅን ክብር ለመጠበቅ ነው፡፡

- የሴቶችን ክብር ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ወንዶች በሚያደርጉት እንቅስቃሴ እገዛ ለማድረግና ወንዶች ከሴቶች ጋር እለታዊ ግንኙነት ሲያደርጉ ሴቶችን እንደእንስሳ እንዳይመለከቱ በአንጻሩ በዕውቀትና ትምህርት ዘርፍ በርካታ ጠንካራ ነገሮች ማግኘት እንደሚችሉ አድርገው እንዲገምቱ ለማድረግ እንዲሁም ሴቶች የተከማቸን የስሜት ቁልል ማራገፊያና መደሰቻ ቁስ እንዳልሆኑ ለማረጋገጥ ነው፡፡

## በባዕድ ሴትና ወንድ መካከል ሊኖር የሚችል የግንኙነት ስርአት

### 1 ዓይን ያልተፈቀደለትን ነገር እንዳይመለከት መከልከል፡-

ሁለቱም ፆታዎች ዐይኖቻቸውን እንዲሰብሩ ማለትም ያልተፈቀደላቸውንና ወሲባዊ ስሜትን የሚያነሳሳ ነገሮችን እንዳይመለከቱ አዟል፡፡ ምክንያቱም ይህ የራስን ክብር ለመጠበቅ፣ ከጸያፍ ነገሮች ጥብቅ ለመሆን አብይ መንገድ ስለሆነ ነው፡፡ በተቃራኒው ዐይኖችን ካለወሰን እንዲያው መልቀቅ ለወንጀልና ለሃጢአት መንገድ ነው፡፡ ቁርአን እንዲህ የሚል አንቀጽ አስፍሯል፤ ‹ለምእመናን ንገራቸው፡- ዓይኖቻቸውን (ያልተፈቀደን ከማየት) ይከልክሉ፤ ብልቶቻቸውንም ይጠብቁ፤ ይህ ለነሱ የተሻለ ነው፤ አላህ በሚሠሩት ሁሉ ውስጥ ዐዋቂ ነው፡፡ ለምእምናትም ንገራቸው፡- ዓይኖቻቸውን ይከልክሉ፡፡ ብልቶቻቸውንም ይጠብቁ፡፡› (አን-ኑር ፡ 30 -31)

### 2 በስነ-ምግባርና በስነ-ስርአት መገናኘት፡

ወንድና ሴት እንደዕውቀት፣ ሥራና ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉት በርካታ ጉዳዮች ላይ ይገናኛሉ፡፡ ሲገናኙ ግን ክብርንና በማንኛውም መንገድ ስሜትን ከሚቀሰቅሱ ነገሮች በመራቅ መሆን አለበት፡፡



## 3 ሒጃብ

ስሜት የሚቀሰቅሱና ወብትና አጉልተው የሚያሳዩ ነገሮችን ለመሸፈን አላህ ሒጃብን (ሰውነትን መሸፋፈንን) በወንዶች ላይ ሳይሆን በሴቶች ላይ ግዴታ አድርጓል፡፡ በተለይ ይህን ሒጃብ በሴቶች ላይ ግዴታ ያደረገው አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች ከወንዶች ይበልጥ በውበታቸው ለፈተናዎች የተጋለጡ በመሆናቸው እነርሱን ከእንዲህ ዓይነቱ ፈተና ለመታደግ ነው፡፡ ከጥንት ጀምሮ እስከአሁኑ ጊዜ የምንመለከተው በየመድረኩና በተለያዩ መገናኛ ብዙሃኑ ሴቶች የወንዶችን ወሲባዊ ስሜት ማነሳሻ ዋነኛ ዘዴ ሆነው እንደሚቀርቡ ነው፡፡

በእስልምና የሒጃብ ወሰኑ አንዲት ሴት በባይተዋር ወንዶች ፊት ቁርአን እንዳዘዘው ከፊቷና ከመዳፎቿ በስተቀር ሰውነቷን ባጠቃላይ መሸፈኗ ነው፡፡ « ጌጣቸውንም ከእርሷ ግልጽ ከኾነው በስተቀር አይግለጡ፡፡» (አን-ኑር ፡ 31)፡፡



“

በእስልምና የተደነገገውን የሒጃብ ድንጋጌ የሚተቹ በርካታ ሰዎች በዓለም ላይ ከነበሩና ካሉ እንስቶች የተከበረችው እንስት የድንግል ማርያም (መርየም) እንኳ በምስሎች ላይ የሙስሊም ሴቶችን አለባበስ በመሰለ ሒጃብ እንጂ ካለሒጃብ እንዳልቀረበችና እንደማትቀርብ ፈጽሞ ይዘነጋሉ፡፡



# እስላማዊው ሕግ በምግብና በመጠጥ ላይ



እስልምናን ለማጥናት የሚነሳ ሰው ምንጊዜም በቅድሚያ የሚያነሳው ጥያቄ፡ ‹‹ሙስሊሞች አስካሪ መጠጦችንና የአሳማ ስጋን ለምንድን ነው ክልክል የሚያደርጉት?›› የሚል ነው፡፡



ይ ይህን ለመመለስ ግልጽና አንገብጋቢ የሆኑ ማብራሪያዎችን ማስቀመጥ ግድ ይላል፡፡

ቁርአን በምድር ላይ ያሉትን ነገሮች ለሙስሊሞች መጠቀሚያ ፈቅዷል፡፡በምድር ላይ ያሉ ነገሮች በአጠቃላይ ለእኛ የተፈጠሩ መሆናቸውን ግልጽ በሆነና በማያሻማ ሁኔታ የቁርአን ድንጋጌ ተቀምጧል (2፡29)፡፡

በጤንነት ላይ ከሚያደርሱት ጉዳት፣ከቆሻሻነታቸውና በአእምሮ ላይ ከሚያስከትሉት ቀውስ ቁርአን በግልጽ ካስቀመጣቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በስተቀር ሁሉም ምግቦችና መጠጦች ለኛ የተፈቀዱ ናቸው፡፡ምናልባት አስካሪ መጠጦችና የአሳማ ስጋ ለምን ክልክል እንደሆኑ ለማወቅ ሊያሳስብህ ይችላል፤እንግዲያውስ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አስተውል፡፡

## አሳማ፡

በወቅቱ በዐረቦች ዘንድ አሳማ የሚታወቅ ባይሆንም የአሳማ ስጋን መብላትን አስመለክቶ በቁርአን ግልጽ የሆነ ክልከላ ሰፍሯል፡፡ አንዳንዶች ይህን ክልከላ ሲመለከቱ በጣም ይገረማሉ፡፡ ይህ ክልከላ ለሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን በአይሁዶች ዘንድም ክልክል የሆነ ድንጋጌ ነው፡፡ ክልከላውን በግልጽ የሚያመለክቱ አንቀጾች በብሉይ ኪዳን ሰፍረዋል፡፡ በጣም የሚገርመው ግን የበርካታ ሃይማኖት ምሁራን የአሳማ ስጋ በእነሱ ዘንድም ክልክል መሆኑን መናገራቸውና ማረጋገጣቸው ነው፡፡ በክርስትና ሃይማኖትም በአዲስ ኪዳን ግልጽ የሆኑ አንቀጾች ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ አንቀጾች ተበርዘዋል፣ ተለውጠዋልም፡፡ ለምሳሌ ያህል ማርቆስ ምዕ. 5፡ 11-13፣ ማቴዎስ ፡ 67፣ የጴጥሮስ መልእክት 2 ፡ 22፣ ሉቃስ ምዕ. 15 ፡ 11 መመልከት ይቻላል፡፡

አዳምን (ዐ.ሰ) አላህ ገነት ውስጥ ከሚገኙት መልካም ምግቦች እንዲመገብ ከፈቀደለት በኋላ ያቺን ዛፍ እንዳይበላ እንደከለከለው ሁሉ ለእኛም ሁሉን ነገሮች እንድንመገብ ከፈቀደልን በኋላ የእምነታችንንና ለእሱ ያለንን ታዛዥነት ደረጃ ለመፈተን ብሎ አንዳንድ ነገሮችን የሚከለክልበት ምን ምክንያት አለ?

አብዛኛዎቹን የምግብ ዓይነቶች በምግብነት ከፈቀደልን ከምግቦቹ መካከል አንዱን በመከልከል አላህ እኛን መፈተኑን የሚከለክለው ነገር ምንድነው? አላህ ይህን የሚያደርገው ልክ አዳምን -በእሳቸው ላይ ሰላም ይሁን- የጀነትን መልካም ነገሮች ሁሉ ከፈቀደላቸው በኋላ ያችን የተለየች የሆነችውን ዛፍ እንዳይመገቡ እንደፈተናቸው የእኛንም እምነትና ለእሱ ያለንን ታዛዥነት ለመፈተን ነው፡፡



## የአልኮል መጠጦች

የሰው ልጆችን ሕይወትና ጤናን አደጋ ላይ የሚጥሉ ነገሮችን ለመከላከል ሕጎችን፣ አዋጆችንና ደንቦችን የማዘጋጀትና የመደንገግ ግዴታ የየሀገሮቹ መንግስታት ከሚያከናውኗቸው ዋና ዋና ተግባራት መካከል አንዱ ነው፡፡ በእነርሱ መካከል የሚፈጠር ክፍተት መጥፎ ተጽእኖውን በግለሰብና በሕብረተሰቡ ላይ ያሳርፋል፡፡



ለምሳሌ እንደ ዓለም አቀፉ የጤና ተቋምና ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ እ.ኤ.አ ማርች 15 ቀን 2012 ዓ.ል ኔቸር በተሰኘው መጽሔት ቁጥር 483 ላይ እንዳወጣው ዓይነት አንዳንድ የሚጠኑ ጥናቶች የሚሰጡን መረጃዎች ለሁላችንም አስደንጋጭ ናቸው፡፡

የዓለም አቀፉ የጤና ተቋም እ.ኤ.አ ባወጣው ዘገባ በአልኮል መጠጥ ምክንያት በየዓመቱ ከሚሞቱ ሰዎች ቁጥር በኤድስ፣ በወባና በሳንባ ነቀርሳ በሽታዎች፣ በጅምላ ጭፍጨፋና በሽብር ጥቃት ከሚሞቱት ሰዎች ቁጥር በሶስት እጥፍ እንደሚበልጥ በማረጋገጥ ዘግቧል፡፡ እነዚህ ጥናቶች የደረሱባቸውንና ዓለም አቀፉ የጤና ተቋም ይፋ ባደረገው ዘገባ ላይ የቀረቡትን አኃዛዊ መረጃዎች ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡




ዓለም ላይ በዓመት ውስጥ በአልኮልና በአልኮል መጠጥ ሱስ ምክንያት ከሚሞቱት አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሰዎች መካከል ከ15-29 ዓመት ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ 320,000 ወጣቶች ሕይወታቸውን ያጣሉ፡፡ ይህም በዓለም ላይ በዓመት ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ከሚሞቱት ሰዎች በአልኮል መጠጥ ምክንያት የሚሞቱት ወጣቶች ቁጥር በመቶኛ ሲቀመጥ 9% ነው፡፡





አሜሪካ ውስጥ የተደረገ ጥናት እንደሚያስረዳው 700,000 የሚሆኑ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በአልኮል መጠጥ በተሸነፉ ተማሪዎች ጉዳት ይደርስባቸዋል፡፡






እ.ኤ.አበ2001 በጽሑፍ የሰፈረ አንድ ሰነድ ይፋ እንዳደረገው እስቶኒያ ውስጥ በዓመት በወጣቶች ከሚፈጸሙ ወንጀሎች ውስጥ 80% የሚሆኑት የሚፈጸሙት ከአልኮል ጋር በተቆራኙ ወጣቶች ነው፡፡






በዓለማችን ላይ ከሚፈጸሙ ወንጀሎች መካከል ሩብ ያህሉ የሚፈጸሙት ከአልኮል መጠጥ ጋር በተያያዘ ምክንያት ነው፡፡







በአጠቃላይ የዓለም አቀፉ የጤና ተቋም ዘገባዎች በአልኮል መጠጥ ምክንያት የሚከሰቱ አደጋዎችንና ችግሮችን ለመከላከልና ለመቀነስ ሁሉም ሀገራት ተገቢውን ሕግና ስርአት መደንገግ እንዳለባቸው በማሳሰብ ተገቢውን ሁሉ ያደርጉ ዘንድ ጥሪ ያቀርባሉ፡፡



## እንግሊዝ ውስጥ በአንድ ዓመት ብቻ፡፡

- ከአልኮል መጠጥ ጋር በተያያዘ አንድ ሚሊዮን የወንጀል ድርጊቶች ተፈጽመዋል፡፡ እንደ አጠቃላይ ግማሽ ሚሊዮን የሚሆኑት የወንጀል ድርጊቶች የሚፈጸሙት ከአልኮል መጠጥ ጋር በተያያዘ ምክንያት እንደሆነ በወንጀሎቹ ተጎጆዎች የሆኑ ሰዎችን አስተያየት በመጥቀስ መረጃዎች አረጋግጠዋል፡፡

- በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ ከአልኮል መጠጥ ጋር በተያያዘ 7 ሚሊዮን ድንገተኛ የሆኑና ድንገተኛ ያልሆኑ አደጋዎች ይከሰታሉ፡፡ በዚህ ሳቢያም እንግሊዝ 650 ሚሊዮን ፖውንድ የሚሆን የታክስ ገቢ ታጣለች፡፡

- በአጠቃላይ እንግሊዝ ከአልኮል መጠጥ ጋር በተያያዘ በሚፈጸሙ ወንጀሎችና ሁከቶች 13.8 ቢሊዮን ፓውንድ የሚጠጋ የታክስ ገቢ ታጣለች፡፡



## ቁርአን የአልኮል መጠጥን ያስተናገደው እንዴት ነበር?

እስልምና የአልኮል መጠጥ በግለሰቦችና በሕብረተሰቡ ላይ የሚያደርሰውን ተጽእኖ ለማወቅ የዓለም አቀፉን የጤና ተቋም ዘገባ መጠበቅ አላስፈለገውም፡፡ በእርግጥ የሰው ልጅን የፈጠረ ለሰው ልጅ በሕይወቱ ሳለ እሱንና ሕብረተሰቡን ምን እንደሚጠቅመውና ምንስ እንደሚጎዳው ጠንቅቆ ያውቅለታል፡፡

እስልምና ዓረቦች ከአልኮል መጠጥ ፈጽሞ የማይላቀቁ በሆኑበት፣የተለያዩ የአልኮል መጠጦችን ትልቁ የደስታቸው ምንጭ አድርገው በሚቆጥሩበትና በርካታ ሀብታቸውን በእሱ ላይ እያባከኑ በሚፎካከሩበት ወቅት ላይ ነበር ወደነርሱ ዘንድ የመጣው፡፡

ቁርአን ሁኔታውን በቀስታና በሎጂካዊ አካሄድ በፍትሕ ተመልክቶታል፡፡ በአልኮል መጠጥ ላይ ያለውን ጠቀሜታ ሲያረጋግጥ የሚጠጣው ሰው ለጊዜው ደስታን ያጎናጽፋል፣ ሃሳቡና ጭንቀቱ እልም ብሎ ይጠፋል፡፡ ነገር ግን የመጠጥ ፍጻሜው በጣም አሳፋሪና አዋራጅ እንዲሁም የሚያስከትለውን ጠባሳ ማከም በጣም ከባድ እንደሆነ በሰው ልጅ ስነ-ልቦና፣ ስነ-ምግባር፣ በግለሰብና ማሕበረሰብ ዘንድ የሚያመጣውን የጤና ቀውስ ተናግሮ ነው፡፡ ቁርአን እንዲህ አስፍሯል፤ «አእምሮን ከሚቃወም መጠጥና ከቁማር ይጠይቁሃል፡፡ በሁለቱም ውስጥ ታላቅ ኃጢአትና ለሰዎች ጥቅሞች አሉባቸው፡፡ ግን ኃጢአታቸው ከጥቅማቸው በጣም ትልቅ ነው» በላቸው፡፡» (አል-በቀራህ ፡ 219)

ከዚያ በኋላ መጠጥ ክልክል እንደሆነና ከሰይጣን ተግባራት መካከልም አንዱ እንደሆነ እንዲሁም በሰዎች መካከል ጠላትነትን፣ ጥላቻን ከመፍጠሩ ባሻገር መልካምና የላቁ ተግባራትን ፈጽሞ ለማከናውን ትልቅ እንቅፋት እንደሚሆን በማስረገጥ ደነገገ፡፡ ሰዎችንም በቁርአን ውስጥ አላህ፣ «ታዲያ እናንተ (ከነዚህ) ተከልካዮች ናችሁን?» (5፡90) አላቸው፡፡ ሰዎችም፣ «እንዴታ! እንዴታ! ተከልክለናል... ተከልክለናል» አሉ፡፡ አላህ በቁርአን ላይ ላስተላለፈው ትእዛዝ ፍጹም ታዛዥነት ተጠምቀው የነበሩ በርካታ የአልኮል መጠጦች በመደፋታቸው የመዲና መንገዶች በአልኮል መጠጥ ጎርፍ ተጥለቀለቁ፡፡

# ሐጢአት እና ንስሐ



# የስሕተትና

የስሕተትና የትክክለኛነት ፍልስፍና በበርካታ እምነቶችና ሃይማኖቶች ውስጥ ብዥታን የሚፈጠር ነገር ነው፡፡ እምነቶቹም ሆኑ ሃይማኖቶቹ ከስህተት፣ከሐጢኣት፣ከንሰሐና ከጸጸት ጋር ያላቸው ግንኙነቶች እንደ እምነቶቹና ሃይማኖቶቹ ይለያያሉ፡፡



እስልምና የሰው ልጅን ተፈጥሯዊ ጠባይ አላህ በፈጠረው ሁኔታ፣ የመልካምነትንና መጥፎነትን ክፍፍል መሰረት አድርጎ በረቀቀና ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ ይመለከታል፡፡ የሰው ልጅን ልክ ጽድቅ ተግባር ይፈጽም ዘንድ እንደተገደደ መልአክ አድርጎ አይመለከትም፡፡ የሰው ልጅ ባጠቃላይ ስሕተተኛ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ ነገር ግን በአንጻሩ በውሳኔውና በምርጫው ላይ ሃላፊነትን ያሸክመዋል፡፡ ከዚህ በመነሳትም የእስልምና የሃጢአትና የንሰሐ ጽንሰ-ሃሳብ ይመነጫል፡፡ ይህንንም በሚከተለው አኳኋን አጠር ባለ መልኩ መመልከት ይቻላል፡፡

- ቁርአን ላይ በቅድሚያ የሚገጥመን እንዲሁም ግልጽ በሆነ መልኩ የተቀመጠውና ምንም ውስበስብነት የሌለበት ነገር ሃጢአትም ሆነ ንሰሐ ግለሰባዊ እንደሆነ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከመወለዱ በፊት ምንም ዓይነት ሃጢአት አልነበረበትም፡፡ ሁሉም የሰው ልጅ ከሃጢአት የጸዳ ሆኖ ይወለዳል፡፡ ከዚያ በፊት ምንም ሃጢአት አይሸከምም፡፡

ማንኛውም ሰው እንዲሁ ሃጢአትን የማሰረይ፣ ወንጀሎችን ይቅር የማለት መብትም የለውም፡፡ የሰው ልጆች አባት አደም (በእሳቸው ላይ ሰላም ይሁን) ሃጢአት የግላቸው ሃጢአት ነው፡፡ ከዚህ ሃጢአት መጽዳት የሚቻለው በቅርብ በቀላሉ ንስሐ ማድረግ ነው፡፡ የአደም ልጆቻቸው የእያንዳንዳቸው ሃጢአት እንዲሁ የየግላቸው ነው፡፡ ለንሰሐ በሩ ዝግ ሳይሆን ዘውትር ክፍት ነው፡፡ ይህም ለሰው ልጅ በማያሻማ ሁኔታ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ተብራርቷል፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ አቅሙ የፈቀደለትን ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡ ተስፋ መቁረጥና ተስፋውን ማጨለም የለበትም፡፡ እስልምና ለእያንዳንዱ የሰው ልጅ የየራሱን ሃጢአትና ወንጀል እንዲሸከም አድርጓል፡፡ አንዱ በፈጸመው ሃጢአትና ወንጀል ሌላው አይጠየቅም፣ አይሸከምም፡፡ ይህ መርሕ ነቢያት ሁሉ ከአላህ ይዘውት የመጡት መርሕ መሆኑን ቁርአን እንዲህ በማለት ገልጾልናል፤ ((ይልቁንም በዚያ በሙሳ ጽሑፎች ውስጥ ባለው ነገር አልተነገረምን? በዚያም (የታዘዘውን) በፈጸመው በኢብራሂም (ጽሑፎች ውስጥ ባለው አልተነገረምን?)፡፡ (እርሱም ኃጢያት) ተሸካሚ ነፍስ የሌላይቱን ነፍስ ኃጢአት አትሸከምም፡፡ ለሰውም ሁሉ የሠራው እንጅ ሌላ የለውም፡፡ ሥራውም ሁሉ ወደ ፊት ይታያል፡፡ ከዚያም ሙሉውን ምንዳ ይመነዳዋል፡፡)) (አን-ነጅም ፡ 36-41)

> አንድ ሰው በሰራው ሃጢአት ተጸጽቶ ከሃጢአቱ በመላቀቅ፣ በሰራው ሃጢአትም በመጸጸት ዳግም እንደማይመለስ ቃል ከማስገባት፣ የሰዎችን ሐቅ እንዲመልስ ከማድረግ ውጭ ንስሐ በእስልምና ሌላ ተጨማሪ መሰፈርቶችን አይፈልገም፡፡



- ንስሐ ከታላላቅ አምልኮታዊ ተግባራት አንዱ ነው፡፡ ወደአላህ ዘንድ መቃረቢያም ነው፡፡ በርሱም የሰው ልጆች አንዳቸው ከአንዳቸው የተለየ አይደለም፡፡ ንስሐ ምንም ዓይነት ልዩ ስፍራና ለየት ለሚሉ ሰዎች መናገርን እንዲሁም የሌሎችን ፈቃድ ፈጽሞ አይፈልግም አይጠይቅምም፡፡ በአንጻሩ በአላህና በባሪያዎቹ መካከል የሚፈጸም አምልኮታዊ ተግባር ነው፡፡ በቁርአን ውስጥ ከሰፈሩት የአላህ መልካም ስሞችና መገለጫዎች መካከል ((በእጅጉ ንሰሐን ተቀባይና እጅግ አዛኝ))፣ ((ወንጀልን መሐሪ ንሰሕን ተቀባይ)) የሚሉ መገለጫዎችና ስሞች ይገኛሉ፡፡ ቁርአን ጀነት የሚገቡትን እነዚያ አላህን በእጅጉ የሚፈሩ የሆኑ ፈሪሃንን መገለጫ ሲነግረን እነዚህ ሰዎች እንኳ የተወሰኑ ወንጀሎችን እንደሚፈጽሙ ነገር ግን ከእያንዳንዱ

ወንጀል ወደንሰሐ እንደሚቻኮሉና የአላህን ምሕረት እንደሚጠይቁ ይገልጽልናል፡፡ ((ለእነዚያም መጥፎ ሥራን በሠሩ ወይም ነፍሶቻቸውን በበደሉ ጊዜ አላህን የሚያስታውሱና ለኀጢአቶቻቸው ምሕረትን የሚለምኑ ለኾኑት ከአላህም ሌላ ኀጢአቶችን የሚምር አንድም የለ፡፡ (በስሕተት) በሠሩትም ላይ እነርሱ የሚያውቁ ሲኾኑ የማይዘወትሩ ለኾኑት (ተደግሳለች)፡፡›› (አል-ዒምራን ፡ 135)

በእስልምና ንሰሐ ሃጢአተኛው ከተዘፈቀበት ሃጢአት መውጣቱን ፣ በፈጸመው ሃጢአትም መጸጸቱን፣ ይፈጽመው ወደነበረው ሃጢአት አለመመለስ ላይ ጽኑ አቋም መያዙን እንዲሁም የሰዎችን ንብረት ወደባለቤቶቹ መመለሱን ብቻ እንጂ ከዚህ የበዛ አሊያም የበለጠ ነገርን ከሃጢአተኛው አይጠይቅም፡፡ ነገር ግን ሃጢአተኛው ወደ ሃጢአቱ ከተመለሰና ሃጢአቱን ከደገመ የመጀመሪያው ንሰሐ ውድቅ አይደረግበትም፡፡ የመጀመሪያው ሃጢአት ከቀጣዩ ጋር አይጣመርም፡፡ ነገር ግን ይህ ሰው አዲስ ሃጢአት የፈጸመ በመሆኑ ዳግመኛ ንሰሐ ማድረግ ግድ ይለዋል፡፡

በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የሰው ልጅ በእስልምና ውስጥ ሚዛናዊ ሆኖ ይኖራል፡፡ ይኸውም ምሉእነትንና የላቀ ደረጃን በመፈለግና ከሃጢአቶች በመራቅ እንዲሁም ደካማ የሆነውን የሰው ልጅን ተፈጥሯዊ ጠባይ በማወቅ ምናልባትም በዚህ ደካማ ተፈጥሯዊ ጠባይ ቀናውን መንገድ መሳት እንዳለ በማወቅ መካከል ይኖራል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በማንኛውም ሁኔታና እንቅስቃሴው፣ አላህን በመፍራቱ ወይም ግዴታ የተደረገበትን ተግባር በማጓደሉ ወይም ቅኑን መንገድ በመሳቱ ወደቀናው መንገድ የሚያመለክተውን ኮምፓስ ማጣት የለበትም፡፡ እንዲያውም ወደአላህ በመጠጋት ወደርሱ ንሰሐ ሊገባና ከእርሱም ምሕረትን ሊጠይቅ ይገባል፡፡

እዚህ ላይ ቁርኣን እንደሚነግረን መልካም በሆኑ ሰዎችና በሌሎች መካከል ልዩነት እንዳለ መታወቅ አለበት፡፡ ይኸውም መልካም የሆኑ ሰዎች ምንጊዜም ሐጢአት ሲፈጽሙ ወዲያውኑ አላህን በማስታወስ ንሰሐ በማድረግ ወደርሱ ይመለሳሉ እንጂ ንሰሐ ሳያደርጉ በፈጸሙት ሐጢአት ላይ ሙጭጭ የማይሉ ናቸው (7፡201-202)

> በእስልምና የሰው ልጅ ከመወለዱ በፊት ሃጢአት የመጻፍ መርህ የለውም፡፡ በአንጻሩ የሰው ልጅ ባጠቃላይ ከወንጀሎች የነጻና ከዚያ በፊት ምንም ሃጢአት እንደማይሸከም ያምናል፡፡





# የሃይማኖት እና የአእምሮ ተቃርኖ



አንዳንድ ሰዎች ምንጊዜም ሃይማኖት ከአእምሮ ጋር ፈጽሞ እንደማይጣጣምና አእምሮ ከሚደርስባቸው ሳይንሳዊእውነታዎች ጋር እንደሚቃረን ያስባሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ይህን መሰሉ አስተሳሰብ ሊኖራቸው የቻለው የሃይማኖት ምንጬ ምናባዊ፣ያልተጨበጠና መስረት አልባ ከሆነ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ሳይንስና ፍልስፍና ወደ ፍጥረተ-ዓለሙ እውነተኛነትና ሚዛናዊነት በተጨባጭና በማስረጃ በተደገፈ ሁኔታ በምርምር፣በማስተዋልና በሙከራ መስፈርቶች ላይ ተንተርሰው የሚያደርሱን ነገሮች ናቸው ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰባቸውና እምነታቸው በተወሰነ ደረጃ እውነትነት ያለው ሲሆን በተወሰነ ደረጃ ደግሞ ስሕተት ነው፡፡



እውነታው በርካታ ሃይማኖቶች አንዳንድ ጊዜ አእምሮ ከሚቀበለው አስተሳሰብ ጋር የመስማማታቸው ያህል አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አእምሮ ከሚቀበለው አስተሳሰብ ጋር መቃረናቸው ነው፡፡ የእነዚህ ሃይማኖቶች ምንጮችና መጽሐፍት በምናባዊና ተቀባይነት በሌላቸው ከፍጥረተ-ዓለሙና ከሳይንስ እውነታ ጋር በሚቃረኑና በሚጋጩ አስተሳሰቦች የተሞሉ ናቸው፡፡

ስሕተቱ ደግሞ አንዱን ወይም የተወሰኑ ሃይማኖችን ፍልስፍናና አመለካከት በመመልከት ብቻ ሌሎችም ሃይማኖቶችም እንዲሁ አንድ ዓይነት ፍልስፍናና አመለካካት አላቸው በማለት ሁሉንም ሃይማኖቶች ሳይመረምሩ፣ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ሳያጤኑና ምንጫቸውንም ሳይለዩ ለሁሉም አንድ ዓይነት ፍርድ መስጠቱ ላይ ነው፡፡

> ቁርአንን የሚያነብ ሰው ቁርአን አእምሮ እንዲያስተውልና እንዲያስብ እንደሚያነሳሳ ለአእምሮ ጥሪ እንደሚያቀርብ ለመገንዘብ ጥልቅ የሆነ ምርምርን መጠየቅ አያስፈልገውም፡፡

የእስልምና ዋነኛ ምንጭ የሆነውን ቁርኣንን የሚያነብ ሰው ሌሎች ሃይማኖቶች ለአእምሮ ያልሰጡትን ስፍራ እስልምና እንደሰጠ በእርግጠኛነት ለማወቅ ይችላል፡፡ ቁርኣንን የሚያነብ ሰው እስልምና ለአእምሮ የሰጠውን የላቀ ስፍራ እምብዛም ጥልቅ ፍተሻ ሳያደርግ በቀላሉ ማግኘት ይችላል፡፡ ቁርአን የሰው ልጅ አእምሮውን በመጠቀም ስለምን እንደሚያስተነትን ይጠይቃል፡፡ በተለይ ቁርኣን አታስተነትኑምን? የሚለውን ጥያቄ ከአስር ጊዜያት በላይ ደጋግሞታል፡፡

አእምሮ በተገቢው ሁኔታ ተግባራቱን ማከናወን እንዳለበት ቁርአን በብዙ መንገዶች ገልጿል፡፡ ለአብነት ያህል የተወሰኑትን እንጥቀስ፡-

1



ቁርኣን ከማንኛውም ጭቆና፣ ኩራት፣ ፍራቻና መሐይምነት ነጻና ክፍት የሆነ አእምሮ ያለውን ሰው ያናግራል፡፡በአላህ የማመንን እውነታ በአእምሯዊ ማስረጃና በተለያዩ አመክንዮዎች (ሎጂኮች) ላይ ተመርኩዞ ማወቅ ግዴታ እንደሆነም ያመላክታል፡፡ከነዚህ የቁርኣን ምሳሌዎች መካከል የሚከተለው የቁርኣን አንቀጽ ይገኛል፡፡ ‹‹ወይስ ያለ አንዳች (ፈጣሪ) ተፈጠሩን? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን? ወይስ ሰማያትንና ምድርን ፈጠሩን? አይደለም አያረጋግጡም፡፡›› (52፡ 35-36)

2



የሚያስተባብሉትን ሰዎች ማስረጃዎች ይመረምራል፡፡በማስረጃና በአሳማኝ ሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረቱትን ደግሞ አስተያየታቸውን ወይም አስተሳሰባቸውን ውድቅ ያደርጋል፡፡ እንዲህ በማለት፤‹‹እውነተኞች እንደኾናችሁ አስረጃችሁን አምጡ በላቸው፡፡›› (2፡111)

3



አእምሯቸውን የማያሰሩትን ይወቅሳል፡፡ የስሜት ሕዋሳት እንደሌላቸው አድርጎም ይገልጻቸዋል፡፡ ምክንያቱም ትክክለኛ የሆኑ ውሳኔዎችን መወሰን ወይም ምርጫዎችን መምረጥ ይችሉ ዘንድ ከሚመለከቱትና ከሚሰሙት ነገር አንዳች ነገር አይጠቀሙምና ነው፡፡ ((ለእነርሱም በእነርሱ የሚያውቁባቸው ልቦች ወይም በእነርሱ የሚሰሙባቸው ጆሮዎች ይኖሯቸው ዘንድ በምድር ላይ አይሄዱምን እነሆ ዓይኖች አይታወሩም ግን እነዚያ በደረቶች ውስጥ ያሉት ልቦች ይታወራሉ፡፡)) (አል-ሐጅ ፡ 46)



ለሰው ልጅ አስተሳሰብ እንቅፋት ከሆኑት አስጠንቅቋል፡፡ ቁርአን አእምሯችንንና የስሜት ሕዋሳቶቻችንን በመጠቀምና በማክበር ላይ በማነሳሳት ላይ ሳይገደብ የሰው ልጅን የመልካምና መጥፎ ባሕሪ ክፍፍል ላይ ከሚከሰቱ አእምሯዊ ወለምታዎችን እንድንጠነቀቅ አድርጎናል፡፡ ይኸውም ለአስተሳሰባችን ወሰን ሳይኖረው የምናደርገው ተፈጥሯዊ እሳቤና ምልከታ ለስሕተት ሊያገልጥ፣ በመፈለግም ሆነ በመፍራት ወይም በመሳሳት እውነታን ለመሳት ስለሚዳርግ ነው፡፡

## ለመልካም አስተሳሰቦች እንቅፋት የሆኑትን ነገሮች ቁርአን ሲገልጻቸው፡-

- ባሕል፡- ባሕላዊና ሥነ-ምግባራዊ ውርስ እንዲሁም ኡሉታዊ የሆኑ አስተሳሰባዊ ልምዶች በአእምሮና በአስተሳሳብ ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽእኖዎችን ያሳድራሉ፡፡ ከእነዚህ ጋር እውነታን መቀበልና ሐሴትን መተው ሊከብድ ይችላል፡፡ ምናልባትም ይህ የተወለድኩበት ወይም የለመድኩት ነው በማለት አስተሳሰብን ሊገታ ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ ቁርአን ስለአንዳንድ እውነታው ግልጽ ሆኖላቸው ባሕላቸው እውነታውን ከመከተል የሚከለክላቸው ሰዎች ነበሩ ብሎ እንደሚነግረን ዓይነት ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች አላህ ያወረደውን እውነታ ተከተሉ በተባሉ ጊዜ «እኛ ከአያቶቻችን ያገኘነውንና አባቶቻችን ሲተገብሩት የነበረውን ነው የምንከተለው» ይላሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች አባቶቻቸው በአእምሯቸው ወይም በእውቀት ወይም ቅኑን መንገድ ላይ የሚደገፉ ቢሆኑም ይከተሏቸዋልን? በማለት ከዚያ በኋላ የቁርአን ማሳረጊያ ይመጣል፡፡ (( ለእነርሱም «አላህ ያወረደውን ተከተሉ» በተባሉ ጊዜ «አይደለም አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘንበትን ነገር እንከተላለን» ይላሉ፡፡ አባቶቻቸው ምንም የማያውቁና (ወደ እውነት) የማይመሩም ቢኾኑ (ይከተሉዋቸዋልን?))) (አል-በቀራህ ፡ 170)

- ግትርነትና ኩራት፡- ለማንኛውም ሰው አንዳንድ ጊዜ አእምሮ እውነት የሆነው ነገር ግልጽ ያደርግለታል፡፡ ነገር ግን ጥቅሙንና ክብሩን ለማስጠበቅ አሊያም እውነቱ የተገኘበትን ምንጭ በመናቅ እውነቱን ያስተባብላል፡፡ ይህን አስመልክቶ አላህ እንዲህ ብሏል፤ «ነፍሶቻቸውም ያረጋገጧት ሲኾኑ፥ለኩራት በርሷ ካዱ፤» (27፡14)

- በራስ ፍላጎት ውስጥ መዘፈቅ፡ አንዳንድ ጊዜ አእምሮ እውነት የሆነውን ነገር ቢያውቅም ይህን እውነት የሆነ ነገር በትክክል ለመምረጥ ድፍረት አይኖረውም፡፡ ምክንያቱም ባለቤቱ በራሱ ፍላጎት ውስጥ የተዘፈቀ ሊሆን ስለሚችል ነው፡፡ ቁርኣን በአንድ ወቅት እውቀት ተሰጥቶት የነበረና በተሰጠውም እውቀት በሕይወቱ ሳለ ይጠቀምበት ይችል የነበረ ሰው የተሰጠውን እውቀት በመተውና ፍላጎቱን ብቻ በመከተሉ ፍጻሜው ትክክለኛ በሆነው ነገር ላይ ለመወሰንም የማይችልበት ደረጃ ላይ እንደነበር በምሳሌነት ነግሮናል፡፡ (7፥175-176)

ቁርኣን ምንጊዜም የሰው ልጅ በሁሉም መስክ አእምሮውን እንዲጠቀም፣እንዲጠይቅ፣እንዲመለከት፣እንዲያስተውል፣ከራሱ፣ከፍጥረታትና ከፍጥረተ-ዓለሙ ትምህርት እንዲቀስም ቅድመ- መስፈርቶችንና ወሰኖችን ሳያስቀምጥ ጥሪ ያቀርባል፡፡

በእርግጥ በውስጡ ያለውንና ከእነሱ ጋር የሚቃረነውን ጥያቄና አስተሳሰብ ነው የሚፈራው፡፡ እውነተኛ የሆነ ሃይማኖት በእርግጥ የሰው ልጅን ከፈጠረውና ይህን የመሰለ አእምሯዊ ተሰጥኦ ካስቀመጠበት ከአላህ መሆን ይገባል፡፡ አላህ አፈጣጠር ለሰዎች ከደነገገው ሃይማኖት ጋር ፈጽሞ ሊቃረን አይገባም፡፡ ታዲያ ጥያቄንና አእምሮን ማሰራትን መፍራት ምንድን ነው? ((ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ብቻ ነው፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ፡፡)) (አል-አዕራፍ ፡ 54)

> ቁርኣን ምንጊዜም የሰው ልጅ በሁሉም መስክ አእምሮውን እንዲጠቀም፣እንዲጠይቅ፣እንዲመለከት፣እንዲያስተውል፣ከራሱ፣ከፍጥረታትና ከፍጥረተ-ዓለሙ ትምህርት እንዲቀስም ቅድመ- መስፈርቶችንና ወሰኖችን ሳያስቀምጥ ጥሪ ያቀርባል፡፡



ማንኛውም ሙስሊም የአላህ አፈጣጠር ለሰው ልጆች መመሪያ ካደረገው ነገር ጋር ፈጽሞ ሊጋጭ እንደማይችል ያምናል፡፡ ይህ ከሆነ ታዲያ ጥያቄ መጠየቅና አእምሮን ማሰራት ምንድነው የሚያስፈራው?

# እስልምና የሰላም ሃይማኖት ነው





# በመገናኛ

በመገናኛ ብዙሃን ከሚደጋገመው ሁኔታ አኳያ- አንዳንድ ሰዎች ሰላም በእስልምና ሃይማኖት ልዩ ስፍራ እንዳለው ሲያውቁ ይደነቃሉ፡፡ ማንኛውም ሙስሊም ሰላም የሚለውን ቃል ትርጉም በውስጡ እያስተዋለ በቀን ውስጥ በርካታ ጊዜ ይደጋግመዋል፡፡

ሰላም የሚለው ቃል መልካም ከሆኑት የአላህ ስሞች መካከል ሲሆን በወዲያኛው ዓለም ያለቸው መኖሪያ ገነትም ስሟ ዳሩ-ስሰላም ነው፡፡ የሙስሊሞች ሰላምታ በሰላም ሲጀምር ሙስሊሞች ስግደት ሰላም የሚለውን ቃል ሁለት ጊዜ በመደጋገም ይቋጫሉ፡፡ ይህን ሁሉ ደግሞ የሃይማኖቱ ስያሜ የሆነው ((እስልምና) በውሰጡ ያዘለውን የሰላምና የመረጋጋት ትርጉም ያጠቃልላል፡፡



ስለዚህ እስልምና ወደሰላምና የደካማዎቹን እንስሳት መብት ማክበር የሚጠራ ሃይማኖት ነው፡፡ መልእከተኛው ሙሐመድ (በእሳቸው ላይ ሰላም ይስፈን)፤ «አንዲት ሴት በድመት ምክንያት ሲኦል ገባች፡፡ ድመቷን እስከትሞት ድረስ አሰረቻት፡፡ አልመገበቻትም አላጠጣቻትም እንዲሁም መሬት ላይ የምታገኘውን እንድትመገብ እንኳ አልተወቻትም፡፡» (ሙስሊም 2242) አንዲት ሴሰኛ እንስት ውሃ ባጠጣቸው ውሻ ሳቢያ ገነት ገባች፡፡ (ቡኻሪ 3280) ብለው ነግረውናል፡፡



(ምንም በአስተሳሰብና በሃይማኖት ብንለያም) እስልምና የሰው ልጆች መብቶች እንዴት እንደሚከበሩና እንደሚጠበቁ የሚደነቁ ምሳሌዎችንና ሕግጋትን አስቀምጧል፡፡ ነብዩ ሙሐመድ አንድ ሙስሊም ሙስሊም ያልሆነን ሰው ቢያሰቃይ ወይም ካቅሙ በላይ ሥራ ቢያሠራው ወይም ቢበድለው በትንሳኤ ቀን ከእሳቸው ጋር ጠላት እንደሚሆን አስጠንቅቀዋል፡፡ (አቡዳዉድ 1044)

ነገር ግን እስልምና ከሌሎች ጋር በመሆን ወደ ሰላም ሲጣራ በእርግጥም በትክክል ወደ እውነተኛ ሰላም እና ለሁሉም ሰው እኩል መብቱን ወደ ሚሰጥ፣ለተበደለ የበደሉን እንዲሁም በሃይል ለተቀማ ንብረቱን ወደሚመልስ የፍትሕ ስርአት ነው እንጂ ለሌባ የሰረቀውን እቃ የሚመልስ እንዲሁም ቤት ያለው ቤቱን በርካሽና ረብ የለሽ ዋጋ እንዲሸጥ ወደ ሚያደራድር ሐሰተኛ ሰላም አይደለም የሚጣራው፡፡

ስለዚህ ለቃላት የሚሰጠው ትርጓሜ ወሰን የለሽ ነው፡፡ መገናኛ ብዙሃን በርካቶች ሸቀጣቸውን የሚያራግፈባቸው፣ የአስተሳሰብ ርእዮታቸውን የሚያሳርፉባቸው መጠቀሚያ ድልድዮች ሆነዋል፡፡ለሁሉም ክስተት በርካታ አንግሎች ያሉት ሲሆን ለሁሉም ታሪክ በርካታ ተራኪ አለው፡፡ ከበርካታ ሰዎች መካከል እውነታን የመፈለግ ሃላፊነት የሚሰማቸው፣ የመገናኛ ብዙሃንን ማስታወቂያዎች የሚጋፈጡና ትክክለኛ መረጃዎችን ከዋና ምንጮቻቸው ለማወቅ የሚፈለጉ፣ አውቀውም ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ በክስተቱ ላይ ሚዛናዊ የሆነ ውሳኔ ለመስጠት የሚሹ ሰዎች ጥቂቶች ናቸው፡፡

ታስተውሉ ዘንድ የተወሰኑ እውነታዎች እንደሚከተለው ተቀምጠውላችኋል፡፡

> ሙስሊም ያልሆነን ሰው የሚበድል፣ የሚጎዳ ወይም ከአቅሙ በላይ የሆነን ስራ የሚያዝ ሰው ክቡር ለሆኑት መልእክተኛ በትንሳኤ ቀን ጠላት እንደሚሆን ነቢዩ ሙሐመድ አስጠንቅቀዋል፡፡

“

እውነት የመፈለግ ሃላፊነቶችን አንግበው የሚንቀሳቀሱ፣ የመገናኛ ብዙሃንም የእውነታውን መረጃዎች ከምንጮቹ ቆፍረው እንዲያወጡና በነገሩ ላይ ሚዛናዊና ተጨባጭ በሆነው እንዲፈርዱ ለማድረግ መገናኛ ብዙሃኑን የሚጋፈጡ ሰዎችን ቁጥር እጅግ በጣም ጥቂት ነው፡፡






እስልምና በአሁኑ ጊዜ ከሃይማኖቶች መካከል በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ ያለ ሃይማኖት ነው፡፡

የሁኔታዎች በወጉ አለመመቻቸት፣የሙስሊሞች ደካማነት፣የመልካምነቱን ስምና ዝና ሆንብለው የሚያጎድፉ፣ለሰዎች የተሳሳቱና በማስረጃ ላይ

ያልተመሰረቱ እንዲሁም ከእስልምና ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸውን መረጃዎች የሚሰጡ ከዚህ አልፎም እውን እስልምና ሰዎችን በማስገደድ ነው ወይስ በማሳመን ላይ የተስፋፋው? የሚለውን ጥያቄ መርምረው ለመመለስ የማይዋጥላቸው የተለያዩ የዓለም የመገናኛ ብዙሃን ቢቀጣጥፉም በአሁኑ ጊዜ እስልምና የአሜሪካንን፣የአውሮፓን፣አፍሪካና የእስያ አህጉራትን በማካለል በዓለማችን ላይ በሚገርም ፍጥነት እየተሰራጨ ያለ ሃይማኖት ነው፡፡ (የሃይማኖት ምርምር ተቋም PEW. Pewresearch.org)

አውነታውን ለሚታዘቡ ግልጽ የሚሆነው ሙስሊሞች የሌሎች ሰዎችን መብቶች እስከጠበቁና ባህሎቻቸውን እስካከበሩ ድረስ ይህ ሁኔታ በሌሎች ልቦና ውስጥ ትልቅ ተጽእኖ ከማሳረፉ በተጨማሪ ሌሎች ሰዎች ወደ እስልምና እንዲገቡ ያደርጋል፡፡ይህ የሙሰሊሞች ችሮታ ሳይሆን አላህ ቁርአን ውስጥ ያረጋገጠውንና ያብራራውን መርህ በመተግበር ነው፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡ ‹‹በሃይማኖት ማስገደድ የለም፤ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፤›› (2፡256)

# ሰዎች እስልምና ውስጥ እንዲገቡ ተገደዋልን?



የሰው ልጅ አስተሳሰቡንና አመለካከቱን በሌሎች ላይ ለመጫን፣ፍላጎቱ ይፈጸምለት ዘንድ እንዲሁም ይዞት የመጣውን ዓላማ ዳር ለማድረስ ሃይልን ተጠቅሟል፡፡ በዚህ ዓይነቱ ድርጊቶች ላይ የተለያዩ ሃይማኖቶችና የአስተሳሰብ አራማጆች ተሳታፊ እንደነበሩ በሚያሳዩ ምሳሌዎች የተሞላ ነው፡፡

ለምሳሌ አዲስ ምድር አቅኚዎች አዳዲስ ምድሮችን ሲያገኙና ወደነዚህ አዳዲስ የምድር ክፍሎች የሚሰደዱ ሰዎችም ቀድሞውኑ በዚያ ምድር ላይ ይኖሩ በነበሩ ቀደምት ነዋሪዎች ላይ ያደርሱ የነበረውን ግፍና ስቃይ ታሪክ ተመልክቶታል፡፡ይህንንም ሁኔታ ሰፔናዊው ቄስ ፓርቶ ሎሚዴ ላስካሳስ በዓይኑ ያየውን እልቂት እንዲህ በማለት ገልጾታል፡፡ «ቀደምት ነዋሪዎችን ልክ እንደ ሰው ልጅ ፍጡር አይመለከቷቸውም ነበር፡፡ እንዲያውም እነዚህን ነዋሪዎች ከእንስሳት ያነሱ ፍጡራን አድርገውም ይመለከቷቸው ነበር፡፡»

(A Brief Account of the Destruction of the Indies by Bartolome de las Casas(Jan 1, 2009)

## ከዚህ አንጻር ሙስሊሞች አዳዲስ ሀገራትን ተቆጣጥረው ሲያስተዳድሩ በነበረበት ወቅት ምን ይፈጽሙ ነበር?

## ሙስሊሞች አንደሉስን (ስፔንን) ለስምንት ክፍለ-ዘመናትአስተዳድረዋል



ሙሰሊሞች በጥንት ስያሜዋ አንደሉስ ተብላ የምትታወቀውን የአሁኗ ስፔንን እ.ኤ.አ ከ 711-1492 ዓ.ል ድረስ ለ781 ዓመታት አስተዳድረዋታል፡፡ በእነዚህ ዓመታትም አንደሉስ (ሰፔን) የስልጣኔ ማዕከል ከመሆኗ ባሻገር በውስጧ የሚኖር ማንኛውም ሰው በሃይል እስልምናን እንዲቀበል አልተደረገም ነበር፡፡እንዲያውም በእነዚህ ዓመታት ሙሰሊሞች ስፔን ውስጥ የነበረው የንግድ እንቅስቃሴ ባለበት እንዲቀጥልና እንዲጎለብት ፣እስልምና ስፔንን ድል አድርጎ እስኪከፍት ድረስ በአይሁዳዊያን ላይ ይደርስ የነበረውን መገለልና መድልኦ በመጣል ለአይሁዳዊያኑ ነጻነታቸውን አጎናጽፏቸዋል፡፡ እነዚህን እውነታዎች ታሪክ በጉልህ አስፈሯቸዋል፡፡

ነገር ግን ሰፔን ውስጥ ንግስት ኤልሳቤትና ንጉስ ፈርዲናንድ በሙስሊሞች ላይ ድል ከተቀዳጁ በኋላ የእስልምና መገለጫዎች የሆኑ ነገሮችን ሁሉ እንዳይታዩ ከልክለዋል፣በርካታ ሙሰሊሞችን ገድለዋል፣ከቤት ንብረታቸው አፈናቅለዋል ይባስ ብለውም እስልምና ሃይማኖት ላይ በሚቆዩና ሃይማኖታቸውን በሚደብቁ ሙስሊሞች ላይ ፍርድ ቤቶች ከባድ የቅጣት ውሳኔ እንዲያስተላልፉባቸውና እንዲቀጧቸው አድርገዋል፡፡

መስሊሞች ተባረዋል፡፡ ከቤት ንብረታቸውም ተፈናቅለዋል፡፡ ነገር ግን ትኩረትን የሚስበው ነገር ከስፔን ሙስሊሞች መባረር ጋር አይሁዳዊያን ስለተባበረሩ ሙስሊሞችን ተቀላቅለው ወደሙስሊም ሐገራት በመሰደድ በጥገኝነት፣ በሰላምና በክብር ኖሩ ችለዋል፡፡



እስልምና ግብጽን ከ1400 ዓመታት በላይ አስተዳድሯል በእነዚህ ዓመታት ውስጥም ለግብጻዊያን ኮፕቲኮች የነበራቸውን ስፍራ ጠብቆላቸዋል

የመልእክተኛው ባልደረባ የሆኑት ዐምር ቢን አል-ዓስ በድል ከከፈቷት ከእስልምና ጅማሮ ጊዜ አንስቶ ሙስሊሞች ግብጽን አስተዳድረዋል፡፡ ሃይማኖታቸውንና ቤተ-አምልኮታቻቸውን ብቻም ሳይሆን የጠበቁላቸው፣ ሃይማኖታቸው አንድ ቢሆንም በሃይማኖት ቀኖና መለያየት ሳቢያ ሮማዊያን ይፈጽሙባቸው ከነበረው ግፍ፣ በደልና ጭቆና ነጻ አውጥተዋቸዋል፡፡ በዚህ ወቅት ለኮፕቲኮች ሃይማኖትና አምልኮታዊ ነጻነታቸው ተመልሶላቸዋል፡፡ በዚያን ወቅት ኮፕቲኮች ቁጥር ከ 5 ሚሊዮን በላይ ነበር፡፡

ሙስሊሞች ሕንድን ለአንድ ሺህ ዓመታት ያህል አስተዳድረው ነበር በወቅቱ ከሕንዳዊያኑ 80% የሚሆኑት ደግሞ ሙስሊም ያልሆኑ ነበሩ፡



ሙስሊሞች የሕንድን ከፊል ግዛት ለአንድ ሺህ ዓመታት ያህል አስተዳድረው ነበር፡፡በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ሙስሊም ላልሆኑ የሌላ እምነት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን፣አምልኮቶቻቸውንና መብቶቻቸውን ከመጠበቃቸውም በላይ በሃይማኖቶቻቸው ምክንያት ይደርስባቸው ከነበረው ጭቆና ነጻ አውጥተዋቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ታሪክ ጸሐፊያን በሙሉ ያረጋገጡት እውነታ እስልምና ሕንድ ውስጥ በሃይል እንዳልተስፋፋና ማንንም በማስገደድ እስልምናን እንዲቀበል ፈጽሞእንዳላደረገነው፡፡

## እስልምና ካለ ጦርነትና ካለምንም የጦር ሃይል የገባባቸው ትልልቅ ሙስሊም ሃገራት



ኢንዶኔዢያ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሙሰሊሞች በአንድ ላይ የሚኖሩባት ሀገር ስትሆን የሕዝቦቿ ቁጥርም ከ250 ሚልየን በላይ ነው፡፡ ከዚህ የሕዝብ ቁጥር ውስጥ 87% የሚሆኑት ሙሰሊሞች ናቸው፡፡ እስልምና ኢንዶኔዢያ ውስጥ የገባው እንደሂጅሪያ አቆጣጠር በስድስተኛው ክፍለ-ዘመን በሙስሊም ነጋዴዎች የላቀ ስነ-ምግባር ምክንያት ነው፡፡ አንድም የሙሰሊም ጦር አልገባባትም፡፡ ቅኝገዢዎቹ ፖርቱጋሎች፣ሆላንዶችና እንግሊዞች እየተፈራረቁ በቅኝ ግዛትነት እስከሚይዟት ድረስ ምንም ደም አልፈሰሰባትም፡፡



# በእስልምና እና በተወሰኑ ሙስሊሞች መካከል ያለው ነባራዊ ሁኔታ



‹‹ይህ አስደንጋጭ ተቃርኖ ምንድን ነው?›› የሚለውን አባባል ወደላቂ የስነ-ምግባር እሴቶች፣ ምድርን ወደማልማት፣ሰዎችን ወደመጥቀምና ሰላምን በሰው ልጆች መካከል ወደማሰራጨት የሚጣሩትን የእስልምናን ድንጋጌዎች እውነታ ጋር በወጉ የተዋወቁ ሰዎች በዙሪያቸው የሚገኙ ከእስልምና ሃይማኖት ጋር ቁርኝት ያላቸው ናቸው የተባሉ አንዳንድ ሰዎች ከእነዚህ እሴቶች ሁሉ የራቁ መሆናቸውን ሲመለከቱ በእርግጥ ሊገረሙ ይችላሉ፡፡ እውን ከዚህ እውነተኛ ሃይማኖት ጋር የተቆራኙ ሰዎች እንዲህ ሊሆኑ ይችላሉን?

እንደእውነቱ ከሆነ ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ግራ ወደማጋባት የሚመራ በመሆኑ ሁኔታውን በተረጋጋ መንፈስ ከተለያዩ አቅጣጫዎች መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ይኸውም፡-

- ከእስልምና ጋር የተቆራኘ ወይም በእስልምና ውስጥ የተወለደ ማንኛውም ሰው ለሁሉም እስላማዊ ድንጋጌዎች እጁን የሰጠ ታዛዥ ነው ብሎ መደምደም አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም ከእስልምና ጋር የተቆራኙ ናቸው የሚባሉና በዙሪያችን የሚገኙ አንዳንድ ሙስሊሞች ከእስላማዊ እሴቶች ሲያፈነግጡና ሲያጓድሉ ከመስተዋላቸው ባሻገር ከስሙ በስተቀር እስልምናን ምንም የማያውቁ ሙስሊሞች አሉ፡፡
- የሂትለር ጭካኔ የመጣው በሃይማኖቱ ምክንያት ነው ወይም ሂትለር የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ስለነበር የክርስትና ሃይማኖት ወደእልቂትና ጭፍጨፋ የሚጣራ ሃይማኖት ነው ወይም ሃይማኖት የለሹ ጆሴፍ እስታሊን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን የገደለው ሃይማኖት የለሽ ሰው በመሆኑ ነበር ማለትና መፈረጅ እንደማይቻለው ሁሉ፤ የሰዎችን ጥፋቶች ከሃይማኖታቸውና ከእምነታቸው ጋር ማቆራኘት ተገቢ አይደለም፡፡ ስለዚህ እነዚህ ዓይነቶቹ ፕሮፖጋንዳዎች ከእውነት የራቁ ናቸው፡፡

> በማንኛውም ሁኔታ የሰዎችን ስሕተቶች ወደሃይማኖቶቻቸውና ወደቀኖናዎቻቸው ማስጠጋት አይቻልም፡፡

- የእስልምናን እውነታ፣ እስልምና የሰላም፣ የእውቀት፣ የብልጽግና መንፈስ እንደሆነ ሁሉም ያወቀበትና የተመለከተበት ምሳሌያዊ ክስተቶች በታላቅነታቸውና በአስገራሚነታቸው ታይተዋል፡፡ ታሪክም በገጾቹ ላይ አስፍሮ ለዓለም አስተዋውቋቸዋል፡፡ እነዚህ በምስራቅ ከሕንድ ከምዕራብ በስፔን የፈነጠቁ እስላማዊ አሻራዎች እስከዛሬም ድረስ ብርሃን አያሰራጨ ይገኛል፡፡ ለዘመናዊው ስልጣኔም መንገድ እየጠረገ ይገኛል፡፡ በስልጣኔ መጥቀዋል የሚባሉት ሐገሮችም መሰረታቸውን ከዚሁ ወስደዋል፡፡

- ማንም ሰው ዘመናዊውን የሕክምና ሳይንስ እያወቀ የተወሰኑ ሐኪሞች መጥፎ ወይም ብልሹ ስለሆኑ ብቻ ከበሽታው መታከም የሚርቅ፣ ወይም ብልሹ ስነ-ምግባር ያላቸው የተወሰኑ መምህራን መኖራቸውን ስላወቀ ብቻ ልጆቹን ከማስተማር ወይም ከትምህርት ቤት የሚከለክል ወላጅ አይኖርም፡፡ የአንድ ነገር እውነታ የሚታወቀው ወደእርሱ በሚጠጉና ከእርሱ ጋር በተቆራኙ ነገሮች ሳይሆን በራሱ ነው፡፡

በጣም የሚደንቀውና የሚገርመው ከጠላቶች ጎራ እስልምናን ለማጠልሸት የሚደረገው ርብርብ ሰፊ ቢሆንም ብዙ ሰዎች እውነታውን ከምንጩ ለማወቅና ትክክለኛ ሃሳቡን ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የሚገኙ በርካታ ሰዎችም እስልምናን እየተቀላቀሉ ይገኛሉ፡፡

> ይህን የተከበረ ሙያ ያዋረዱ ትምህርት ቤቶችን ወይም መምህራንን በማወቁ ምክንያት ብቻ ማንም ሰው ትምህርትን አይዋጋም ወይም ልጆቹን ትምህርት አይከለክልም፡፡





## አዲስ የአስተሳሰብ እይታ

ለራስህ የሚጠቅሙ ውሳኔዎችንና አጋጣሚዎችን ለመወሰን ስንት ጊዜ ነው ያመነታኸው? ለእንደዚህ ዓይነቱ ማመንታት ራስህን እስከዛሬ ትወቅሳላህን?

የሰው ልጅ ትልቁ ክብሩ ነጻነቱና በሚጠቅሙት ነገሮች ላይ ካለማወላወል፣ ካለመፍራትና ካለማመንታት ውሳኔ የማሳለፍ ብቃቱ ነው።።

በአንድ ነገር ፍጻሜ ላይ ጽኑ መሆን ጀግና የሚያሰኝና የሚያስወድስ፣ ክብር የሚያጎናጽፍ ስነ-ምግባር ሆኖ የሚቆጠር ነው፡፡ በአንድ ራስን በሚጠቅም ነገር ላይ ውሳኔ ለመስጠት መቁረጥና ስህተትን አውቆ በጀግንነት መንፈስ በጸጋ ለመቀበል መዘጋጀት ትልቅ የሕሊናና የመንፈስ እርካታ፣ መረጋጋትና ጀግንነት ከመሆኑ ባሻገር በኩራትና መኮፈስ ላይ ታላቅ ድልን መቀዳጀት ነው፡፡ የዚህን መልካም ውጤት ግለሰቡ ራሱ በሂደት የሚመለከተው ነገር ነው፡፡

የእስልምናን ገጽታ ከዋና ምንጩ ለማወቅ እድሉን ለራስህ እስከሰጠህ ድረስ ባነበብከው ለማመዛዘንና ሁኔታዎችን ለማስተዋል ለራስህ እድሉን አትንፈገው፡፡

የዚህ ሃይማኖት ውብት ግልጽ ሆኖ ከታየህ፣ ስለእስልምና ሃይማኖት መገለጫዎች ተጨማሪ ምርምር ማድረግና ጥያቄ መጠየቅ ካስፈለገህ፤ የማንበብ፣ የመጠየቅና ውይይት የማድረግ መስኮቹ ከፊት ለፊትህ ናቸው፡፡ ነገር ግን ከአሁን ጀምረህ ሁኔታዎቹን ከተለያየ አቅጣጫና አመለካከት መቃኘት ይኖርብሃል፡፡



ይህን መጽሐፍ አንበብህ መጨረስህ ለእኛ ከብር ነው። ብርቱ የሆኑ ጥያቄዎችን እንደጫረብህ ወይም ባንተ ዘንድ የምትስማማበቸው ወይም የማትስማማባቸው የሆኑ ሃሳቦችን እንዳነሳሳብህ ተስፋ እንዳርጋለን። አስተያየትህን ወይም ጥያቄህን ወይም ተቃውሞህን ካንተ ማዳመጥ ያስደስተናል። እነዚህን ሁሉ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተነን በደስታ በሙሉ ልብ ለመቀበል ቃል እንገባለን።

በእስልምና ዙሪያ ሌሎች መረጃዎችን ለማግኘት፡

LAUNCHING
CURiOSiTY
JUST SCAN IT.!!

THISISLAM.net

ያለዎትን ተሞክሮን ያካፍሉን

info@modern-guide.com